# ኆኅተ ብርሃን
# ወ
# መክሰተ ጥቅስ

የሽፋን ዲዛይን
የማነ ተካ

በዲያቆን ወንድወሰን መገርሳ

1994 ዓ.ም
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

## መታሰቢያነቷ

ከልጅነት ጀምሮ በእውቀት በሃይማኖት ተኰትኩቼ ላደከባት ለመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ትሁንልኝ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ ላይ ተመስርቶ የተጻፈ።

**ልዩ ማስታወሻ**

ይህን መጽሐፍ ሲያነቡ በተቻለ መጠን መጽሐፍ ቅዱስ ከአጠገብዎ ሊኖር ያስፈልጋል፤ እያመሳከሩ ለማንበብ ይረዳል።

# ምስጋና

«የረዳኝን እግዚአብሔር አመሰግናለሁ።» መዝ. 13፥6

በቅድሚያ የቤተክርስቲያንን ትምህርት አውቄ በመንፈሳዊ ሕይወቴ እንድበረታ ብሎም ዘወትር በሃሳብና በምክር ለሚተባበሩኝ መሪጌታ ቀጸላ መንግስቱ የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መምህር ለሆኑት እግዚአብሔር እድሜና ጤና እንዲሰጣቸው እየለመንኩ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በዚህ የመጽሐፍ ዝግጅት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ በማድረግ ከጐኔ ያልተለዩኝን አቶ የማነ ተካ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ።

ይህንን ጽሁፍ በኮምፒውተር በመጻፍ ቀና ትብብራቸው ሳልተለየኝ መንፈሳዊ እህቶች እና ለፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ሰንበት ት/ቤት ምስጋናዩ ላቅ ያለ ነው።

በገንዘብ ለተባበሩኝ ፈለገ አብርሃም መንፈሳዊ ማኅበር ከፍ ያለ ምስጋና እያቀረብኩ እግዚአብሔር ማኅበሩን እንዲጠብቅልን የዘወትር ጸሎትና ምኞቴ ነው።

በመጨረሻም መንፈሳዊ ምክራቸውና አስተያየታቸው ሳልተለየኝ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

«በእውቀት ዓለም ከስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠው የመጽሐፍ ስጦታ ነው።»

**ስጦታ**

ለ ______________________

ከ ______________________

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
© ALL RIGHT RESERVED.

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


| ተራ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1/ | እግዚአብሔር | 9 |
| 2/ | ምሥጢረ ሥላሴ | 15 |
| 3/ | ምሥጢረ ሥጋዌ | 16 |
| 4/ | ምሥጢረ ጥምቀት | 20 |
| 5/ | ምሥጢረ ቁርባን | 21 |
| 6/ | ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን | 23 |
| 7/ | ስግደት ክብርና አማላጅነት | 24 |
| 7.1/ | እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም | 26 |
| 7.2/ | ቅዱሳን መላእክት | 30 |
| 8/ | ቅዱሳን ሰዎች | 32 |
| 9/ | መጽሐፍ ቅዱስ | 35 |
| 10/ | ሃይማኖትና ምግባር | 36 |
| 11/ | ቤተክርስቲያን | 37 |
| 12/ | ታቦት | 39 |
| 13/ | መስቀል | 45 |
| 14/ | ማዕተብ | 46 |
| 15/ | ሥዕል | 48 |
| 16/ | ዕጣን | 49 |
| 17/ | መብራት | 51 |
| 18/ | ጸንጸል | 52 |
| 19/ | ጾም | 53 |
| 20/ | ጸሎት | 60 |
| 21/ | ንስሐ | 61 |
| 22/ | ምጽዋት | 62 |
| 23/ | አሥራት በኩራት | 63 |
| 24/ | ስዕለት | 64 |
| 25/ | ጋብቻ(ሥርዓተ ተክሊል) | 65 |
| 26/ | ቀንዲል | 68 |
| 27/ | ሜሮን | 69 |
| 28/ | ክህነት | 69 |
| 29/ | ምንኩስና | 71 |
| 30/ | ልሳን | 71 |
| 31/ | ትንቢት | 72 |
| 32/ | በዓላት | 73 |
| 33/ | ጸበል | 75 |
| 34/ | የጽዋ ማኅበር | 76 |
| 35/ | ዝክር | 77 |
| 36/ | ሞትና ሐዘን | 78 |
| 37/ | ተዝካር | 80 |
| 38/ | ጸሎተ ፍትሐት | 81 |
| 39/ | ሐውልት | 81 |
| 40/ | ጥበብ | 82 |
| 41/ | መሐላ | 84 |
| 42/ | ክርስቲያናዊ አለባበስ | 85 |
| 43/ | ቸልተኝነት | 85 |
| 44/ | እውነት | 85 |
| 45/ | ሐሰት | 86 |
| 46/ | ፍቅር | 86 |
| 47/ | ጸብና ክርክር | 87 |
| 48/ | ሰላም | 88 |
| 49/ | ትዕግስት | 88 |
| 50/ | ትዕቢት | 88 |
| 51/ | ትሕትና | 89 |
| 52/ | ቅንዓት | 89 |
| 53/ | ምኞት | 90 |
| 54/ | ፈተና | 90 |
| 55/ | ተስፋ | 91 |
| 56/ | ስድብ | 92 |
| 57/ | ሐሜት | 92 |
| 58/ | ይቅር ባይነት | 92 |
| 59/ | ቁጣ | 93 |
| 60/ | ጉቦኝነት | 94 |
| 61/ | ገንዘብ | 94 |
| 62/ | ልብ | 95 |
| 63/ | የመጠጥ/የስካር/ አስከፊነት | 95 |
| 64/ | መዝሙር | 96 |
| 65/ | ሕመም | 97 |
| 66/ | ቃል ኪዳን | 98 |
| 67/ | ሰላምታ | 99 |


www.ethiopianorthodox.org

68/ ደስታ ............................................. 99
69/ መከራ ............................................. 100
70/ ሕልም ............................................. 101
71/ ራእይ ............................................. 101
72/ ተአምር ............................................. 102
73/ ቃል ............................................. 102
74/ ኢትዮጵያ ............................................. 103
75/ በጸጋው መዳን ማለት ምን ማለት ነው? ... 104
76/ አዋልድ መጻሕፍት ............................ 105
77/ 666 (አውሬው ማነው?) ........................ 106
78/ ጸሎተ ሃይማኖት ............................ 107
79/ ከመናፍቃን እንዴት እንጠበቅ? .............. 109

# መግቢያ

«እውነትን ግዛ አትሽጣትም» ምሳሌ. 23:23

ሁሉን የሚችል ፡ ሁሉን የሚያስችል ልዑለ ባሕርይ አምላካችን እግዚአብሔር ቃሉ እውነት ነው። ለሰው ልጆች ጥበብን እውቀትንም የሚሰጥ እሱ ነው። ለኛ ያልሰጠን ነገር ምንም የለም። ሁሉንም ነገር ሰጥቶናል። ደካሞች ነንና አንዳች የሚያስመካ የእኛ የሆነ ነገር የለንም። ሁሉ የሱ ሁሉ ከእርሱ ነው።

የሰው ልጅ ሕጉን በተላለፈ ጊዜ እንኳን ልጅነትን አጥቶ ሲኖር አንድያ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል። በልጁ ሞት በፈሰሰ ደሙ ፈሳሽነት ዓለም ሁሉ ዳነ። ቅድስት ቤተክርስቲያንንም በወርቀ ደሙ መሰረታት። ቀደሳት አጸናት።

ይህች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተመሰረተችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዓላማዋ በጌታችን የተገኘውን አዲስ ሕይወት፣ የዲያቢሎስን ድል መነሳት ማስተማርና በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘውን ሰላም ላልሰሙት ሕዝቦች ማብሰር ነው።

የበጐ ነገር ሁሉ እናት የሆነችው የምሥጢር ግምጃ ቤት ቅድስት ቤተክርስቲያን ትላንትና ዛሬም ቢሆን ነገ ከአምላካችን የተገኘውን የመዳን ጥሪ ታሰማለች ሰዎችን በቀና መንገድ እየመራች የእውነትን በር እያሳየች ትገኛለች፤ ሰምቶ መቅረብና መዳን የእኛ ድርሻ ነው።

ዛሬ ግን ብዙዎች በሥጋ ምኞት በመሸነፍ የእውነትን መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ፣ የቤተክርስቲያንን ትምህርት በሐሰት ለመበረዝ ፣ ስማቸውንና ቁጥራቸውን ለማወቅ እንኳን እስኪያዳግት ድረስ ልዩ ልዩ እምነቶች በዝተው ከመቸውም ጊዜ በበለጠ መልኩ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ቅዱስ ቃሉ «ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ እንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» ይለናል። ዕብ. 13:9

በመሆኑም ቤተክርስቲያን ከተመሰረተች ጊዜ አንስቶ ባሳለፈችው ዘመናት ሁሉ ከተጠራጣሪዎች የኑፋቄ ቀስት ሳይሰነዘርባት ያለፈችበት ዘመን የለም። ነገር ግን የሚሰነዘረው ቀስት ሁሉ ቤተክርስቲያንን

www.ethiopianorthodox.org

ማድማት፣ ማሸነፍ አልቻለም:: ዛሬም የተለያዩ እንግዳ ትምህርት በማንገብ ተመሳስለው ወደ በጐች በረት ለመግባትና መንጋውን ለመበተን ብዙ ተኩላዎች ቢነሱም የማንነታቸው የክህደት ለምድ እየተገለጠ በኀፍረት እየተመለሱ ይገኛሉ::

ይህንን ሁሉ ፈተና ማለፍ የቻለችውም በክርስቶስ ደም የተመሠረተች ቤት ስለሆነች ነው:: እኛም ዛሬ እውነትን መከተል በቃሉም መታመን ይገባናል:: «የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናል::» ዕብ. 3:14

ስለዚህ በየጊዜው ከሚነሱት መናፍቃን መጠበቅና መልስ መስጠት የሚቻለው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ዶግማዋን፣ቀኖናዋን ጠንቅቀን ስናውቅና ሥርዓቷን ስንጠብቅ ነው:: «ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ::» ይላል፡፡ 1ኛጴጥ. 3:15

የዚህ መጽሐፍ ርእስ ኆኅተ ብርሃን ወመክሰተ ጥቅስ ማለትም የብርሃን በር (ደጅ) እና የጥቅስ ማውጫ የሚል ነው:: በጨለማ ዓለም ለነበረው ሕዝብ ሁሉ እውነተኛ ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ዮሐ. 8:12 በዚህ የእውነተኛው ብርሃን በር ደግሞ አሁን ተኛ በጐች የሚገቡበት የሚመላለሱበት ደጅ ነው:: ዮሐ. 10:7

በመጽሐፉ ሽፋን የሚታየው መንበር ሲሆን በላዩም ላይ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ ቅድስት ሥላሴ፣እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ታቅፋ ከቅዱሳን መላእክት ጋር፣እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል የያዘው በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ገላጭነት የተጻፈው መጽሐፍቅዱስ ፣ ቅዱስመስቀል፣ ስንዴውና ወይኑ ደግሞ ጌታ በመስቀል ላይ የሰጠን ቅዱስ ሥጋ ፡፡ ያፈሰሰልን ክቡር ደም ነው::

በዚህች መጽሐፍም ውስጥ ለማካተት የታሰበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እምነት፣ሥርዓት፣ትውፊት፣ክብረ ቅዱሳን፣ንዋያተ ቅድሳትን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን በተመለከተና በተቃዋሚዎች መናፍቃን ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል:: ይኸውም በጥልቀት ለማሳወቅ ሳይሆን ተቀድቶ ከማያልቀው የቤተክርስቲያን ትምህርት የተጨለፈች በመሆኗ ለመነሻ ያህል ነው:: ለመምህራንና ለምእመናን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫ ፣ መናፍቃንን መቃወሚያነት የምትረዳ ናት:: አንብበው ይጠቀሙበት::

ዲያቆን ወንድወሰን መገርሳ

# ፩. እግዚአብሔር

እግዚአብሔር የማይመረመር ረቂቅ፡ ጥንት የነበረ ቀዳማዊ፣ ዛሬም ያለ ማዕከላዊ ፣ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ደኃራዊ ፣ በዚህ ጊዜ ... ተገኘ፡ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይሉት ነዋሪ፣ ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር ያለምንም አማካሪ ያመጣ፣ ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ አልፋና ኦሜጋ ... ዘላለማዊ አምላክ ነው::

በባህርዩም ምንም ጉድለት የሌለበት እሱ ቢሰጥ እንጂ ሰጡኝ ... የማይል ሁሉን ማድረግ የሚቻለው ባለጸጋ፥ የእጆቹ ሥራዎች ለሆንን ለእኛ ዘወትር ፈቃዳችንን አስተካክሎ የሚፈጽምልን ፣ ዕለታትን ... ማምንታትን፥ ወራትንና ዓመታትን ሁሉ እያፈራረቀ የሚኖር፣ ሁሉም ነገር ሲያልፍ እሱ ግን የማያልፍ ብቻውን ለዘላለም የሚኖር ኃያል ጌ... ነው::

| | | |
|---|---|---|
| መዝ 89፥1 | መዝ 101፥26 | ኢሳ 40፥13 |
| ሐዋ 4፥24 | ራእይ 1፥8 | ዘፍ 1፥1 |

## ፩.፩ እግዚአብሔር በባሕርዩ

- ዘላለማዊ ነው:: መዝ 89፥2 ፣ 101፥24 ፣ ኢሳ 44፥6 ፣ ያዕ 1፥11
- ቅዱስ ነው:: ዘሌ 11፥44 ፣ 19፥2 ፣ ዘጸ 15፥11 ፣ 1ኛ ሳሙ 2፥2
  ኢሳ 6፥3 ፣ ዕን 1፥13 ፣ ኢሳ 6፥3 ፣ 1ኛ ጴጥ 1፥16
- ሁሉን ቻይ ነው:: ዘፍ 18፥14 ፣ ኢሳ 40፥27 ፣ ኤር 32፥17
  ዳን 4፥35 ፣ ኢዮ 42፥2 ፣ መዝ 134፥6
  ማቴ 19፥26 ፣ ሉቃ 18፥27



www.ethiopianorthodox.org

- <u>በሁሉ ቦታ ምሉዕ ነው</u>።  መዝ 138፡7-11 ፤ ኤር 23፡23
  ዮሐ 1፡9 ፤ ሐዋ 17፡27

- <u>ሁሉን አዋቂ ነው</u>።  መዝ 32፡11 ፤ 93፥8 ፤ 138፥1-6 ፤
  ሕዝ 11፥5 ፤ ሮሜ 11፥33 ፤ ዕብ 4፥13 ፤
  ዕብ 6፥17
- <u>የማይለወጥ ነው</u>።  1ኛ ሳሙ 15፥29 ፤ ሚል 3፥6 ፤ ሮሜ 11፥29
- <u>እውነተኛ ፈራጅ ነው</u>።  ዘሌ 26፥3 ፤ ኢሳ 9፥7 ፤ ማቴ 3፥12
- <u>ፍቅር ነው</u>።  1ኛ ዮሐ 4፥8፥16 ፤ ሮሜ 5፥8 ፤ ኤፌ 2፥5
- <u>ቸር፥ መሐሪ ፥ ይቅርባይ ነው</u>።  መዝ 33፥8 ፤ 102፥8-13፤ 144፥9
  2ኛ ዜና 30፥9 ፤ ሰቆ 3፥22 ፤
  ዮናስ 4፥2

## ፩.፪ <u>የእግዚአብሔር ስሞች</u>

እግዚአብሔር ለባሕርዩና ለግብሩ ተስማሚ የሆነ ስም ያለው አምላክ ነው።

✞ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለአብርሃም ሁሉን ቻይ መሆኑን ኤልሻዳይ (ከሃሌ ኩሉ) በሚል ስም ራሱን ገለጠ።
ዘፍ 17፥1  ዘጸ 6፥3  ሕዝ 10፥15

✞ ለአገልጋዩ ሙሴ ዘሃሎ ወይሄሉ (አህያ ሽራህያ) ያለና የሚኖር፤ እና አምላከ አብርሃም፥ አምላከ ይስሐቅ፥ አምላከ ያዕቆብ ተብሎ እንዲጠራ ፈቀደ። ዘጸ 3፥14 ፤ ዘጸ 3፥16



www.ethiopianorthodox.org

✞ ቀጥሎ ያህዌ የሚለውን ስም ግልጽ አደረገ። ይህም "እግዚአብሔር" በሚል ቃል ተተክቶ ይገኛል።
ዘፍ፡ 22፥14  ዘጸ 17፥15

✞ ከዚህ በተጨማሪ አዶናይ (ጌታ)፤ ኤሎሄ (አምላኬ)፤ ተብሏል።
መዝ 34፥23  ማቴ 27፥46

እንዲሁም

⇨ ሕያው እግዚአብሔር፥ ዳን 6፥20
⇨ ጌታ እግዚአብሔር፥ መዝ 8፥1 ፤ ኢሳ 50፥5
  ሕዝ 2፥4 ፤ ሕዝ 21፥24
⇨ ልዑል እግዚአብሔር፥ ዳን 5፥18 ፤ ዘፍ 14፥18
⇨ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ 2ኛ ሳሙ 7፥26
  ኢሳ 44፥6 ፤ 47፥4
⇨ የእስራኤል ቅዱስ፥ ኢሳ 41፥4 ፤ 30፥50 ፤ 45፥11
⇨ የእስራኤል አምላክ፥ ኢሳ 48፥1

እየተባለ በመጽሐፍ ተጠርቷል።

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ስሙ ታላቅ ፥ ክቡር ፥ ገናና ፥ ቅዱስ ነው።

| | |
|---|---|
| መዝ 32፥20 | ሚል 1፥11 ፤ 2፥2 |
| መዝ 53፥1 | ኤር 10፥6 |
| መዝ 110፥9 | ሕዝ 39፥7 |
| መዝ 134፥1-3 | ሉቃ 1፥49 |
| ምሳ 18፥8 | ፊልጵ 2፥9 |

## ፩.፫ ሃያ ሁለቱ (22ቱ) የእግዚአብሔር ስሞች

መዝ 118 ፤ ሰቆ. ኤር ከምዕ. 1- ምዕ. 4

፩. **አሌፍ** :- ብሂል አሐዱ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር የአለም፥ የሁሉ ፈጣሪ ነው።

፪. **ቤት** :- ብሂል ባዕል እግዚአብሔር

" :- ማለት ጌታ እግዚአብሔር ሁሉን መስጠት የሚችል ባለፀጋ አምላክ ነው።

፫. **ጋሜል**:- ብሂል ግሩም እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ሊመረምሩት የማይቻል ግሩም ፥ ድንቅ ነው።

፬. **ዳሌጥ** :- ብሂል ድልው እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ለዙፋኑ የተገባ ነው።

፭. **ሄ** :- ብሂል ሀልው እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ዘላለማዊ አምላክ ነው።

፮. **ዋው** :- ብሂል ዋሕድ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር በሥልጣን፥ በአገዛዝ፥ በባሕርይ አንድ አምላክ ነው።

፯. **ዛይ** :- ብሂል ዝኩር እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ እየታሰበ የሚመሰገን ፈጣሪ ነው።



፰. **ሔት** :- ብሂል ሕያው እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ያለና የሚኖር ዘላለም ሕያው አምላክ ነው።

፱. **ጤት** :- ብሂል ጠቢብ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ጥበበኛ ነው።

፲. **ዮድ** :- ብሂል የማን እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ቀኝ (ሀያልና ፅኑ) ነው

፲፩. **ካፍ** :- ብሂል ከሀሊ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

፲፪. **ላሜድ**:- ብሂል ልዑል እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ከፍ ያለ ነው።

፲፫. **ሜም** :- ብሂል ምዑዝ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር የሚማርክ መዓዛ ያለው አምላክ ነው።

፲፬. **ኖን** :- ብሂል ንጉሥ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር የነገሥታት ንጉሥ ነው።

፲፭. **ሳምኬት** :- ብሂል ሰፋኒ እግዚአብሔር

" :- ማለት እግዚአብሔር ሁሉን የሚገዛ ፥ የበላይ ፈራጅ አምላክ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፮. | ዔ | :- | ብሂል ዐቢይ እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር ታላቅ ገናና ፥ ከፍ ያለ አምላክ ነው:: |
| ፲፯. | ፌ | :- | ብሂል ፍቁር እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር ሁሉን ወዳጅ፥ በሁሉ ተወዳጅ ነው:: |
| ፲፰. | ጻዴ | :- | ብሂል ጻድቅ እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ነው:: |
| ፲፱. | ቆፍ | :- | ብሂል ቅሩብ እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር ቅርብ ነው:: |
| ፳. | ሬስ | :- | ብሂል ርዑስ እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር ክብሩ ከእርሱ ለእርሱ የተገኘ መልካም ጌታ ነው:: |
| ፳፩. | ሳን | :- | ብሂል ስቡሀ እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር ምስጉን ነው:: |
| ፳፪. | ታው | :- | ብሂል ትጉሀ እግዚአብሔር |
| | " | :- | ማለት እግዚአብሔር ድካም ፥ እንቅልፍ የሌለበት ትጉህ ጠባቂ ነው:: |



## ፪ ምሥጢረ ሥላሴ

ሠለሰ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ሦስት አደረገ ማለት ነው:: ሥላሴ ማለት ሦስትነት ማለት ነው::

እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ፥ ሦስት ሲሆን አንድ ነው:: እግዚአብሔር የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት መጠሪያ ስማቸው ነው:: የእግዚአብሔር አንድነት በመለኮት፣ በሕልውና፣ በአገዛዝ በባሕርይ፣ በመፍጠር፣ በሥልጣን፣ በፈቃድ በመሳሰሉት ነው::

ዘፍ. 1:1 ፣ መዝ. 101፥25፣ ዮሐ. 10፥30 ዮሐ. 14፥10

የእግዚአብሔር ሦስትነት በስም፣ በአካል፣ በግብር ነው::

የስም ሦስትነት:- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣
ማቴ.28፥19

የአካል ሦስትነት:-ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዳቸው ፍጹም መልክዕ፣ ገጽ፣ አካል አላቸው::
ማቴ.3፥16

የግብር ሦስትነት:-አብ ወላዲ አስራጺ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ከአብ የሰረጸ
ዮሐ. 15፥26

ሦስቱም በባሕርይ መለያየት፥ በአካል መቀላቀል ሳይኖርባቸው ስማቸውና ግብራቸው ሳይፋለስ በአንድነት በሦስትነት ጸንተው ለዘላለም ይኖራሉ::

ሀ/ አንድነትና ሦስትነት በብሉይ ኪዳን

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ. 1፥26 | ዘፍ.18፥1-15 | መዝ. 32፥5 |
| ዘፍ. 2፥18 | ዘጸ. 3፥6 | መዝ. 117፥15 |
| ዘፍ. 3፥22 | ዘኁ. 6፥24 | መዝ.146፥5 |
| ዘፍ. 11፥6 | 1ኛ.ሳሙ. 2፥2 | ኢሳ. 6፥1-8 |



www.ethiopianorthodox.org

## ለ/ ምሥጢረ ሥላሴ በሐዲስ ኪዳን

| | | |
|---|---|---|
| ማቴ.3÷17 | ዮሐ.10÷30 | 2ኛቆሮ.13÷14 |
| ማቴ.17÷1-8 | ዮሐ.14÷10 | 2ኛተሰ.2÷16-17 |
| ማቴ.28÷19 | ዮሐ.14÷23-27 | 1ኛ ጴጥ.1÷1-2 |
| ማር.1÷9-11 | ዮሐ.15÷26 | 1ኛዮሐ.5÷7(የ1878 ዓ.ም እትም መጽሐፍ ቅዱስ) |
| ሉቃ.1÷35 | ዮሐ.16÷15 | |
| ሉቃ.3÷21 | 2ኛዮሐ. 3 | |

* ሥላሴ የሚለው ስም በ81ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል::

| | | |
|---|---|---|
| ሲራክ 3÷22 | ሄኖክ 5÷38 | ጥበብ 6÷6 |
| ሲራክ 15÷17 | ሄኖክ 6÷24 | ዕዝራ ሱቱ. 4÷5 |
| ሲራክ 39÷21 | ሄኖክ 13÷14 | ዕዝራ ሱቱ.12÷48 |
| ሲራክ 44÷17 | ሄኖክ 17÷17 | ጦቢት 8÷6 |

ስለዚህም ቤተክርስቲያን አንድ አምላክ ብላ ታምናለች እንጂ ሦስት አማልክት አትልም:: አምላካችን እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው::

| | | |
|---|---|---|
| ዘዳ. 6÷4 | 2ኛ ሳሙ. 7÷22 | ኢሳ. 44÷6 |
| ዘዳ. 32÷39 | መዝ. 82÷18 | ሚል. 2÷10 |
| | ኤፌ. 4÷6 | |

## ፫ ምሥጢረ ሥጋዌ

ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ ( ቃል ) ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ሳይለይ በተለየ አካሉ ሰው የሆነበት ምሥጢር ነው:: እርሱም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በቅድምና የነበረ፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ የተወለደ፣ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ አዳምን ለማዳን ሰው የሆነ የባሕርይ አምላክ ነው::

| | | |
|---|---|---|
| መዝ.2÷7 | ዳን.9÷26 | ዮሐ.1÷14 |
| መዝ.109÷3 | ሲራክ.24÷6 | ሮሜ.5÷12 |
| ኢሳ.7÷14፣9÷6 | ማቴ. 1÷22 | ገላ.4÷4 |



### ሀ/ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው::

| | |
|---|---|
| ዘጸ.3:14 ⇔ ራእይ.1÷8 | ኢሳ.40÷3 ⇔ ማር.1÷2 |
| መዝ.2:7 ⇔ ገላ.4:4 | ኢሳ.40÷10 ⇔ ራእ.22÷12 |
| መዝ.46:5 ⇔ ሉቃ.24÷50 | ኢሳ.44÷6 ⇔ ራእ.22÷13 |
| መዝ.49:2 ⇔ ሐዋ.1÷11 | ኤር.9÷23 ⇔ 1ቆሮ.1÷30 |
| መዝ.77:65 ⇔ ማቴ.28÷1 | ኤር.31÷31 ⇔ ዕብ.8÷11 |
| መዝ.106:13 ⇔ ማቴ.4÷16 | ኢዩ.2÷32 ⇔ ሐዋ.2÷21 /ሮሜ.10÷13/ |

### ለ/ ከመጀመሪያም የነበረ ዛሬም ያለ ለዘላለም የሚኖር ፈጣሪ ነው::

| | | |
|---|---|---|
| ሚክ.5:2 | 1ኛቆሮ. 8÷6 | ዕብ.13÷8 |
| ዮሐ.1:1-3 | ዮሐ. 8÷56፣17÷5 | ቈላ.1÷7 |

### ሐ/ የባሕርይ አምላክ ነው::

| | | |
|---|---|---|
| ኢሳ. 9÷6 | ማቴ.22÷31 | ሮሜ. 9÷5 |
| | 2ኛጴጥ.1÷1 | 1ኛ ዮሐ. 5÷20 |

### መ/ የጌቶች ጌታ የአማልክት አምላክ ነው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ.109÷1 | ሐዋ.9÷5 | 1ኛቆሮ.8÷5 | ራእ.19÷11-16 |
| መዝ.135÷2 | ሮሜ.10÷9 | 1ኛጢሞ.6÷15 | ራእ.17÷14 |
| | | | ራእ.22÷21 |

### ሠ/ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአገዛዝ፣ በሥልጣን፣ በመለኮት፣ በሕልውና አንድ ነው::

| | | |
|---|---|---|
| ማቴ. 28÷19 | ዮሐ. 10÷30 | ዮሐ. 8÷58 |
| 1ኛዮሐ. 2÷23 | | |

### ረ/ ተማላጅ ነው እንጂ አማላጅ አይደለም::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማቴ.25÷35 | ዮሐ.5÷8 | *ዮሐ.16÷26 | ሮሜ.14÷11 |
| ማር.10÷48 | ዮሐ.9÷6 | ዮሐ.17÷5 | 2ኛቆሮ.5÷10 |



www.ethiopianorthodox.org

✞ መናፍቃን ጌታን አማላጅ ነው ብለው ለማሳሳት ከሚጠቅሷቸው መካከል ትክክለኛው ጥቅስ ማስረጃ፣

ሮሜ 8÷34 «የሚፈርድ ማነው፤ ክርስቶስ ኢየሱስ ሞተ፣ ከሙታንም ተለይቶ ተነሣ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፣ ስለእኛም ይፈርዳል።» ይፈርዳል እንጂ ይማልዳል አይልም።

1ኛ ጢሞ 2÷5 «አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

1ኛ ዮሐ 2÷1 «ልጆቼ እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፣ የበደለም ቢኖር ጻራቅሊጦስ አለን፣ ከአባት ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ቸር ነው፣ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ።»

(በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የሊቃውንት ጉባኤ በ1975 ዓ.ም የተዘጋጀ ግዕዝና አማርኛ ሐዲስ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳን አማርኛ 1938 ዓ.ም. የታተመ ይመልከቱ።)

ኢየሱስ ክርስቶስ ከፅንሰት እስከ ዕለተ ዓርብ ድረስ በዚህ ዓለም በአካለ ሥጋ ተመላልሶ በመጨረሻ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በፈጸመልን ካሳ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስና ከራሱ ጋር አስታረቀን። ስለዚህ በዕብ. 7÷25 ላይም ካሳ በመስቀል ላይ ከተፈጸመ በኋላ ለወደፊት እንደሚያማልድ አድርጐ በትንቢት አንቀጽ ተናገረ እንጂ ድርጊቱስ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተፈጽሟል። ካሳ ከተፈጸመ በኋላ ግን አስታራቂ አማላጅ አይባልም

📖 ማስረጃ፡- ዮሐ. 19÷30 ዮሐ. 5÷21 ገላ.1÷7-9 ቈላ.1÷22 ዕብ.5÷7 ዕብ.9÷25

✞ ኢየሱስ ክርስቶስ የግል አዳኝ ሳይሆን የዓለም አዳኝ ነው።
ዮሐ 4÷42 ፣ ሉቃ. 2÷18 ፣ ዕብ 6÷6 ፣ 9÷28

✞ ምልጃ የቅዱሳን የፍጡራን ነው። ጌታ አይለምንም አይማልድም። 2ኛቆሮ.5÷18-21 ዮሐ.16÷26 2ኛቆሮ. 9÷14

✞ ቅዱሳን ጌታ ሲመጣ በክብር ዙፋን ተቀምጠው ይፈርዳሉ።
ማቴ. 19÷27-29 ፩ኛ ቆሮ. 6÷2



ሠ መንፈስ ቅዱስ

ፍጹም መለኮታዊ አካል ያለው ፍጥረታት ሁሉ ጸንተው የሚኖሩበት ምሉዕና ረቂቅ የማይጨበጥ የማይዳሰስ የባሕርይ አምላክ ነው። ከአብ የሠረጸ /የወጣ/ ከአብ ከወልድ ጋር በሥልጣን እኩል የሆነ፣ ከመጀመሪያው የነበረ ለዘላለም የሚኖር ነው።

ሀ/ እግዚአብሔር ነው

ዘጸ.17÷7, መዝ.96÷6-11 } ዕብ.3÷7
ኢሳ.6÷8-10 ⇔ ሐዋ.28÷25-26
ኢሳ.40÷13 ⇔ 1ኛቆሮ.2÷10

መዝ.138÷7 } 1ኛቆሮ.12÷11, ዮሐ.14÷26
ኤር.31÷32 ⇔ ዕብ.10÷15
ኢሳ.61÷1
ዕብ.9÷14

ለ/ ከአብ ከወልድ ጋር በሥልጣን በአገዛዝ እኩል መሆኑ

| | | |
|---|---|---|
| መዝ.138÷7 | ሐዋ.2÷33፤5÷3 | ሮሜ.15÷19 |
| ኢሳ.40÷13 | ዮሐ.14÷15-16 | 1ኛቆሮ.2÷10 |
| ኢሳ.48÷16 | ዮሐ.14÷26 | 2ኛቆሮ.13÷14 |
| ማቴ.28÷19 | ዮሐ.15÷26 | 1ኛጴጥ.1÷1 |

ሐ/ ረቂቅ አካል ያለው ነው።

| | |
|---|---|
| ኢሳ. 48÷16፣ 61÷1 | ሐዋ. 1÷8 |
| ኢሳ. 63÷10 | ሐዋ.15÷18 |
| ማቴ. 3÷16 | ሮሜ. 8÷16 |
| ሉቃ. 1÷35 | |

መ/ ፈጣሪ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ.1÷2 | ሐዋ.2÷1 | ሮሜ.8÷1 |
| ኢዮ.26÷13፤ 33÷4 | ሐዋ.5÷19 | 1ኛቆሮ.2÷10 |
| መዝ.103÷29 | ሐዋ.8÷15 | ዕብ.9÷14 |



www.ethiopianorthodox.org

## ፬. ምሥጢረ ጥምቀት

ጥምቀት ከእብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ተወልደን የሥላሴን ልጅነት የምናገኝበት ምሥጢር ነው።

ማር. 16፥16 ዮሐ. 3፥5 ቲቶ. 3፥5
1ኛ ጴጥ. 3፥21

✞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዘመኑ በዮርዳኖስ፥ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ጥምቀታችንን መሰረተልን፤ ባረከልን፤ ቀደሰልን።

ማቴ. 3፥15፤ ቈላ.2፥14

✞ ጥምቀት የሚፈጸመው በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው።

ማቴ.3፥1 ማቴ.28፥19

✞ ጥምቀት አንዲት ናት፤ አትደገምም።

ኤፌ.4፥5 ፤ ሮሜ.15፥20፤ 1ኛቆሮ.3፥1 ቈላ.2፥12

✞ <u>ሕጻናት በ40 እና በ80 ቀን የመጠመቃቸው ምክንያት</u>

ዘሌ.12፥1-8፤ መዝ.8፥2 ፤ ኢሳ.49፥22 ፤ ኤር.1፥5፤ ኩፋሌ.4፥9፤

ሉቃ.1፥15፤ ሐዋ.2፥39፤ 10፥33፤ 16፥15፤18፥8፤1ኛቆሮ. 1፥16

✞ <u>የጥቅምት ትንቢትና ምሳሌ</u>

ዘፍ.12፥1፤ ዘጸ.14፥1፤2ኛነገ.6፥1፤መዝ.76፥16፤113፥4 ሕዝ.36፥25



እምነት ነው እንጂ ጥምቀት አያድንም ለሚሉት።
«... ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። » ሮሜ. 3፥26 ይህን ጠቅሰው መጠመቅ አያድንም የሚሉ አሉ።

ጥምቀት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰረተ ሲሆን ራሱ አምላክ ተጠምቆ እንድንጠመቅ አዘዘን። /ማቴ 4፥1፤ ዮሐ.3፥5/ ስለዚህ የክርስቶስን አምላክነት የወንጌልን እውነት ያመኑ ሁሉ እንዲጠመቁ ታዘዋል። (ሐዋ.2፥38፤16፥16-31፤ 22፥16) ያለ ጥምቀት ድኅነት የለም። /ማር.16፥16/

በጌታ ቀኝ ተሰቅሎ የነበረው ፈያታዊ ዘየማን ሳይጠመቅ እንዴት ዳነ ቢባል? ጥምቀት 1/ በውኃ ዮሐ. 3፥5 2/ በእሳትና በመንፈስ ዮሐ. 3፥1 3/በደም 1ኛዮሐ. 5፥6 ይፈጸማል። ስለዚህ ፈያታዊ ዘየማን የደም ጥምቀት ፈጽሟል። በመሆኑም የክርስቶስን ደመ ማኅተም ይዞ ወደ ገነት ገብቷል። /ሉቃ. 23፥43/

## ፭. ምሥጢረ ቁርባን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ለደቀመዛሙርቱ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ፤ ይህ ደሜ ነው ጠጡ ብሎ ለሐዲስ ሥርዓት የብዙዎችን ኃጢአት ለማስተስረይ የሰጣቸው፥ እኛም የዘላለም ሕይወትን የምናገኝበት የሕይወት ምግብና መጠጥ ነው።

ማቴ.26፥28 ሉቃ. 22፥19 1ኛ ቆሮ. 10፥16
ማር. 14፥22 ዮሐ. 6፥33-56 1ኛ ቆሮ. 11፥23

<u>የጌታ ሥጋና ደም መታሰቢያ ነው ለሚሉት</u>

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እማናዊ ነው ብላ ታምናለች ትመሰክራለች። ነገር ግን በፕሮቴስታንት ዘንድ የጌታ ሥጋና ደም መታሰቢያ ነው ሲሉ «ይህን



www.ethiopianorthodox.org

ለመታሰቢያዬ አድርጉት » ሉቃ. 22፥19 ያለውን ይጠቅሳሉ:: እዚህ ላይ ልንረዳው የሚገባን ነገር አለ::

ቅዱስ ጳውሎስ « እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው:: በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት » አለ 1ኛቆሮ. 11፥23-25 መታሰቢያ ሲል ሥጋውን ደሙን በተቀበልን ጊዜ ሞቱን መከራውን ማሰብ ማለት ነው:: በቅዳሴ ላይ «ንዜኑ ሞተከ» የሚባለው ለዚህ ነው:: ሞትህን ፣ ትንሣኤህን፣ ዕርገትህን፣ ዳግም ምጽአትህን እንናገራለን ይባላል:: ለዚህም ምርጥ እቃ የተባለው ቅዱስ ጳውሎስ «ይህንም እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ» ብሏል 1ኛ ቆሮ. 11፥26:: ስለዚህ መታሰቢያ ሲል ሥጋውንና ደሙን ስንቀበል የጌታ ግርፋቱን ፣ በመስቀል መሰቀሉን ፣ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዕርገቱን፣ ዳግም ምጽአቱን በልባችን እያሰብን ፣ በአፋችን እየመሰከርን እንቀበላለን እንጂ ሕይወት የሚሰጠውን ፣ ከኃጢአት ቀስል የሚፈውሰውን ፣ መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ የሚሆነውን ሥጋና ደም መታሰቢያ ነው አንልም:: ጌታም አማናዊ መሆኑን ሲያረጋግጥልን « ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው» ብሉናል:: ዮሐ. 6፥55 ይህንንም አምነን እንቀበላለን:: ለሐዋርያትም ይህን ስርዓተ ምሥጢር በምሴተ ሐሙስ ባሳያቸው ጊዜ « ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራውን አንስቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ:: ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ:: ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው::» /ማቴ. 26፥26-27፣ ሉቃ. 22፥17-20፣ ዮሐ. 6፥51፣ ማር. 14፥22-25/ ደቀመዛሙርቱም አማናዊ ነው ብለው ተቀብለውታል:: ሥጋውና ደሙ መታሰቢያ ነው ከተባለ የዘላለም ሕይወት ባልተገኘበት ነበር:: እርሱም ጌታ ይህ ሥጋዬ ነው ደሜ ነው አለ እንጂ ምሳሌ ነው አላለም:: « ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው » ሲል ጌታ አስተምሯል:: ዮሐ. 6፥54 ስለዚህ የጌታ ሥጋና ደም የዘላለም ሕይወትን የሚሰጥ አማናዊ (እውነተኛ) መድኃኒት ነው:: ስለዚህ የቀራኒዮን ውለታ በመስቀል ላይ የተገለጸውን ፍቅሩን መከራውን ሞቱን እያሰብን ወደ እርሱ ልንቀርብ ያስፈልገናል::



## ፮. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

የሰው ነፍስ ከእግዚአብሔር ከአፉ እስትንፋስ የተገኘች ስለሆነች ሕያዊት/ዘላለማዊት/ የማትሞት ነዋሪ ናት:: ዘፍ. 2፥7 ሰው ከሞተ በኋላ የፈረሰና የበሰበሰ ሥጋው ከሕያዊት ነፍስ ጋር ተለያይቶ ሲኖር በመጨረሻ ዘመን ጎብረት ኖሮት በሞይሞትና በማይፈርስ ሥጋ የሚነሳ መሆኑን የሚያስረዳ ምሥጢር ነው::

ማቴ.22፡29 ሐዋ.24፥15 1ኛቆሮ.4፥16 ኢሳ.26፥19
ሆሴዕ.13፡14 ዮሐ.5፥28 1ኛቆሮ.15፥35 ራእይ.20፥12
ዳን.12፡2 መክ.3፥19

ሀ/ ገነት

በመጀመሪያ አዳም ይኖርባት የነበረች በኋላ ግን ዕፀ በለስን በልቶ የወጣባት ናት:: ዘፍ. 2፥8 ለጻድቃን ከሞት በኋላ ለነፍሳቸው ማረፊያ የምትሆን መካነ ተድላ ናት::
ኢሳ.51፥3፣ ሕዝ.36፥35፣ ሉቃ.23፥43፣ 2ኛቆሮ.12፥4፣ ራእይ2፥7

ለ/ ሲኦል

ሲኦል ማለት ጉድጓድ /መቃብር/ ማለት ነው:: የኃጥአን ሰዎች ነፍስ እስከ እለተ ምጽአት ድረስ የሚቀጣባት የስቃይ ቦታ ነች:: ኩፋሌ 8፥25 መዝ. 9፥17፣ 15፥10፣ 29፥3 ምሳሌ 15፥24 ፣ ሉቃ. 16፥22-31 ፣ ራእይ 20፥13

ሐ/ <u>ገሃነመ እሳት</u>

ኃጥአን በምጽአት ጊዜ ተፈርዶባቸው በሐዘን እየተሰቃዩ የሚኖሩበት የቅጣት ስፍራ ነው::
ዳን. 12፥2 ማቴ 25፥31 ራእይ 14፥10፣20፥10 2ኛጴጥ. 2፥4

መ/ <u>መንግሥተ ሰማያት</u>

ጻድቃን ከትንሣኤ በኋላ የመጨረሻ ፍርድ ተፈርዶላቸው በተድላ በደስታ የሚኖሩባት ሰማያዊት ሀገር ናት::

ዳን. 12፥2 ማቴ.6፥10፣ 25፥34 ዮሐ.14፥2 ዕብ.11፥15
2ኛጴጥ.3፥10 ገላ. 4፥26 ራእይ 21፥1



www.ethiopianorthodox.org

## ፯ ስግደት፣ ክብርና አማላጅነት

ስግደት:-በፈጣሪና በፍጡር፣ በገዢና በተገዢ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጠብት የመገዛት ምልክት ነው:: ራስን ዝቅ አድርጐ በመንበርከክ በተሰበረ ልቡና ይቀርባል::
ስግደት ሁለት አይነት ነው::

ሀ/ የባሕርይ (የአምልኮት) ስግደት:- ይህ ስግደት የሚገባው ለፈጣሪ ብቻ ነው:: አምላክነቱን አምኖና ተረድቶ የሚፈጸም የአምልኮት ስግደት ሲሆን ለሌላ አይሰጥም::
ዘፀ.20፥1-6 መዝ.81፥9 መዝ.135፥15-18

ለ/ የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት:-ይህ ስግደት ደግሞ ለእግዚአብሔር ቅዱሳን፣ አገልጋዮቹ ፍጡራን የሚሰጥ ነው:: ይኸውም ለእግዚአብሔር ማደሪያ ለአመቤታችን፣ ለመላእክት፣ ለቅዱሳን ሰዎች ጌታ ተሰቅሎ ክቡር ደሙን ላፈሰሰበት ቅዱስ መስቀል የሚፈጸው ከአክብሮት ጋር የጸጋ ስግደት ነው::
ኢያ.5፥13 ኢሳ.49፥23 ዳን.2፥46 ራእይ.3፥8

ክብር:- ማለት ጌትነት፣ ታላቅነት፣ ከፍተኛነትን የሚገልጽ ነው:: ከሁሉም ነገር በላይ ክብር ያለው አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ነው::
ዘጸ.16፥7 መዝ.18፥1 1ኛነገ.8፥11 ኢሳ.6፥3
ስለዚህም ለእግዚአብሔር ልዩ ክብር መስጠት ይገባል:: ይሁዳ.25
እግዚአብሔር ክብሩን በሚፈቅደው ምሳሌ ይገልጻል እንጂ ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ሊያይ አይችልም::
ዘጸ.33፥17 ዮሐ.1፥14 ማቴ.17፥1 ዕብራ.1፥3
የጌታ ክብር በዳግም ምጽአትም ይገለጻል::
ማር.8፥38 ማቴ.24፥36
እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እሳተ መለኮትን በማህጸኗ የተሸከመች የአሸናፊው የእግዚአብሔር ወልድ ማደሪያ ናትና ክብርት እናት ነች::
ሉቃ.1፥30-37 ሉቃ. 1፥48



አገልጋዮቹ ቅዱሳን መላእክትና፣ ቅዱሳን ሰዎችም ክብር አላቸው:: ሉቃ. 2:9 1ኛቆሮ. 11፥7፥15፥41
ክብር ለሚገባቸው ቅዱሳን የአምላክ አገልጋዮች ክብር መስጠት ይገባል:: «ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ::» ሮሜ.13፥7

አማላጅነት:- ማማለድ ማለት አንዱ ለሌላው መጸለይ፣መለመን፣ ማስማር፣ የደረሰበትን ችግር ማስወገድ ማለት ነው:: በአማላጅነት ሥራ ውስጥ ሦስት ወገኖች አሉ:: ይኸውም:- የሚለመንለት ሰው፣የሚለምንለት ቅዱስ፣የሚለመነው አምላክ ነው::

ሀ/ አማላጅ:- ማማለድ ለፍጡራን ባሕርይ የሚስማማ የትህትና ሥራ ነው:: ቅዱሳን ሰዎችና ቅዱሳን መላእክት እንዲሁም ደግሞ የአማላጆች ሁሉ የበላይ የሆነች እመቤታችን ስለ ኃጥአን ወደ እግዚአብሔር ይማልዳሉ:: ሰዎች ዘላለማዊ ድኅነትን እንዲያገኙ እራሳቸውን እስከማሳለፍ ደርሰው እንኳን ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ::

ዘጸ.32፥32 ሮሜ.9፥3 1ኛዜና.21፥17

ለ/ የሚማለድለት:- ቅዱሳን አማላጆች ሆነው ወደ እግዚአብሔር ምልጃን የሚያቀርቡት ስለኃጥአን ሰዎች መዳን ነው:: የሚለመንለትም ሰው በቅዱሳን ምልጃ እንደሚድን ማመንና የንስሐ ልቡና ሊኖረው ይገባል:: ነገር ግን ኃጥኡ ሰው በሠራው ኃጢአት የማይጸጸትና የማይመለስ ከሆነ ግን እግዚአብሔርም የሚለመንለትን አይቀበልም::

1ኛሳሙ.16፥1 ኤር.7፥16-20 ኤር.15፥1

ሐ/ ተማላጅ:- የአማላጆችን ጸሎትና ልመና የሚቀበል ተቀብሎም ምሕረትን ይቅርታን የሚያድል ማለት ነው:: የጸሎት ሁሉ ተቀባይ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር የቅዱሳንን ልመና ተቀብሎ ፈቃዳቸውን ይፈጽማል::
ዘጸ.33፥17 መዝ.33፥15



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ መሠረት ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች፣እመቤታችን በተሰጣቸው የማማለድ ጸጋ ሰዎችን ከጭንቅ ያወጣሉ ከአምላካቸው ምሕረትን ይለምናሉ::

የአማላጅነት አስፈላጊነት:- 1/ ጸሎታችን በፍጥነት ወደ እግዚአብሔር እንዲደርስልን፣ 2/ እግዚአብሔር የቅዱሳኑን ጸሎት ሰምቶ ችግራችንን ስለሚያቃልልን ነው:: እግዚአብሔር ከኃጥእን ጸሎት ይልቅ የቅዱሳንን ጸሎት ይሰማል::

መዝ.33፥15 ምሳ.10፥24፤ 15፥29 ያዕ.5፥16
ራእይ.8፥3

- እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸውን ስግደት፣ ክብርና አማላጅነት ከዚህ በታች በተጻፉት ርዕሶች ላይ እናገኛቸዋለን::

## ፯.፭ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ ልጅነትን አጥቶ ሲኖር አምላክ በሰጠው ተስፋ መሰረት 5500 ዘመን ሲፈጸም ሊያድነው ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ:: እመቤታችን ለሰው ልጆች ሁሉ የመዳን ምክንያት ሆና የተሰጠች እናት ነች:: አስቀድሞም በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር የነበረች፣ በኋላም በንጽሕና በጥበበ እግዚአብሔር ተጠብቃ ስትኖር የዓለም መድኃኒት ለሆነው ጌታ ማደሪያ የሆነች፤ እሳተ መለኮትን በማኅፀንዋ የተሸከመች፣የመዳናችን ምሥጢር የተገለጸባት፤ ለእኛ ለክርስቲያኖች የጽድቅ መሰላል፣ ከመስቀል ስር የተገኘች የአደራ እናታችን ናት::

📖 የአምላክ እናት መሆኗ

ኢሳ.7፥14፤ 9፥6፤ 11፥1
ማቴ.1፥14፤ 2፥13
ሉቃ.1፥26፤ 2፥34-51
ገላ.4፥4

📖 አማላጅነቷና እናታችን መሆኗ

መዝ. 44፥9-16፤ 47፥12፤ 86፥2-5፤
131፥3-13
ዮሐ.2፥1-11፤ 19፥25-27



📖 ዘላለማዊ ድንግልናዋና ንጽህናዋ

መኃ. 6፥9፤ 4፥12
ሕዝ. 44፥1-2
ሉቃ. 1፥30-27
ራእይ. 12፥1

📖 ስግደት፣ ክብርና ምስጋና ይገባታል

ኢሳ. 1፥9፤ 49፥25፤ 60፥12
መዝ. 44፥17
ምሳሌ. 24፥15
ሚል. 5፥2
ሉቃ. 1፥28-42 ፤ 1፥48

ዮሴፍ የእመቤታችን እጮኛ ለምን ተባለ?

እጮኛ፣ እጮኝነት የሚለው ቃል ለብዙ ነገር ይሆናል:: ይኸውም
ሀ/ ከጋብቻ በፊት በወንድና በሴት መካከል የሚፈጸም ቃል ኪዳን መተጫጨት ይባላል::

ለ/ ሰዎች ለሹመት፣ ለሥራ ሲመረጡ የታጩ ይባላሉ::
ሐ/ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና በምዕመናን መካከል ያለው አንድነት እጮኝነት ይባላል:: 2ኛቆሮ.11፥2
መ/ ለቅድስና ለክብር መመረጥ መታጨት ይባላል:: 1ኛመቃብ.12፥35 ሆሴ.2፥21-22

ስለዚህም ዮሴፍ የእመቤታችን እጮኛ ተብሎ የተጠራው ጠባቂ፣ አገልጋይ ለማለት ነው::

ይኸውም ጌታን በምትወልድበት ጊዜ(ሉቃ.2፥4) ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ (ማቴ.2፥13) ጠባቂዋ ዮሴፍ አልተለያትም::

የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም:: ማቴ.1፥25

የበኵር ልጅ ሲል የመጀመሪያ(ዘጸ.13፥1)፣ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ብቻ (ዮሐ.3፥16፣ዕብ.1፥6፣ዮሐ.1፥18፣ቈላ.1፥17) ማለት ነው::

ስለዚህ ለቅድስት ድንግል ማርያም ክርስቶስ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድያ ልጇ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

እስከ የሚለው ቃል በሁለት መልክ ይፈታል።
፩ ፍጻሜ(መጨረሻ) የሌለው እስከ
ዘፍ.8÷7 1ኛሳሙ.15÷35 2ኛሳሙ.6÷23 ኢሳ.22÷14
ማቴ.28÷19 ሮሜ.5÷14 ራእይ.2÷10
፪ ፍጻሜ(መጨረሻ) ያለው እስከ ሲሆን
ዘፍ.38÷11 ማቴ.2÷14 ሉቃ.1÷20

ስለዚህ «ዮሴፍ እስከምትወልድ ድረስ አላወቃትም» የሚለው እስከ መጨረሻው በግብር አላወቃትም። ይህም ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው። ዘላለማዊት ድንግል ናት። ሕዝ.44÷1-3

## ወንድሞቹ የተባሉትስ ለምንድነው?

ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉም? እህቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም። ማቴ.13÷55 ማቴ.12÷46

ወንድሞች የተባሉት የዮሴፍ ልጆች እነ ዮሳ ከጌታ ጋር አብረው ስላደጉ ነው። በእስራኤል ልማድ የአንድ ሀገር ልጆች፣ የቅርብ ዘመዶች አብሮ አደግ ጓደኞች ሲሆኑ ወንድሞች ይባባሉ ነበር። ዘጸ.2÷11 ዘኍ. 20÷14፣ 2ኛ ሳሙ. 1÷26፣ 19÷11፣ ዕብ. 3÷2፣ አሞ. 1÷9 በአንድ ሃይማኖት የሚኖሩ ሰዎች ወንድሞች ይባባላሉ።
ሐዋ. 6÷3 ሮሜ. 1÷13 ፊልጵ.1÷12

አብርሃም ለሎጥ አጎቱ ሲሆን « እኛ ወንድማማቾች ሳለን ... » ብሎታል። ዘፍ. 13÷8 ወንድሙ ነው ማለት ነው? አይደለም። ስለዚህ እነ ያዕቆብና ይሁዳ የእመቤታችን ልጆች የጌታ ወንድሞች አይደሉም። ወንድሞች ቢሆኑ ኖሮ መልእክቶቻቸውን ሲጽፉልን የጌታ ባሪያ ከማለት ይልቅ ወንድም ብለው በጻፉ ነበር። ይሁዳ 1÷1፣ ያዕቆብ 1÷1 ታዲያ ወንድም ያሉት በጌታ ወንድምነት አፍረው ነው? አይደለም በእርግጥም ወንድም ስላልሆኑ ነው። እንዳንዶቹ ግን ጌታን « እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ነው። » ይሉ ነበር። ሉቃ. 3÷23 ወንድሞቹና የዮሴፍ ልጅ በማለታቸውም ተሰናክለውበታል። ማቴ.13÷56 ዛሬም ይህን የማሰናከያ ቃል የሚናገሩትን ልንቀበል አይገባም። ሉቃ. 8÷21፣ 11÷27



«አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም።» ዮሐ.2፡4

ይህ የጌታ አነጋገር የንቀትና የማዋረድ ንግግር ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን «እናትህንና አባትህን አክብር» ያለን የሕግ ባለቤት የሆነውን ጌታ እናቱን አዋረደ እንዴት ይባላል? ዘጸ.20፡12 ማር.7፡10 ነቢዩም «በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም» ሲል መስክሯል። ኢሳ.53፡9
ስለዚህ አንቺ ሴት ብሎ መጥራቱ የተለመደ አነጋገር ነው።
ማቴ.15፡28 ዮሐ.4፡21፤8፡10፤20፡13-15

ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ሲል ትርጉሙ ከአንቺ ጋር ምን ጸብ ክርክር አለኝ ሲል ነው። 2ኛሳሙ.16÷10 1ኛነገ.17፡18 ማቴ.8÷29 ማር.5÷7

ለምሳሌ፡ እንደ ሀገራችን አነጋገር አንድ ልጅ ሲላክ እንቢ ካለ ትርጉሙ አልሄድም ማለት ይሆናል። ነገር ግን በጦርነት ጊዜ አንድ ሰው 'እንቢ ለሀገሬ' ቢል ትርጉሙ እሄዳለሁ ይሆናል። ደግሞም አንድ ሰው ፍሬ ከርስኪ ቢባል የማይረባ የማይጠቅም ለማለት ነው። ነገር ግን በግዕዙ 'ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ' ሲል የማህፀንሽ ፍሬ ቡሩክ ነው ማለት ይሆናል።

በመሆኑም አንቺ ሴት ብሎ ንቀትን ሳይሆን የሚያሳየን ክብርንና መውደድን ነው። ጌታ የእመቤታችንን ልመና ሰምቶ ቢቃና ሰርግ ተአምራትን አድርጓል። ዛሬም በአማላጅነቷ ለሚታመኑ ሁሉ እንደወይን የሚጣፍጥ የፍቅር ሕይወት ታሰጣለች።

ጊዜዬ ገና አልደረሰም፡ ማለቱም በመስቀል ተሰቅዬ አዲሱን ወይን ደሜን የምሰጥበት ፡ ዘላለማዊ ሕይወት የምታገኙበትን ደሜን የምሰጣችሁ ጊዜው ገና ነው ሲል ነው። ነገር ግን ሰዓቱ(ጊዜው) በደረሰ ጊዜ ከአስራሁለቱ ሐዋርያት ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሥጋውን ደሙን ሰጠ። ሉቃ.22፡14 እግዚአብሔር ለሚሰራው ሥራ ሁሉ የሥራ ጊዜ አለው። መክ3፡1.መዝ 118፡126 ጊዜው ሲደርስ ተወለደ። (ገላ.4፡4) በመጨረሻም በዕለተ ዓርብ ለቤዛ ዓለም በመስቀል ተሰቅሎ በክቡር ደሙ ፈሳሽነት ዓለምን አዳነ። ኤፌ.2፡13. 1ኛዮሐ1፡7



www.ethiopianorthodox.org

## ፪.፱ ቅዱሳን መላእክት

በሥነፍጥረት መጀመሪያ ቀን በዕለተ እሁድ ለምስጋና የተፈጠሩ፡ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሆነው የሚላላኩ፡ የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ በረከት፣ ረድኤት ወደ ሰዎች የሚያስተላልፉ፣ የሰዎችን ልመና ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው::

| | | |
|---|---|---|
| መዝ.102:20 | ማቴ.10÷32 | |
| መዝ.103:4 | ማቴ.13÷30 | ሐዋ.10÷4 |
| ኢሳ.6:3 | ማቴ.÷31 | 1ኛቆሮ.14÷26 |
| | | ራእይ.4÷4 |

✞ ቅዱሳን መላእክት አፈጣጠራቸው እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ (ካለመኖር ወደ መኖር) እምቀ ነው፤ ነገር ግን በግብራቸው በእሳትና በነፋስ ተመስለዋል:: ይኸውም እሳት ረቂቅ ነው፤ መላእክትም ረቂቃን ናቸው፤ ነፋስ ፈጣን ነው፤ መላእክትም ለተልእኮ ይፋጠናሉና ነው:: (አክሲማሮስ)
መዝ.103÷4 ዕብ.1:14

✞ መላእክት በአፈጣጠራቸው ረቂቃን ሲሆኑ እንደ ሰው አይበሉም አይጠጡም:: ሉቃ.24:39

✞ መላእክት ጾታ የላቸውም:: አያገቡም አይጋቡም:: ማቴ.22÷30

✞ ቁጥራቸው አይታወቅም እልፍ አእላፋት ናቸው::
ሄኖክ. 10÷11 20÷39-46 ዕብ.12:23 ራእ.5:11

✞ ሊቃነ መላእክት ሰባት ናቸው::

1/ ቅዱስ ሚካኤል ፡- ዳን.10÷21 ሄኖክ.10÷12፤ 20÷32 ይሁዳ.9
2/ ቅዱስ ገብርኤል ፡- ዳን.8÷ ሄኖክ.10÷14 ሉቃ.1÷26
3/ ቅዱስ ራጉኤል ፡- ሄኖክ 6÷4
4/ ቅዱስ ዑራኤል ፡- ሄኖክ. 6÷2፤ 26÷35፤ 28÷13
5/ ቅዱስ ሩፋኤል ፡- ጦቢት.3÷17 ሄኖክ.3÷5 ፤ 6÷3 ፤ 10÷13
6/ ቅዱስ ፋኑኤል ፡- ሄኖክ 10÷15
7/ ቅዱስ ሳቁኤል

✞ መላእክት በነገድ መቶ ሲሆኑ ፤የመላእክት ከተማ ሦስት ናቸው:: እነርሱም ፡- 1/ ኢዮር 2/ ራማ 3/ ኤረር ናቸው::



✞ መላእክት ያለማቋረጥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ
መዝ.148÷2 ዳን.7:10 ሄኖክ.20:38 ራእይ.4:2

✞ ቅዱሳን መላእክት በሰዎች ልጆች ንስሐ መግባት ይደሰታሉ:: ሉቃ.15:10

✞ ለእያንዳንዱ ሰው የሚጠብቁት መላእክት አሉት:: ማቴ.18:10

✞ የቅዱሳንን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ:: ራእይ.8:3-4

* ቅዱሳን መላእክት በብሥራት (ሉቃ 1:26) በልደት (ሉቃ.2÷8) በገዳመ ቆሮንቶስ (ማቴ.4:11) በጌቴ ሴማኒ (ሉቃ.22:39) በትንሣኤ (ዮሐ.20:11) በዕርገት (ሐዋ.1:10) በአጠቃላይ በምሥጢረ ሥጋዌ የተለዩበት ጊዜ የለም:: በዳግም ምጽአትም ጊዜ አይለዩም:: ማቴ.25:31

ሀ/ ቅዱሳን መላእክት ሰውን ይጠብቃሉ፣ ያማልዳሉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ. 16:7 | 1ኛ ነገ. 19:5 | ማቴ.18:10 | ሄኖክ.6÷14 |
| ዘፍ.48:15 | 2ኛ ነገ. 6:15 | ሉቃ.1:26 | ሄኖክ10÷13 |
| ዘጸ. 23:20 | ዳን. 8:15-19 | ሉቃ 13:6 | ሄኖክ 8÷13 |
| መሳ. 6:11 | ዳን.3:17፥4፥13 | ሉቃ.15:7 | ጦቢት5÷21 |
| መዝ.33:7 | ዳን.10:21 | ዮሐ.20:11 | ጦቢት12÷15 |
| መዝ.88:6 | ዘካ. 1:12 | ሐዋ. 12:6 | ሲራክ2÷30 |
| መዝ.90:11 | | ራእይ12÷7 | |

ለ/ መላእክት የጸጋ ስግደትና ምስጋና ይገባቸዋል::

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ. 19:1-2 | ኢያሱ 5:13 | 1ኛዜና. 21÷1-7 |
| ዘኁ. 22:31 | መሳ. 13:20 | ዳን.8÷15 |

ሐ/ መላእክት አጥፊዎችን ሰዎች ለመቅጣት ይላካሉ::

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ. 19:10 | መሳ. 5÷23 | 2ኛ ሳሙ.24÷15 |
| 2ኛ ነገ.19:35 | መዝ. 34÷5 | ሐዋ.12÷23 |

«በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ:: እርሱም፡- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ::»

ራእይ 19÷10፤ ራእይ 22÷8



www.ethiopianorthodox.org

ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ ለመላእክት ስግደት አይገባም የሚሉ አሉ:: ነገር ግን ይህ የመልአኩ አነጋገር የትህትና አነጋገር ነው:: መልአኩ ቅዱስ ዮሐንስን እኔ እንደአንተ እንደ ወንድሞችህም የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ሲል የሐዋርያትን ክብር፡ የቅዱስ ዮሐንስንም በንጽህናውና በቅድስናው ታላቅ ክብር ያለው መሆኑን መግለጡ ነው:: ይኸውም ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በመቅደሱ ደጅ ተኝቶ የነበረውን በሽተኛ ካዳኑት በኋላ ሕዝቡ ትኩር ብሎ ሲመለከታቸው ይህንን በእኛ ኃይልና ሥልጣን እንዳደረግነው ለምን ታዩናላችሁ? እንዳሏቸው ያለ የትህትና ንግግር ነው:: ሐዋ. 3:1-12

ስለዚህም መልአኩ ቅዱስ ዮሐንስን አትስገድልኝ ሲለው የሐዋርያው ዮሐንስ ክብሩ እንደ መላእክት መሆኑን ለማመልከት ነው:: ዮሐንስም በመሳሳት ሳይገባው አልሰገደም:: ከአንድም ሁለት ጊዜ ሰግዷል:: ምሥጢረ መለኮትን፣ ራእየ ዮሐንስን ሌላም ብዙ ምሥጢር የጻፈ ሐዋርያ ለመላእክት ሳያውቅ ሰገደ ማለት አይቻልም ፤ ሌሎችም ለመላእክት የሰገዱ አባቶች ሁሉ አልተከለከሉምና:: ለመላእክት የሚቀርበው የጸጋ ስግደት ነው::

ኢያሱ 5÷13 | 1ኛ ዜና.21:16 | መሳ.13:20 | ዳን. 8:15

## ፳. ቅዱሳን ሰዎች

ስለ አምላካቸው ክብር፣ ስለ እውነተኛይቱ ሃይማኖት ሲሉ የምድር ሥጋውያን ነገሥታትን ፊት ሳይፈሩና ሳያፍሩ የመሰከሩ፣ ከጣዕመ ዓለም ተለይተው በየዋሻው ሲጸልዩ የኖሩ፣ ጸዋትወ መከራን የተቀበሉ፣ እስከ ሕይወት ፍጻሜ የተጋደሉ ቅዱሳን አባቶች ናቸው:: በዚህም የቅድስና ስራቸው የጸጋ አማልክት፣ የዓለም ብርሃናት ተብለዋል:: ከአምላክ ዘንድ የማማለድ ቃል ኪዳን ተገብቶላቸዋል::

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ. 7÷1 | ማቴ 5÷12 | መዝ. 33÷15፤ 66÷35 |
| ምሳ. 11÷23፣30 | 2ኛቆሮ 5÷19 | ዘሌ. 19÷2 |
| መዝ. 88÷3፣ 88÷34 | ምሳ. 15÷29 | ዕብ. 11÷33 |
| ሉቃ. 10÷16 | ኤር. 7÷16 | ራእይ 12÷11 |
| ሉቃ. 16÷19 | መዝ. 81÷6 | ዮሐ. 15÷7 |



ሀ/ የቅዱሳን ምልጃ በአጸደ ሥጋ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ. 18:17 | 1ኛሳሙ. 16:1 | ኢዮ.42:7 | ማቴ.8:5፡15:22 |
| ዘፍ.20:1-18 | 2ኛሳሙ.24:15-5 | መዝ.15:3 | ማር. 2:1-5 |
| ዘጸ. 8:8-25 | 1ኛ ነገ. 13:1-6 | መዝ.105:23 | ሉቃ. 9:35 |
| ዘጸ.32:11-14 | 1ኛነገ.17:17-24 | ኤር. 15:1 | ዮሐ. 4:46 |
| ዘኍ. 12:13 | 2ኛ ነገ. 4:18 | ኤር. 42:2-6 | |

ለ/ የቅዱሳን ምልጃ በአፀደ ነፍስ

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ. 9:5 | ምሳሌ. 10:7፡25 | ዮሐ. 11÷25 |
| 2ኛነገ. 13:20 | ጥበብ. 3:1፡4:16 | ፊልጵ. 1÷22 |
| ኢሳ. 56:4 | ማቴ. 10:41፡19:27 | 2ኛቆሮ. 9÷14 |
| መዝ. 102:17 | ሉቃ. 16:19-31 | ዕብ. 11÷4 |
| መዝ. 115:6 | 1ኛነገ. 11:11-13 | ራእይ. 6÷9-11 |

ሐ/ ለቅዱሳን የጸጋ ስግደት ይገባቸዋል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ. 33:1-7 | ዘጸ. 18:7 | 1ኛነገ.18:7 | ሐዋ.16÷25-30 |
| ዘፍ. 42:6 | 1ኛሳሙ.28:14 | 2ኛዜና. 29:29 | ፊልጵ. 2÷29 |
| ዘፍ. 49:8 | 2ኛሳሙ. 1:2 | ዳን. 2:46 | ራእይ. 3÷9 |

« ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላል » የሚለውን በተሳሳተ መልክ መተርጐም አግባብ አይደለም :: መክ. 9÷4-6 ትክክለኛውን ትርጉም ካለመረዳትና ካለማስተዋል የተነሳ ተጠራጣሪዎች ያልሞተ ውሻ የተባልን እኛ ስንሆን የሞተ አንበሳ የተባሉት ደግሞ ቅዱሳን ናቸውና እኛ ከቅዱሳን እንሻላለን የሚሉ አሉ:: በመሠረቱ እውነተኛ ክርስቲያን እራሱን ከፍ ከፍ አያደርግም፤ እኔ እበልጣለሁ አይልም:: ሉቃ. 18÷14

ያልሞተ ውሻ:- የተባሉ ግን በዚህ ዓለም ሲኖሩ የሰሩትን በደልና ኃጢአት እያሰቡ ክፉ ስራቸውን አውቀው በመሪር ዕንባ እየተጸጸቱ የሚያለቅሱትን፣ የእግዚአብሐርን ምሕረት ፈልገው



www.ethiopianorthodox.org

ሕይወታቸውን ለንስሐ የሚዘጋጁትን፣ ወደ አምላክ መተላለፋቸውን እያሰቡ የሚቀርቡትን ኃጢአተኞችን ነው። ይህም ማለት በንስሐ የሚመለሱትን እንጂ ያልተመለሱትን ሁሉን ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ከክፉ ስራቸው የተነሳ ኃጢአተኞች በውሻ ተመስለዋል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማቴ. 15፡26 | 2ኛጴጥ. 2፡22 | ፊልጵ3፡2 | ራእይ 22፡15 |
| መዝ. 21፡16 | ዘዳ. 23፥18 | | |

የሞተ አንበሳ፡- የተባሉት ደግሞ በክፉ ኃጢአት ሲኖሩ ቆይተው ንስሐ ሳይገቡ የሚሞቱትን ኃጢአተኞች ነው። እነዚህ ለፈቃደ ሥጋቸው የሚኖሩ ለዝሙት፣ ለርኩሰት፣ ለጣዖት አምልኮ፣ ለስካር፣ ለዘፈን፣ ለመናፍቅነት፣ ለቁጣ፣ ለመግደል፣ ለአድመኝነት በአጠቃላይ ለኃጢአት ስራ ሁሉ አንበሶች፣ ኃይለኞች የሆኑትን ነው። አገዛውና ተጸጽተው ንስሐ ሳይገቡ የግብር አባታቸውን የዲያብሎስን ፈቃድ የሚፈጽሙ ለሥጋ ፈቃድ የተገዙ በመሆናቸው በአንበሳ ተመስለዋል።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ. 30፥30 | ኤፌ. 5፥3-7 | 1ኛቆሮ.6፥9 |
| 1ኛጴጥ.5፥8 | ራእይ.21፥8 | ገላ.5፥19 |

1ኛ ቅዱሳን ሕያዋን ናቸው።

መዝ. 33፥22 ማቴ.22፥29 1ኛጴጥ. 4፥19 ዮሐ.11፥25

2ኛ ቅዱሳን መታሰቢያቸው ዘላለማዊ ነው። ከአምላክ ዘንድ የተሰጣቸው የምሕረት ቃል ኪዳን አይሻርም።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ.111፥6 | ምሳሌ.10፥7 | መዝ.33፥15 | ማቴ.10፥41 |
| መዝ.8፥3 | ኢሳ.42፥6 | ሕዝ.37፥26 | ማቴ. 5፥12 |
| መዝ. 110፥4 | ኤር.14፥24 | ሉቃ.1፥73⇔መዝ.104፥41እና 42 | |

3ኛ ቅዱሳን ዋጋቸው ሰማያዊ ነው።

ማቴ. 5፥12 ማቴ. 10፥32 መዝ. 33፥21-22



www.ethiopianorthodox.org

## ፱ መጽሐፍ ቅዱስ

ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ የጻፉት የተለየ የተቀደሰ መጽሐፍ ነው። የሰው ልጅ አዕምሮ ሊደርስበት የማይችለውን ረቂቅ ምሥጢር የሚያሳውቅ፣ የእግዚአብሔርን ጥበብና ደግነት የሚገልጽ፣ የሰውን ልጅ የሚመክር ምንም ስህተት የሌለበት ቃሉ የማይለወጥ፣ ዘላለማዊ፣ ቅዱስ የአምላክ ቃል ያለበት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምንጊዜም አዲስ ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘዳ.6፡2 | ኤር.23፡29 | ሉቃ.10፡39-42 | 2ኛጢሞ.3፡15 |
| መዝ.118፡130 | ሕዝ.3፡1 | ሉቃ.11፡28 | 2ኛጢሞ.1፡21 |
| ኤር.15፡16 | ማቴ.4፡4 | ሐዋ.19፡20 | ዕብ.4፡12 |

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት ሰማንያ አንድ ናቸው ብላ ታምናለች። ሐዋርያትም ሲጽፉ ከ81ዱ ክፍል ከሆኑት መጻሕፍት ጠቅሰው ጽፈዋል።

ማቴ. 27፡9 ⇔ ተረፈ ኤር7፡3 * ይሁዳ 14 ⇔ ሄኖክ 1፥9
ማቴ. 4፡7 ⇔ ዮዲት 8፡12 ራእይ 22፡2 ⇔ ሄኖክ 7፥16
ማቴ. 7፡12 ⇔ ጦቢት 4፡15 ራእይ 4፡8-9 ⇔ሄኖክ 9፥38-41

«እኔ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም ፤ ከእርሱም አታጉድሉም።» ሲል ምን ማለት ነው?

ዘዳ. 4፡2 ፡ ራእይ. 22፥18-19

እነዚህን ጥቅሶች ብንመረምራቸው የቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥር የሚወስኑ ሆነው አናገኛቸውም። ምክንያቱም በኦሪት ዘዳግም ላይ እና በዮሐንስ ራእይ ላይ ብቻ ከእግዚአብሔር ተገኝተው በተጻፉት ቃላት ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ እንደማይገባ የመለከተናልና ነው። ደግሞም ከሙሴ የኦሪት መጻሕፍት በኋላ ነቢያት በየጊዜው ብዙ መጻሕፍት ጽፈዋል። እነዚህንም መጻሕፍት ተቀብለው ሲሠሩባቸው ኖረዋል እንጂ ሙሴ አትቀበሉ ብሎናል ብለው ሌሎች ነቢያት የጻፏቸውን መጻሕፍት ሕዝቡ አንቀበልም አላሉም። ዘዳ.12፡32

## ፩ . ሃይማኖትና ምግባር

ሃይማኖት በዓይን የማትታይ፣ በእጅ የማትዳሰስ በጆሮ ብቻ ሰምቶ ይህ ሲደረግ እንደምን ይቻላል ሳይሉና ሳይጠራጠሩ የቤተክርስቲያን መምህራን ያስተማሩትን መጻሕፍት የተናገሩትን አምኖ በመቀበል በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል ብሎ በሀሊና የሚታመን ረቂቅ ምሥጢር ነው።

ሃይማኖት በጎ ምግባር ከሌላት የሞተች ናት። ሃይማኖትና ምግባር እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው በአንድ ሰው ላይ ካልተገኙ ለየራሳቸው ከሆኑ የማይጠቅሙ ምውታን ናቸው። ነገር ግን ሃይማኖት ከምግባር ጋር ቢተባበር ከጸብአ አጋንንት፣ ከሥጋዊ ጠላት፣ ከገሃነመ እሳት ያድናል።

ኤር. 6:16 ማቴ.5:16 ሉቃ.18:27 2ኛቆሮ. 13:5
መዝ.115:1 ማቴ.17÷20 ሮሜ.4:3 *ያዕ. 2:14-17
ዘፍ.18÷14 ዕብ. 11÷3 ማር.9:23

በአንዲት ሃይማኖት ጸንተን እንድንኖር:-

ኤፌ. 4÷5 ማቴ.7÷13-23 ማቴ.24:13
ሮሜ.16÷17 2ኛቆሮ.11÷13 2ኛጢሞ.3:4
ዕብ.3÷1 ዕብ.13÷7-9 1ኛዮሐ.4:1

### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መመሪያዎች

ሀ/ ዶግማ /እምነት/:- የማይለወጥ፣ የማይቀየር፣ ሊሻሻል የማይችል፣ የማይቀነስበት ፣ የማይጨመር በት ነው።
ዕብ. 13÷7

ምሳሌ:- መጽሐፍ ቅዱስ፣ 10ቱ ትዕዛዛት እና 5ቱ አዕማደ ምሥጢር

ለ/ ቀኖና /ሥርዓት/:- የክርስቲያኖች ሕይወት የሚጠበቅበት ውሳኔ ነው። ቀኖና በአባቶች ሲኖዶስ ሊለወጥ ሊሻሻል ይችላል።
1ኛ ቆሮ. 14÷14 ፤ ቆላ 2÷5 ፤ 2ኛ ተሰ. 3÷6



ምሳሌ: የጾም ሰዓት ለበሽተኞች፣ ለወለዱ: የቅዳሴና የበዓላት ሰዓትና ጊዜ

ሐ/ ትውፊት : ቅብብል ፣ ውርርስ ፣ ርክክብ ማለት ነው። መንፈሳዊ ትውፊት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ትክክለኛ ትውፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት አይጋጭም።

ዘፍ. 4:1 <> ዕብ 11:4 ዮሐ. 20:30 1ኛ ቆሮ.11÷34
ዘጸ. 7:11 ⇔ 2ጢሞ. 3:8 ዮሐ. 21:25 ፊልጵ. 4÷9
2ኛተሰ. 2:15

## ፲፩ ቤተክርስቲያን

የክርስቲያኖች ቤት፣ መሰብሰቢያ፣ መኖሪያ ማለት ነው። ቤተክርስቲያን የእምላክ ማደሪያ ስትሆን ታቦተ ሕጉ የሚገኝባት፣ ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባት፣ ልጅነት የሚሰጥባት የአምልኮ መገለጫና የጸሎት ቤት ናት። በክርስቶስ ደም የተመሠረተች የእውነት ዓምድና መሠረት የጸጋ ግምጃ ቤት ናት።

✣ የቤተክርስቲያን ትርጉም:-

1. ሕንጻ ቤተክርስቲያን :-

መዝ.121:1 ባሮክ 3÷22 1ኛ ነገ. 8÷10 ነህ. 6÷10

2. የክርስቲያኖች ማኅበር አንድነት:-

ማቴ.18÷17፤18÷20 ሐዋ.5÷11፤9÷31፤12÷1
1ኛቆሮ.11÷16፤16÷19 1ኛጴጥ.5÷13

3. እያንዳንዱ ክርስቲያን:-

1ኛ ቆሮ. 3÷9 2ኛ ቆሮ. 6÷16



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

✝ ቤተክርስቲያን በውስጥ አሰራሩ በሦስት/3/ ክፍል ይከፈላል፡፡
ይኸውም፡-

1. መቅደስ
2. ቅድስት
3. ቅኔ ማኅሌት

✝ ቤተመቅደስ የእግዚአብሔር ማደሪያው ቅድስት ሥፍራ ናትና በመቅደስ ተገኝቶ ለእግዚአብሔር መስገድ፣አምልኮትን መፈጸም ፣ ጸሎትን ማድረስ የሚገባ ነው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘጸ. 28÷10-28 | መዝ. 5÷7 | መዝ. 68÷9 | ኢሳ. 56፡7 |
| ዘጸ. 3÷5 | መዝ. 26÷4 | መዝ. 121÷1 | ሐዋ. 7፡33 |
| ዘጸ. 33÷7-10 | መዝ. 28÷2 | መዝ. 131÷7 | ዘፍ. 28÷17 |
| ዘሌ. 26÷2 | መዝ. 83÷10 | መዝ.137÷2 | መዝ. 117፡20 |
| ኢያሱ. 5÷15 | መዝ. 95÷6 | ዕንባ. 2÷20 | |

✝ ቤተመቅደስ እንዲሰራለት ያዘዘው እግዚአብሔር ነው፡፡ ማደሪያው ነውና፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘጸ. 25÷2-8 | 1ኛነገ. 8÷1-66 | 1ኛ.22÷10 | ኢሳ. 6÷1 |
| ዘሌ. 26÷11 | 1ኛ ነገ. 9÷3 | 2ኛ ዜና. 3÷1 | ኢሳ.66÷1 |
| | | ሐዋ.7÷48/ሐጌ.1÷6/ | |

✝ ቤተመቅደስ ሰማያዊ ምሥጢር የሚገለጥባት ናትና በሐዲስ ኪዳን አልተሻረችም፡፡ አገልግሎት ይፈጸምባታል፡፡

| | |
|---|---|
| ማቴ. 5÷17 | ሐዋ. 3÷1 |
| ማቴ. 21÷12 | ሐዋ. 22÷17 |
| ማቴ.22÷40 | 2ኛተሰ.2÷1-3 |
| ማቴ. 27÷51 | 1ኛጢሞ. 3÷15 |
| ሉቃ. 2÷4-9 | *ራእይ. 11÷19 |
| ሉቃ. 24÷53 | ራእይ. 15÷5 |
| | ራእይ. 21÷3 |



## ፲፱ ታቦት

ታቦት ማለት ማደሪያ ሲሆን ማደሪያነቱም ለጽላተ ኪዳኑ ነው። ታቦት የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ዙፋን ነው። በአዲስ ኪዳን የጌታ ስጋውና ደሙ ይፈተትበታል። ታቦት እንዲሠራ ያዘዘው እግዚአብሔር ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘጸ 25፥10 | ዘጸ 32፥15 | ዘኁ 1፥89 | 1ኛ ሳሙ 6፥19 |
| ዘጸ 37፥1 | ዘጸ 34፥1-5 | ዘዳ 10 ፥1-5 | 2ኛ ሳሙ 6፥11 |

✝ ታቦትን መንካት መሸከም የሚችሉት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው አባቶች ካህናት ብቻ ናቸው። ክህነት የሌለው ሰው ቢነካው ግን ይቀሰፋል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘሌ. 16፥2 | ኢያ 3፥5-17 | 1ኛሳሙ 5፥9-12 | 1ኛነገ 8፥4 |
| ኢያ 6፥12 | 2ኛ ሳሙ 6፥6-8 | 1ኛ ዜና 13፥9-11 | 1ኛዜና 15፥2 |

✝ ለታቦት የሚገባ ክብርና ስግደት፦

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘጸ 33፥10 | ኢያ 7፥6 | 1ኛሳሙ 5፥1-5 | 2ኛቆሮ 6፥16 |

✝ ታቦተ ሕጉን ሕዝቡ በርቀት ሊከተል የሚገባው መሆኑ።

ኢያሱ 3፥4



www.ethiopianorthodox.org

የቃል ኪዳኑን ታቦት በዕልልታና በሆሣዕና ማጀብ የሚገባ መሆኑ፦

1ኛሳሙ 4፥5   2ኛሳሙ 6፥12-15   መዝ 134፥2   ዘጸ15፥1

✞ በአዲስ ኪዳን የክብር ዙፋን የሆነው ታቦት ይከበራል፣ አልተሻረም፣ አልቀረም በሰማይ መቅደስ እንኳን አለ።

ማቴ 5፥17-19   2ኛቆሮ 6፥14-16   ዕብ 9፥1-22

ራእይ 11፥19   ኢሳ 45፥23 ↔ ፊልጵ 2፥10

## ✞ *በታቦት ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው፦*

➡ ኤር 10፥2-5 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የአሕዛብን መንገድ አትማሩ፣..... የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና፣ ዛፍ ከዱር ይቆረጣል፣ በሠራተኛም እጅ በመጥረቢያ ይሠራል። በብርና በወርቅ ያስጌጡታል፣ እንዳይናወጥም በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል። እንደ ተቀረጸ አምድ ናቸው እነርሱም አይናገሩም መራመድም አይቻላቸውምና ይሸከሟቸዋል፣ ደግሞም መልካም ይሠሩ ዘንድ አይችሉምና አትፍሩዋቸው።



ልብ እንበል፡ ከነፋዎች ጥርጥር እንጠበቅ ኤፌ5፥16 ይህን የአሕዛብ ልማድ የተባለ ጣዖትን ለታቦት እንደተነገረ አድርገው የሚናገሩ ጠማማዎች አሉ። "ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ።"ሐዋ 2፥40

ይህ ከላይ ያየነው ቃል በአንፃሩ ተጠርበው በችንካር ተቸንክረው ለሚመለኩ ጣዖታት የተነገረ ነው። እነዚህ የአሕዛብ ጣዖታት ከንቱ ናቸው፣ መልካም ሊሠሩ አይችሉምና ይላል። ገቅ እያልን ስናነብ የጣኦትን ሐሰት የእግዚአብሔርን እውነት ያናግርል እንጂ የታቦትን ክብር አይቀንስም። የታቦትን ክብርማ ከላይ ተመልክተናል።
ኤር 10፥6-10፣ ኢሳ 46፥5-7፣ ዘጸ 20፥4፣ 32፥8፣ ሮሜ 1፥25

➡ ኤር 3፥16 " ከእንግዲህ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው አይጠሩም፣ ልብ አያደርጉትም አያስቡትም፣ አይሹትም።"

ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉ እስራኤል ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበትን፣ ጠላቶቻቸውን ድል የሚያደርጉበትን በረከት የሚያገኙበትን፣ የቃልኪዳኑን ታቦት ትተው ወደ ጣዖት በመመለሳቸው ፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር መጥቶ ኢየሩሳሌምን እንደሚወር ፣ ቤተመቅደሱን እንደሚያፈርስ ፣ ንዋያተ ቅዱሳቱም እንደሚዘረፉ ፣ 70 ዘመን እንደሚማረኩ ነቢዩ የተናገረው ትንቢት ስለሆን ቃሉም



www.ethiopianorthodox.org

ተፈጽሞባቸዋል። (ኢር 25፥1-11) በባዕድ አገር በባቢሎን ምርኮ ሳሉ የቃል ኪዳኑን የእግዚአብሔር ታቦት አላገኙምና የታቦቱን ሥርዓት መፈጸም አልቻሉም ማለት ነው እንጂ ታቦት ብላችሁ አትጥሩ ማለት አይደለም። እስራኤል ከምርኮ በኋላ ወደ እግዚአብሔር በአንድነት አልቅሰዋል።(ኢር 50፥1-5)

→ ኤር 31፥31 ፤ 2ኛ ቆሮ 3፥2 ፤ ዕብ 8፥8

"እነሆ ከእሥራኤል ጋር አዲስ ቃል ኪዳን አደርጋለሁ በእነሱም ሕጉን በልቡናቸው እኖራለሁ። ሕጌንም በልቡናቸው እጽፋለሁ።"

የእኛ የክርስቲያኖች ልቡና የክርስቶስ ማደሪያ ቤተመቅደስ ቢሆንም (1ኛ ቆሮ 3፥16) የቃል ኪዳኑ ታቦት አያስፈልግም አልተባለም። እንዲህ ከሆነማ ሕጌን በልባቸው እኖራለሁ ተብሏልና ታቦት አያስፈልግም ካልን ፤ አሥርቱ ትዕዛዛትም በልባችን ብቻ እንጂ በሌላ መጻፍ የለባቸውም ልንል ነው።

ነገር ግን በሐዲስ ኪዳን ታቦት ያስፈለገበት ስለ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ነው። ይኸውም በብሉይ ታቦት ክብሩ ይገለጥበት ፤ ድምፁን ያሰማበት እንደነበረ ፤ በሐዲስ ኪዳንም ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት የክብር ዙፋን ፤ እንዲሆን ነው።



## *ታቦት መሰረቁና መሸጡ ኃይል ባይኖረው ነው ለሚሉት፡*

እግዚአብሔር አምላክ ቸርነቱ ብዙ ነው። ሮሜ 2፥4 እግዚአብሔር ምህረቱ የበዛ ነውና ከቁጣ የዘገየ ነው። መዝ 145፥8 ነገር ግን ከቸርነቱና ከትዕግስቱ በስተጀርባ ደግሞ የበደሉትንና የማይመለሱትን ይቀጣል። መዝ 93፥9-11 ስለዚህ አምላክ ዝም ማለቱ ስለቸርነቱ ብዛት ነው እንጂ ታቦቱ ኃይል ሳይኖረው ቀርቶ አይደለም። እንኳን ታቦት የዓለም ፈጣሪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ በሰላሳ ብር ተሸጧል። (ማቴ 26፥47-56 ፤ 27፥3-10) ታዲያ ጌታ የተያዘው ኃይል ሳይኖረው ቀርቶ ነው? አይደለም ኃይሉንማ ፤ አምላክነቱንማ ሰይፍና ጎመድ ይዘው ሊይዙት ለመጡት ወደኋላቸው እንዲወድቁ አድርጎ አሳይቷቸው ነው የተያዘላቸው። ዮሐ 18፥6

በተለይ ደግሞ "ለሁሉም ጊዜ አለው" እንዲል (መክ 3፥1 ፤ መዝ 118፥126) እግዚአብሔር ጊዜው ሲደርስ ሁሉንም ነገር ይገልጠዋል። ለምሳሌ ከ133 ዓመት በፊት ወደ እንግሊዝ ስኮትላንድ ተወስዶ የነበረው የመቅደላው ታቦት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ አድርጓል። ይህ ጥበበ እግዚአብሔር ነው።



www.ethiopianorthodox.org

***ለሙሴ ከተሰጡት ሁለት ጽላት ውጭ ይህ ሁሉ እንዴት በዛ ለሚሉት፦***

1ኛ/ ሙሴ ጽላት ሲሰበርበት እንደገና እንደፊተኞቹ ዓይነት ሥራ ሲል እግዚአብሔር መፍቀዱ ሰው ጽላትን የመቅረጽ(የመስራት) ፈቃድ እንደተሰጠው ያሳያል። ዘጸ 34፥1-27 ፤ ዘዳ 10፥1

2ኛ/ በዓለም ለሚገኙ ክርስቲያኖች አንድ ወይም ሁለት ጽላት ይኑር ካልን ፤ በዓለም ላሉ ክርስቲያኖች በሙሉ በነቢያት በሐዋርያት እጅ የተጻፈው አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይበቃል ማለታችን ነው። ምክንያቱም እንደ ጽላቱ መጽሐፍ ቅዱስም መሰራጨት መባዛት እያስፈልግም እንደ ማለት ነውና። በተጨማሪም አሥርቱ ትእዛዛትም ተባዝቶ መጻፍ የለባቸውም ልንል ነው። እንደገና በዓለም ላይ የመጀመሪያይቱ ቤተመቅደስ እንጂ ሌላ አይታነጽ እንደማለት ነው፤ ታዲያ ይህ ከሆነ ደግሞ እምልኮታችንን መፈጸም በፈለግን ቁጥር አንዱን መቅደስ ፍለጋ አገር አቋርጠን መሄድ ሲገባን ነው? ይህ ሳይሆን በመላው ዓለም ክርስትና እየተስፋፋ ሲሄድ ቤተመቅደስ በየስፍራው ሁሉ ሊታነጽ ታቦት ሊቀረጽ የግድ ነው። ዮሐ 4፥21 ፤ ሚል 1፥11



ታቦት በእምስቱ ደምስራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት (Oriental Churches) ዘንድ የተለመደ ሕግ ነው።

## ፲፫ ***መስቀል***

ለሰው ልጆች ሁሉ የመዳን ምክንያት የተፈጸመበት፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ሥጋ የተቆረሰበት ቅዱስ ደም የፈሰሰበት፣ የዘላለም ሕይወት ያገኘንበት፣ ሞትና ዲያብሎስ ድል የተደረጉበት፣ እኛም ጠላታችን ዲያብሎስን ድል የምንነሳበት ፣ የጸብ ግድግዳ የፈረሰበት ፣ ለዓለም ሰላም የተሰጠበት የነፃነት አርማ ፣ የድኅነት መገኛ ለእኛ ለምናምንበት ኦርቶዶክሳውያን ኃይላችን፣ የሰላማችን ምልክት ነው ስለዚህ ክብር እንሰጠዋለን፣ እንሰግድለታለን፣ እንሳለመዋለን ፣ እንባረክበታለን።

✞ መስቀል ኃይል ነው። 1ኛ ቆሮ 1፥8 ኤፌ 2፥16 ቆላ 1፥19 ፤ 2፥14

✞ መስቀል መመኪያ ነው። 1ኛ ቆሮ 2፥2 ገላ 6፥14

✞ የመዳናችን ምልክት ነው። መዝ 59፥4 ኢሳ 49፥22 1ኛጴጥ 2፥24 ዘኁ 21፥9 ↔ ዮሐ 3፥14

✞ ሐዋርያት ስለ መስቀሉ ሰብከዋል። 1ኛቆሮ 1፥23 ፤ 2፥8



www.ethiopianorthodox.org

✝ ለጌታ መስቀል ክብር መስጠት መስገድ ይገባል።

መዝ 131፥7 ፤ 98፥5 መኃ 1፥ 2

ዘፍ 48፥13 ዕብ 11፥21

✝ የመስቀሉ ጠላቶች መጨረሻቸው ጥፋት ነው።

ፊልጵ 3፥18 ፤ ገላ 3፥1 ፤ 2ኛ ቆሮ 11፥13

## ፲፬ ማዕተብ

ማዕተብ ማለት ምልክት ማለት ነው። ለተጠመቁ ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስትና ሃይማኖት መታወቂያ ፣ ምልክት ፣ አርማ ነው።

✝ በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ማተብ የተጀመረው በሃይማኖቱ አበው በድርሳነ ያዕቆብ መረጃ መሠረት ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ በነበረው ያዕቆብ ዘእልበረዲ ነው። መስቀል በክር በአንገት ላይ ማሰር የክርስቲያኖች መለያ ሆኖ አንገትን ለሰይፍ ፣ ለመከራ እሰጣለሁ ማለት ነው።

ዘዳ 6፥8 ምሳ 6፥20 ማቴ 10፥38 ማር 10፥2 ሉቃ 14፥27



→ በመስቀል ላይ የሚነሡ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፦

መስቀል ጌታችን የሞተበት ስለሆነ አንሳለምም ፣ አንሰግድም የሚሉት ፕሮቴስታንቶች ናቸው።

✝ በመስቀል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥልን ገድሏል። ጠላታችን ዲያብሎስ ድል ተደርጎበታል ተሸንፎበታል። ኤፌ 2፥14-16፤ ቆላ 2፥14፤ 1ኛ ቆሮ 15፥55 በጌታ ሞት እኛ ሕይወትን አግኝተናል። ኢሳ 53፥5 ፤ ዮሐ 6፥54 መስቀል ጌታን አልገደለውም ሞትንና ዲያብሎስን እንጂ። ስለዚህ መስቀል በዕለተ ዓርብ ከ6-9 ሰዓት የጌታ እግሮች የቆመበት ፤ እጅና እግሩ የተቸነከረበት ፤ ጀርባውን ያስደገፈበት በመሆኑ እንሰግድለታለን። መዝ 131፥7። መስቀል የጌታ ስጋ የተቆረሰበት ደሙ የፈሰሰበት ፤ ደኅንነትን ያገኘንበት ፣ ጠላታችን የተሸነፈበት በመሆኑ እንሳለመዋለን። የጸጋ ስግደት እንሰግድለታለን ክብር እንሰጠዋለን።

ሮሜ 13፥7 ፤ መዝ 98፥5

መስቀልን ዲያብሎስ አይወድም ድል የተደረገበት ነውና ዛሬም የዲያብሎስን ፈቃድ የሚፈጽሙ የግብር ልጆቹ የመስቀልን ኃይል ይክዳሉ ፣ የመስቀሉ ጠላቶች ሆነው



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ይመላለሳሉ። ቤተ ጸሎት ከሚሉት በላይ መስቀልን ይስትላሉ ኃይሉን ግን ይክዳሉ።
2ኛ ጢሞ 3፥5 ፊልጵ 3፥18

➡ ጌታችን ቀጥ ባለ እንጨት ተሰቀለ የሚሉት ጂሆቫ ዊትነሶች ናቸው።

✞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የተመሳቀለ መስቀል እንጂ አንድ ወጥ በሆነ ቀጥ ባለ እንጨት አይደለም። ቅ/ ጴጥሮስ "ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ" 1ኛ ጴጥ 2፥24 ማለቱ ጌታ የተሰቀለበት እንጨት መሆኑን ለይቶ ለመናገር ነው እንጂ ጌታ የተሰቀለው እንደ ተ ፊደል በተመሳቀለ እንጨት ላይ ነው። መስቀል ማለት ራሱ የተመሳቀለ ማለት ነው።

ማቴ 10፥38 ማቴ 27፥32 ፣ ማር 15፥29
ዮሐ 19፥17 ፣ ቈላ 1፥20 ፣ ኤፌ 2፥14

## ፲፫ ሥዕል

ቅዱሳት ሥዕላት ከልዑል አምላካችን ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዝነው ሲሆን፣ በስዕል የመላዕክትን ፣ የሰማዕታትን ፣ የቅዱሳን አባቶቻችንን ፍቅር የምንገልጥበት ፣ ያለፉ አባቶቻችን የፈጸሙትን የሰማዕትነት ተጋድሎ አይተን ጽናትን የምንማርበት ነው እንጂ ሌሎች



እንደሚሉት ቤተክርስቲያን ስዕልን አታመልክም። የስዕሉ ባለቤቶችን ግን እናከብራቸዋለን። ስለዚህ ስዕል የስዕሉን ባለቤት ክብርና ፍቅር መግለጫ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ 25፥18-20 | 1ኛ ነገ 6፥23-26 | ሄኖክ 14፥11 |
| ዘጸ 35፥19 | 1ኛ ነገ 7፥28 | ገላ 3፥1-2 |
| ዘጸ 37፥7 | ሕዝ 4፥1፤9፥3 | |
| ዘኍ 7፥89፤21፥8 | ሕዝ 10፥1፤41፥16-20 | |

## ፲፬ ዕጣን

ለልዑል እግዚአብሔር የሚቀርብ በቤተመቅደስ ውስጥ የሚታጠን ጣፋጭ ሽታ ፣ መልካም መዓዛ ያለው ፣ የሰዎችን መንፈስ የሚማርክ ንጹህ መሥዋዕት ነው። ዕጣን የሰዎችን ጸሎት ማሳረጊያ ስማያዊ ሥርዓት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ 30፥7 እና 24 | 1ኛ ነገ 9፥25 | ሚልክ 1፥11 |
| ዘጸ 37፥29 | መዝ 140፥2 | ፊልጵ 4፥18 |
| ዘጸ 40፥27 | መኃ 3፥6 | ዕብ 9፥4 |
| ዘኍ 16፥46 | ኩፋሌ 5፥24 | ራእይ 5፥8፤8፥3 |

✞ በዕጣን አገልግሎት ጊዜ ከዕጣኑ የሚወጣው ጭስ (ደመና) በጻግም ምጽአት (ማቴ 24፥30 ፣ መዝ 96፥2) በእመቤታችን (1ኛ ነገ 18፥44 ፣ ኢሳ 19፥1)



www.ethiopianorthodox.org

የዕጣኑ በእሳት መጨመር በቅዱሳን ሰማዕታት የተጋድሎ ሕይወት (ሮሜ 12፥11 ኤፌ 5፥2) ይመሰላል። ዕጣኑ በፍህሙ ተቃጥሎ ብቻ እንደማይቀር ወደሰማይ እንደሚወጣ ሁሉ የቅዱሳንም ጸሎት በከንቱ አይቀርም። ከሰማያዊው እግዚአብሔር ጋር ያገናኛል። መዝ 33፥15

✞ ዕጣን ማጠን የሚችሉ አገልጋይ ካህናት ብቻ ናቸው። ከዚህ ውጭ በትዕቢት ፣ በግዴለሽነት ፣ በቸልተኝነት ቢቀርብ ግን ያስቀጣል።

| | | |
|---|---|---|
| ዘሌ 10፥1-3 | 1ኛ ሳሙ 2፥28 | ኢሳ 1፥13 ፣ 66፥3 |
| ዘኁ 16፥5-35 | 2ኛ ዜና 26፥16-21 | ሉቃ 1፥8 |

✞ ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ሊቀርብ የሚገባውን ዕጣን ለሌላ ማዋል አይገባም። ዘጸ 30፥34-38 ፣ ዘጸ 31፥11

✞ ***በዕጣን ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፡-***

ኢሳ 1፥13 "........ምናምንቴውን ቁርባን ጨምራችሁ አታምጡ ፤ ዕጣን በእኔ ዘንድ አስጸያፊ ነው።"

ኢሳ 66፥3-4........ዕጣንን የሚያጥን ጣዖትን እንደሚባርክ ነው። እነዚህ የገዛ መንገዳቸውን መረጡ ፥ ነፍሳቸውም በርኩሰታቸው ደስ ይላታል።" የሚሉ ጥቅሶችን አንስተው ዕጣን በቤተመቅደስ አያስፈልግም የሚሉ አሉ።



በውኑ ይህ ቃል ዕጣን አያስፈልግም ለማለት የተፃፈ ነው? መልሱ አይደለም ነው።

በመቅደስ ካህናት የሚያጥኑትን የመልካም ሽቱ ዕጣን ለመንቀፍ ሳይሆን፤ በነቢዩ ኢሳያስ ዘመን የነበሩ ሕዝበ እስራኤል እጆቻቸው በግፍ የተሞሉ ፣ እግሮቻቸው ወደ ቤተ ጣዖት የሚሮጡ ፣ ዓይኖቻቸው ክፉውን ነገር የሚመለከቱ ፣ በአንደበታቸው ክፋትንና ተንኮልን የሚያወሩ ስለነበር እግዚአብሔር እንዲህ በትዕቢት፤ በኃጢአት ፣ በርኩሰት ፣ በተንኮል ፣ በግዴለሽነት የሚቀርበውን የበደል መስዋዕት እንደ ቃየል መሥዋዕት ያለ ነውና ዕጣናችሁን አልቀበልም ሲል መስዋዕት አቅራቢዎቹን ሰዎች ነቀፋቸው እንጂ መስዋእቱን፤ ዕጣንን መንቀፉ አይደለም ። ስለዚህ እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነውና ንጹሕ መስዋዕት በንጽህና እንዲቀርብለት ይፈልጋል። ኢሳ 1፥10-17 ፣ ዘሌ 19፥2 ፥ 1ኛ ጴጥ 1፥15 ፣ ማቴ 5፥23-24 ዘጻ 33፥10 ሚል 1፥11

## ***፲፯ መብራት***

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ውስጥ በቅዳሴ ፣ በማኅሌት በሰዓታት አገልግሎት ጊዜ ፣ በሰዐላት ፊት ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲነበቡ መብራት (ጧፍ ፣ ሻማ) የሚበራው ከመጽሐፍቅዱስ የተገኘ በመሆኑና ሰማያዊ



www.ethiopianorthodox.org

ምሳሌ ስላለው ነው። ብርሃኑ ብርሃናውያን (ሰማያውያን) ቅዱሳን መላእክት ከእኛ ጋር ለመሆናቸው ምሳሌ ነው። ብርሃን ጨለማን እንደሚያስወግድልን ሁሉ እኛም ጭንቀትን ፣ መከራን ፣ ፍርሃትን እናስወግድበታለን። ሻማው (ጧፉ) ሲነድ እየቀለጠ እንደሆነ ሁሉ ሰማዕታትም ስለ እምነታቸው ክብር ሲሉ መሰዋታቸውን፣ የወንጌል ፋና የደህንነት ብርሃን ለመሆናቸው ምሳሌ ነው።

ማቴ 5፥15 ሉቃ 12፥36 ዮሐ 8፥12 ራእይ 1፥20
ማቴ 13፥43 ዮሐ 1፥5 2ኛ ቆሮ 11፥14
ማቴ 25፥1 ዮሐ 5፥35 ዕብ 11፥35-40

✞ ልዑል እግዚአብሔር በደብተራ ኦሪት ውስጥ ዘወትር መብራት እንዲበራ አዝዞ ነበር።

ዘጸ 25፥31 ፣ 37፥17 ፣ 2ኛ ዜና 4፥20 ፣ 29፥7 ሲራክ 26፥21

✞ በዘመነ ሐዋርያትም ቢሆን ከፍ ብሎ በሠገነት ላይ የሚበራ መብራት ነበር። ሐዋ 20፥8 እኛም ይህን ትውፊት የተቀበልነው ከአባቶቻችን ቅዱሳን ሐዋርያት ነው።

## ፲፰ ጃንጥላ

በቤተክርስቲያን በቅዳሴ ጊዜ ፣ ወንጌል ሲነበብ ፣ ታቦተ ሕግ ሲወጣ ፣ በልዩ ልዩ አገልግሎት ጊዜ ጃንጥላ ወጥቶ ይዘረጋል።



ከተለያዩ ከሚያምሩና ከሚያብረቀርቁ ጨርቅ የሚሰራው ጃንጥላ የመውጣቱና የመጋረዱ ምሳሌ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ጽላተ ኪዳኑን ሲቀበል በደብረ ሲና የጋረደው ደመና ምሳሌ ነው።

ዘጸ 24፥15 ፣ ዘኁ 9፥17 ፣ 10፥34 ፣ ማቴ 17፥2 ፣ ሉቃ 9፥34

## ፲፱ ጾም

ጾም የሰው ልጅ ለአምላኩ እየታዘዘ የምኞት ፍትወትን (የሥጋ ፈቃድን) ለማድከም በሕግ በተደነገጉ የጾም ወራት ለተወሰነ ሰዓት ከእህል ፣ ከመጠጥ መከልከል ፣ መራቅ ፣ መተው ማለት ነው።

ጾም መንፈሳዊ ኃይልና ብርታት ይገኝበታል። ጾም ኃጢአትን ለማስተስረይ ፣ የነፍስ ንስቄልናን ለማጥፋት ይጠቅማል። ጾም ጸብአ አጋንንትን ያርቃል። ትሕትናን ይሰጣል። ሥጋ ለነፍስ እንድትገዛ ያደርጋል።

ዘጸ 9፥9 ዕዝ 8፥21 ፣ 10፥6 ማቴ4፥1-11፣9፥13፣17፥21
እስ 4፥3 መዝ 34፥13፣108፥24 ኢዩኤል 2፥12-15
ነህ 1፥4፥9፥1 ዳን 9፥2 ፣ 10፥2 ሐዋ10፥3-10፣ 13፥2
ሉቃ 2፥37 ዘካ 8፥18፣9፥19 ዮናስ 3፥8፣ኤር36፥9
2ኛ ነገ 2፥11 2ኛ ሳሙ 12፥16 ራእይ 5፥11
2ኛ ቆሮ 11፥27 ፍትሐ ነገስት አንቀጽ 15



www.ethiopianorthodox.org

## ሰባቱ የሕግ አጽዋማትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃቸው

1/ <u>ዐቢይ ጾም፦</u> የሁምሳ አምስት ቀናት ጾም ነው። ዐቢይ ማለት ታላቅ ማለት ነው በቀናቱም ከሁሉም አጽዋማት ሁሉ በላይ ነው። ይህን ጾም ጌታ የጾመው በመሆኑ እኛም እንጾመዋለን። ማቴ 4፥2 ሉቃ 4፥1 ጌታ በዚህ ጾም አርእስተ ኃጣውእ (ሦስት ታላላቅ ኃጢአቶችን ድል አድርጐባቸዋል። እነርሱም ስስት ፣ ትዕቢት ፣ ፍቅረ ንዋይ ናቸው።

ዐቢይ ጾም ጌታ ከጾመው 40 ቀን በተጨማሪ የሚጾመው የመጀመሪያ ሳምንት ዘወረደ (ጾመ ሀርቃል) ፣ ሲባል የመጨረሻው ሳምንት ደግሞ ሰሙነ ሕማማት ይባላል።

የዐቢይ ጾም 55 ቀናት የየሳምንቱ ስያሜ አላቸው። እነዚህም፦

1/ <u>ዘወረደ</u> ⇨ እምላክ ከሰማየ ሰማይ መውረዱን ፣ ከድንግል ማርያም መወለዱን የሚያስታውስ ነው።

2/ <u>ቅድስት</u> ⇨ የሰንበትን ቅድስና ጌታ በምኩራብ ያስተማረበት ያስረዳበት ነው። ማቴ 12፥8



3/ <u>ምኩራብ</u> ⇨ ጌታ በየምኩራብ እየገባ ማስተማሩን ፥ ድውያንን መፈወሱ የሚያሳስበን ነው። ማቴ 9፥35

4/ <u>መፃጉዕ</u> ⇨ ጌታ ሰላሳ ስምንት ዓመት በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ሲሰቃይ የነበረውን ሰው ማዳኑና ሌሎችን በሽተኞች የፈውስ መሆኑ የሚነገርበት ነው። ዮሐ 5፥8

5/ <u>ደብረ ዘይት</u> ⇨ እኩለ ጾም ነው። ጌታ በደብረ ዘይት ለደቀመዛሙርቱ የመምጣቱን ምሥጢርና የዓለምን መጨረሻ የተናገረበት በመሆኑ ይህንኑ የምናስብበት ነው። ማቴ 24፥3 መዝ 49፥2

6/ <u>ገብርሔር</u>⇨ቸር መልካም ባሪያ ማለትነው። መክሊቱን አትርፎ የተገኘውን ሰው "ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝም በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።" እንዳለው ሁሉ መልካም የሠራ ሁሉ በጎ ዋጋ እንዳለው የሚሰበክበት ነው። ማቴ 25፥14-30

7/ <u>ኒቆዲሞስ</u> ⇨ በሌሊት ወደ ጌታ እየመጣ ይማር ለነበረው የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ ስለ ዳግም መወለድ ጌታ ያስተማረበትን የምናስብበት ነው። ዮሐ 3፥1-11



www.ethiopianorthodox.org

8/ <u>ሆሣዕና</u> ⇨ ማለት መድኃኒት ፣ አሁን አድን ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ፣ ሆሣዕና በአርያም እያሉ ያመሰገኑበትና በቤተመቅደስ ይሸጡ ይለውጡ የነበሩትን ያስወጣበትን የሚያስታውስ ነው። ማቴ 21፥1-13 መዝ 117፥25-26 የመጨረሻ ሳምንት ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሰሙነ ሕማማት ነው።

2/ <u>ጾመ ነቢያት (ጾመ ስብከት)</u>

ይህ ጾም ነቢያት መሲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል ሲሉ ስለ መምጣቱና መገለጡ ከክርስቶስ ልደት በፊት የጾሙት ጾም ነው። ከኅዳር 15 እስከ ታህሳስ 29 ድረስ ይጾማል። ነቢያት ሊያዩት ወደው ያላዩትን የጌታን መወለድ እኛ በማየታችን በልደቱ ሰላምን በማግኘታችን ምክንያት እንጾመዋለን።

ዘጸ 24፥18 ፣ 34፥28 ዘዳ 9፥9 ዕዝ 7፥6 1ኛ ነገ 19፥8

3/ <u>ጾመ ነነዌ</u> ፡- (ነይ ነይ ይሏታል)

የነነዌ ከተማ ሕዝቦች በኃጢአታቸውና በክፋታቸው የተነሳ ሊመጣባቸው ካለው የእግዚአብሔር ቁጣ በአመድ ላይ ሆነውና ማቅ ለብሰው በማልቀሳቸው ድነዋል። እኛም የእግዚአብሔርን ምሕረት እያሰብን የምንጾመው ጾም ነው። ዮናስ 3፥1-10



4/ <u>ጾመ ሐዋርያት</u>፡- ቅዱሳን ሐዋርያት አባቶቻችን ለአገልግሎት ለሐዋርያነት ከመሰማራታቸው በፊት የቀና አገልግሎት መስጠት ይችሉ ዘንድ የጾሙት ጾም ነው።

ሐዋ 13፥1-3 ማቴ 9፥15 ማር 2፥20 ሉቃ 5፥33 2ኛ ቆሮ 6፥6

እኛም በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጸናልና (ኤፌ 2፥20) ሐዋርያትን ያጸናህ ያበረታህ እኛንም አጽናን እያልን እንጾመዋለን። ጾሙ በዓለ ሃምሳ ጰራቅሊጦስ በተከበረ ማግስት ጀምሮ እስከ ሐምሌ አምስት (5) ቀን ድረስ ይቆያል።

5/ <u>ረቡዕና ዓርብ</u> (<u>ጾመ ድኅነት</u>)

<u>ረቡዕ</u> ፡- አይሁድ በጌታ ላይ ምክረ ሞቱን የፈጸሙበት ስለሆነ ፣ እኛም ከክፉ ምክር ፣ ሃሳብ አርቀን እያልን እንጾማለን። ማቴ 26፥14-16

<u>አርብ</u> ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል የተሰቀለበት ፣ የሞተበት በመሆኑ መከራውን ፣ ሞቱን በመስቀል ላይ ያዳነንን ጌታ ፍቅሩን እያሰብን እንጾማለን። ሉቃ 23፥32

ይህ ጾም ከትንሳኤ በዓል አንስቶ እስከ ጰራቅሊጦስ ባሉት ሃምሳ ቀናት አይጾምም።



www.ethiopianorthodox.org

6/ <u>የፍልሰታ ጾም</u>

ሐዋርያት የእመቤታችንን ትንሣኤ ጌታ እንዲገልጽላቸው በማለት የጾሙት ጾም ነው። ስለዚህ ሐዋርያት ትንሣኤዋን እንዳዩ ሁሉ እኛም ክርስቲያኖች የትንሳኤዋን በረከት እንደ ሐዋርያት እንዲያሳትፈን በፍቅር እንጾመዋለን። ጾሙ ከነሐሴ መጀመሪያ ለሁለት ሳምንታት ያህል ማለትም ። ከነሐሴ 1 ቀን እስከ 16 ድረስ ይቆያል።

7/ <u>የገሃድ ጾም</u> ፥ ገሃድ ለውጥ ማለት ነው። የጥምቀት በዓል ረቡዕ ቢሆን በዋዜማው ማክሰኞ ፥ ዓርብ ቢሆን በዋዜማው ሐሙስ ይጾምና በዓሉ የሚውልባቸው ቀናት ረቡዕና አርብ አይጾምም።

ከልደት በፊት ያሉት ቀናት በሙሉ ጾመ ነቢያት ሲሆን ፥ አንዳንድ ያልጾሙ ሰዎች ግን በልምድ የገናን ዋዜማ ገሃድ ነው እያሉ ይጾማሉ።

## *<u>በጾም ላይ የሚነሡ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው</u>*

✣ " ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጂ ከሰው ውጭ የሚገባውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም።" ማር 7፥15

ይህ ስለ ጾም የተነገረ ሳይሆን ታጥቦ ስለመብላት በወግ አጥባቂ ፈሪሳውያን ለተጠየቀ ጥያቄ በጌታችን



ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ መልስ ነው። ማር 7፥1-22 እነርሱ እጃቸው እስኪቀላ ድረስ ይታጠቡ ነበርና።

ደቀ መዛሙርቱ ባልታጠበ እጅ ይበላሉ ብለው ለጌታ ሲነግሩት ሰውን ከውጭ ወደ ውስጥ የሚገባው ሊያረክሰው አይችልም። ሰውን የሚያረክሰው ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ ፤ ዝሙት ፤ መስረቅ ፤ መግደል ፤ ምንዝርነት ፤ መጐምጀት ፤ ክፋት ፤ ተንኮል ፤ መዳራት ፤ ምቀኝነት ፤ ስድብ ፤ ትዕቢት ፤ ስንፍና ናቸው። በአጠቃላይ በገላ 5፥19 ላይ የተጠቀሱት የሥጋ ፈቃዳት ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣልና ሰውን ያረክሰዋል አላቸው እንጂ ጾም አይገባም የሚል ትርጉም የለውም። በዚህ ቃል ፈሪሳውያን ተሰናክለውበታል። ማቴ 15፥10-20 ሐዋርያት ጾም እንደሚጾሙማ ጌታ " ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል ፥ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።" ብሏል።

ማቴ 9፥14 ፤ ማር 2፥18 ሐዋርያትም ደግሞ ጾመዋል። ሐዋ13፥2

ጌታ እግዚአብሔር ሰዎች በጾም ወቅት ፈቃደ ሥጋቸውን ገትተው እንዲጾሙ ይፈልጋል እንጂ በጾብ ፤ በክርክር ፈቃደ ሥጋን በመፈጸም ሊሆን እንደማይገባ ተናግሯል።

ጾም የተራበን በማብላት ፤ የተጠማን በማጠጣት ፤ የተራቆተውን በማልበስ ሊሆን ይገባል። ከዚህ ውጪ ግን በኃጢአትና በበደል የሚጾሙት አይጠቅምም። ኢሳ 58፥3-9



www.ethiopianorthodox.org

## ፺ ጸሎት

ሰው ከአምላኩ ጋር የሚነጋገረው ንግግር ማለት ነው።

"ጸሎት ብሂል ተናግሮ ምስለ እግዚአብሔር።"

ጸሎት ሰው የፈለገውን ነገር የሚያገኝበት መንገድ ማለት ነው።

ጸሎት የዲያብሎስን ፈተና ለመቋቋም የሚያስችለን ኃይል ነው። ጸሎትን መላልሰን መጸለይ እንደሚገባ ጌታ አስተምሮናል። እውነተኛ ጸሎት ኃይል አለው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ 4፥1 | ማቴ 7፥7 | ሉቃ 1፥11 | ያዕ 5፥16 |
| " 6፥9 | " 17፥21 | ሉቃ 11፥1-13 | ሲራክ 2፥10 |
| " 16፥1 | " 26፥41 | ሉቃ 18፥1 | 1ኛ ተሰ 5፥9 |
| " 54፥1 | ማር 10፥46 | ፊልጵ 4፥6 | |

### የጸሎት ዓይነቶች

1ኛ/ <u>የግል ጸሎት</u>፦ መዝ 50፥1 ፣ ዳን 9፥3 ፣ ማቴ 6፥5 ፣ ሉቃ 2፥37 ፣ 9፥18 ሐዋ 3፥1 ፣ 20፥36

2ኛ/ <u>የቤተሰብ ጸሎት</u>፦ ኢያ 24፥15 ፣ ኢዮ 1፥5 ፣ ሐዋ 10፥2 ሐዋ 21፥5

3ኛ/ <u>የማኅበር ጸሎት</u>፦ ኢዩ 7፥6 ፣ 2ኛ ዜና 7፥14 ፣ መዝ 21፥8 ፣ ኤር 29፥12 ፣ ማቴ 18፥20

ሰባቱ <u>የጸሎት ጊዜያት</u>፦ (መዝ 118፥164)

እግዚአብሔርን በቀን የምናመሰግንባቸው ሰባት ጊዜያት፦



1ኛ/ ጠዋት፦ ጌታ በጲላጦስ ፊት የቆመበት (ማቴ 27፥1፣መዝ 5፥3)

2ኛ/ <u>በሶስት ሰዓት</u>፦ ጌታ የተገረፈበት ዮሐ 19፥1

3ኛ/ <u>በስድስት ሰዓት</u>፦ ጌታ በቀራኒዮ በመስቀል ላይ የተሰቀለበት፦ ዮሐ 19፥14 ፣ መዝ 54፥17

4ኛ/ <u>በተሰዓት( ዘጠኝ ሰዓት)</u>፦ ጌታ ነፍሱን የለየበት ማቴ 27፥50 ፣ ሐዋ 3፥1

5ኛ/ <u>በሠርክ ( አስራ አንድ ሰዓት)</u>፦ ጌታ ወደ ከርሠ መቃብር የወረደበት ሉቃ 23፥50

6ኛ/ <u>በንዋም( በመኝታ ጊዜ)</u>፦ ጌታ ለሐዋርያት ሥርዓተ ጸሎት ያስተማረበት ማቴ 26፥41 ፣ መዝ 29፥5

7ኛ/ <u>በመንፈቀ ሌሊት</u>፦ ጌታ የተነሳበት በመሆኑ ነው። ሉቃ 24፥5 ፣ ሐዋ 16፥36 ፣ መዝ 118፥62

## ፺፩ ንስሐ

ንስሐ ማለት ቀድሞ ከሠሩት ኃጢአት መመለስ ፣ መጸጸት ፣ ራስን መለወጥና ማዘን ማለት ነው። ሰው በሰራው



www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአት ተጸጽቶና አዝኖ በልቅሶ እግዚአብሔርን ምህረት፥ ይቅርታ ቢለምን ስርየተ ኃጢአትን ያገኛል። ንስሐ አዲስ ሕይወትን ማግኘት ማለት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| 2ኛ ሳሙ 12፥16 | ሕዝ 18፥23 | ሉቃ 15፥18፤23፥42 |
| መዝ 6፥6፤31፥1 | ዘካ 1፥3 | ዮሐ 5፥14 |
| ምሳሌ 28፥13 | ሲራክ 5፥5 | ሐዋ 2፥38፤3፥19 |
| ኢሳ 1፥18 | ማቴ 3፥1፤4፥17 | 2ኛ ቆሮ 7፥10 |
| ሰቆ 3፥40 | ማቴ 11፥28 | 1ኛ ጴጥ 4፥3 |
| 2ኛጴጥ 3፥9 | ራእይ 2፥5 እና16 | ራእይ 3፥19 |

✞ ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ ፣ ራስን ማሳየት (ማስመርመር) ይገባል። ሰውን ከኃጢአቱ የመፍታት ሥልጣን ለካህናት ተሰጥቷቸዋል።

| | | |
|---|---|---|
| ዘሌ 4፥20-26 | ማቴ 3፥6፤8፥4 | ሉቃ 5፥14 |
| ዘሌ 5፥5፤14፥2 | ማቴ 16፥18፤18፥18 | ሉቃ 17፥14 |
| ኤር 42፥1-6 | ማር 1፥44 | ያዕ 5፥16 |
| ዮሐ 20፥23 | 1ኛ ጢሞ 5፥20 | ዮሐ 20፥22-23 |
| ሐዋ 19፥18 | 2ኛ ቆሮ 2፥6 | 1ኛመቃ 26፥5 |

## ፳፩ ምጽዋት

ሰው ወጥቶ ወርዶ ደክሞ ካገኘው ላይ የሚያደርገው በጎ ስጦታ ነው። ምጽዋት ብልና ዝገት በማያበላሸው ሌቦችም



በማይሰርቁት ስፍራ በሰማይ መዝገብ ማከማቸት ነው። ምጽዋት ሲሰጡ ብድራትን ሁሉ የሚከፍል እግዚአብሔር መሆኑን እምነን ሊሆን ይገባል።

ሲራክ 7፥33 ማቴ 6፥9 2ኛቆሮ9፥6 ምሳሌ 19፥17
ሉቃ 14፥12 ሲራክ 3፥29፤4፥1 ሲራክ 29፥11 ሮሜ12፥8

✞ ምጽዋት ሁሉም በአቅሙ ሊፈጽመው የሚገባ በጎ ተግባር ነው። ማር 12፥41

✞ በእምነት የሚፈጽሙት ምጽዋት ሰማያዊ ዋጋ ያለውና የተትረፈረፈ የእግዚአብሔርን በረከት የሚያስገኝ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ11፥24 | መዝ 40፥1 | ሲራክ 17፥21 |
| ምሳሌ 28፥27 | ሲራክ 29፤1-9-13 | ሲራክ 4፥1 |
| 2ኛ ነገ 12፥5 | ሲራክ 7፥10 | ሲራክ 18፥1 |
| 1ኛ ዜና 29፥14 | ሲራክ 3፥28 | ሲራክ 32፥4 |
| ሐዋ 10፥4 | ሲራክ 16፥14 | ጦቢት 1፥1፥4፥7 |
| ማቴ 25፥34 | ዳን 4፥27 | |

## ፳፪ አሥራት በኩራት

አሥራት ከአሥር አንድ ማለት ነው። ሰዎች ከሁሉ ነገር ከአሥር አንድ እንዲሰጡ እግዚአብሔር አዟል።

ዘፍ 14፥20 ዘሌ 27፥32 ዘዳ 26፥2 ዘፍ 28፥22 ዘኁ18፥21
1ኛ ዜና 29፥14 ዘጸ 23፥29 ዘዳ14፥22 ሚል 3፥8



www.ethiopianorthodox.org

✞ ከሰውም ከእንስሳትም የመጀመሪያው ማህፀንን የሚከፍት የበኩር ነውና ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ በአሪት ታዝዞ ነበር። ዘጸ 13፥1 ምሳሌ 3፥9

## ፳፬ ስዕለት

ስዕለት ማለት ልመና ማለት ነው። ሰው በስለት ልመናን ለአምላክ ያቀርባል። እግዚአብሔርም ይሰማል።

ዘፍ 28፥20 መሳ 11፥30 መዝ 55፥12፣65፥13
ዘሌ 27፥2 1ኛ ሳሙ 1፥11 ናሆም 1፥15
ዘኁ 21፥2 ኢዮብ 22፥27 ዮናስ 1፥16፣2፥10
ሐዋ 18፥8

✞ ስዕለታችንን የግድ መፈጸምና ማቅረብ አለብን እንጂ ማስቀረት በፍጹም አይገባም

ዘኁ 30፥2 መዝ 75፥11 መክ 5፥4-5
መዝ 60፥8 ኢሳ 19፥21 ምሳሌ 7፥14
መዝ 65፥13 ኤር 44፥26 ሲራክ 7፥14
ሲራክ 18፥18

✞ ስለዚህ ስዕለት ከመሳላችን በፊት በአቅማችንና በማስተዋል ሊሆን ያስፈልጋል እንጂ ከተሳልን በኋላ ለመፈጸም የሚያስቸግርና የሚከብድ መሆን የለበትም።

ዘዳ 23፥21-23 መሳ 11፥29-40 ምሳሌ 20፥25



## ፳፭ ጋብቻ (ሥርዓተ ተክሊል)

ተክሊል ማለት ክብር ማለት ሲሆን ሙሽሮች በጋብቻቸው ጊዜ የሚፈጸምላቸው ሥርዓት ነው። ይህም ጸሎት ሙሽራውና ሙሽራይቱ አንድ የሚሆኑበት ፣ ሳይለያዩ እንዲኖሩ የሚያስችላቸው መንፈሳዊ ኃይልን የሚያስገኝ ነው።

ስለዚህ እምላካችን አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ጸንቶ በቅዱስ ጋብቻ ተወስኖ መኖር እንደሚገባ አዞናል። የጋብቻ ዋና ዓላማም፦ እርስ በርስ ለመረዳዳት ፣ ልጆችን ለማስገኘት ፣ ከዝሙት ለመጠበቅ ነው። በአዳምና በሔዋን መካከል በፈቃደ እግዚአብሔር የተመሰረተው ጋብቻ ቅዱስ ነው። በቅዱስ ጋብቻ አንድ የሆኑ ሰዎች ከጾምና ከጸሎት በስተቀር ሊለያዩ አይገባም። ከቅዱስ ጋብቻ የሚገኝ ቤተሰብ ፍሬው ያማረ ነው። የጋብቻ ሥነስርዓት መፈጸም የሚገባው ቅድስትቤተክርስቲያን እንደምታዝዘው በተክሊል ፣ በሥጋ ወደሙ መሆን አለበት

ዘፍ 2፥18 ጦቢት 8፥6 ማቴ 19፥4-9
ኤፌ 5፥22 ዮሐ 2፥1-11 ዕብ 13፥4
ምሳሌ 18፥22 1ኛ ቆሮ 7፥2 ሮሜ 7፥2



www.ethiopianorthodox.org

## ✞ ባል ለሚስቱ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ሥራዎች

ባል ለሚስቱ ያለው ፍቅር የጠበቀ መሆን አለበት። ኤፌ 5፥25 ባል ሚስቱን እንደራሱ አድርጎ መውደድ ይገባዋል። 1ኛ ቆሮ 7፥39 እስከ ሕይወት ፍጻሜው የማትለየው የቅርብ ጓደኛው መሆኗን መገንዘብ አለበት። ምሳ 5፥18 ሲራክ 7፥26

በመካከላቸው የሚፈጠረውን ጸብ ሁሉ በሰላም በፍቅር ማሸነፍ ይኖርበታል። ሁልጊዜ የክርስትናን መንገድ መከተል፣ መግባባት እንጂ ሀሳቦቿን ሊንቅና ሊያቃልል አይገባውም ሚል 2፥14 ስለዚህ ሁልጊዜ ሰላማዊና ትሑት ሊሆን እንጂ የበላይነትን መንፈስ ማሳየት ፣ መቆጣትና መጨቆን የለበትም።

1ኛ ጴጥ 3፥7 ፣ ቆላ 3፥19 ሲራክ 25፥1

## ✞ ሚስት ለባልዋ ልትፈጽማቸው የሚገቡ ሥራዎች

ሴት በቤተሰቡ መካከል ያለች ማዕከል ስለሆነች ለሁሉም መልካም ምሳሌ መሆን አለባት። ስለዚህ በእግዚአብሔር ፈቃድ የባልዋን የልጆችዋን ሁሉ ፈቃድ ተቀብላ



www.ethiopianorthodox.org

የምትፈጽም ፣ የቤቱን ጸጥታና ሰላም የምትከታተል መሆን አለባት። ኤፌ 5፥22 ፣ 1ኛጢሞ 5፥10

ከባልዋ ጋር ጥሩ መቀራረብና የፍቅር ሕይወት ሊኖራት ያስፈልጋል። ኤፌ 5፥33 ሚስት ታጋሽ መሆን ይኖርባታል። ምሳ 14፥30 ፣ 14፥1 በእምነት ጠንካራ የሆነች ሚስት የባልዋ ዘውድ ናት። ምሳ 12፥4 ባልዋ ሲበሳጭ በመልካም ንግግሯ በመምከር ማረጋጋት ፣ ማጽናናት ይጠበቅባታል። ምሳ 31፥30 1ኛ ጴጥ 3፥1-6 ፣ ቆላ 3፥18 ቲቶ 2፥4 ሮሜ 7፥2-3

## ✞ ወላጆች ለልጆቻቸው ሊያደርጉዋቸው የሚገቡ ሥራዎች

ለተወለዱት ልጆች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከእግዚአብሔር በታች ተስፋዎቻቸውና አለኝታዎቻቸው ወላጆች ናቸው። ስለዚህ ልጆችን ፍቅርን በተሞላ መንገድ መንከባከብ መምከር ማስተማርና እምነታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ የወላጆች ድርሻ ነው።

ወላጆች በጥሩ ክርስቲያናዊ ሕይወት (ሥነ ምግባር) እየኖሩ ለልጆቻቸው መልካም ምሳሌ መሆን አለባቸው። ፈሪሃ እግዚአብሔር ካደረባቸው ወላጆች የሚወለዱ ልጆች ፈሪሃ እግዚአብሔር ያድርባቸዋል። ስለዚህ ወደ ቤተክርስቲያን

ስንሄድ አብረውን እንዲሄዱ እናድርጋቸው። እምነትን ከሚቃወሙ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ፣ ፊልም ፣ ምግባርን ከሚያበላሹ ጓደኛ ፣ እምነትን ከሚመርዙ ሰዎች ልጆችን ማራቅ አለብን።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ 22፥6 | ምሳሌ 29፥15 | 2ኛ ቆሮ 12፥14 |
| ምሳሌ 23፥13 | ሲራክ 7፥23 | ቆላ 3፥2 |

## ✞ ልጆች ለወላጆቻቸው ሊያደርጉዋቸው የሚገቡ ሥራዎች

ልጅን ከእውቀት ደረጃ እስኪደርስ የሚያከሙሉት ወላጆች መሆናቸው ግልጽ ነው። ስለዚህ ልጆች ለወላጆች ታዛዥ ፣ ቤተሰባቸውን አክባሪ ጣ/ሪ መሆን ያስፈልጋቸዋል። ልጆች ወላጆቻቸውን ቢያከብሩ የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈጽማሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ 22፥1-14 | ምሳ 4፥1 | ሲራክ 3፥1-17 |
| ዘፍ 47፥10 | ምሳ 6፥20 | ሲራክ 7፥27 |
| ዘጸ 20፥12 | ምሳ 23፥22 | ሲራክ 8፥4 |
| ሉቃ 2፥51 | ቆላ 3፥20 | 1ኛጢሞ 5፥8 |
| ኤፌ 6፥1 | 1ኛጢሞ 4፥12 | |

## ፭ ቀንዲል

የታመሙ ሰዎች በቀሳውስት ጸሎት እየተቀቡ የሚፈወሱበት ቅብዕ ነው። የነፍስና የሥጋ ፈውስ የሚያሰጥ



ነው። የመፈወስ ኃይል ሲኖረው ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲፈጸም የነበረ ነው።

ማር 6፥13፤16፥17 1ኛ ቆሮ 4፥1 1ኛ ቆሮ 12፥28 ያዕ 5፥14

## ፮ ሜሮን

አዲስ የሚጠመቅ ሰው ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበረታ እንዲሆን በቀሳውስት የሚቀቡት በጸሎት የከበረ ዘይት ሲሆን ፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ያሰጣል ፣ ልጅነትን ያሰጣል። ምስጢሩ የሚፈጸመው ለተጠመቁ ብቻ ሲሆን የማይደገም ምስጢር ነው።

ሐዋ 2፥1፤8፥16 2ኛ ቆሮ 1፥21 ኤፌ 1፥13፤4፥30 1ኛ ዮሐ 20

## ፯ ክህነት

ካህን ማለት አገልጋይ ፣ ክህነት ደግሞ አገልግሎት ማለት ነው። ይኸውም እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገል ነው። የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ያለው ከፍ ያለ ማዕረግ ነው። ካህን ጠባቂ ነው ኤር 3፥15

✞ ካህን ንስሐን መቀበል ቀኖና መስጠት ይችላል። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው የነፍሱ ጠባቂ ካህን ያስፈልገዋል። መሳ 17፥7-13



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

✞ ካህን በማስተማር ፣ መሥዋዕት በማቅረብ ፣ በመባረክ ፣ ንስሐን በመቀበል ፣ ቀኖና በመስጠት ፣ በማጥመቅ አገልግሎቱን ይፈጽማል።

ዘሌ 4፥20 ማቴ 8፥4 ማቴ 18፥18 ዮሐ 20፥23

ዘሌ 6፥22 ማቴ 16፥19 ሉቃ 17፥14 ማር 6፥13

ያዕ 5፥16

✞ ሥልጣነ ክህነት ለሴቶች እንዲሰጥ አልተፈቀደም።

1ኛ ቆሮ 14፥34 ፤ 1ኛ ጢሞ 2፥10-15

የክህነት ማዕረጋት ሦስት ናቸው።

1ኛ/ <u>ዲቁና</u> ⇨ ሐዋ 6፥3-6 ፤ 1ኛ ጢሞ 3፥8-13

2ኛ/ <u>ቅስና</u> ⇨ ሐዋ 14፥23 ፤ ቲቶ 1፥5 ፤ ያዕ 5፥14

3ኛ/ <u>ጵጵስና</u> ⇨ ሐዋ 20፥28 ፤ 1ኛ ጢሞ 3፥2

## ✞ *<u>ሁላችንም ካህን ነን ለሚሉት</u>*

ሥልጣነ ክህነት ለተመረጡ ሰዎች ብቻ እንጂ ሁሉም ሰው ካህን ሊሆን አይችልም። ኤፌ 4፥11 ሰው ካህን (ጠባቂ) ሊሆን የሚችለው ሲመረጥና ሲሾም ብቻ ነው እንጂ ያልተሾመ ሰዎች ካህን ነን ሊሉ አይገባም።



ዛሬ ግን በፕሮቴስታንት ዓለም ሁሉም ካህን ነው በማለት ሴቶች ሳይቀሩ ጵጵስና እየተሾሙ ፣ እነሱም እጅ እየጫኑ መጸለይ የዕለት ተዕለት የተለመደ ተግባር ሆኗል።

ነገር ግን ክህነት እግዚአብሔር ለመረጣቸውና ለለያቸው እንጂ ሳይመረጡና ሳይሾሙ ካህን ነኝ ማለት አይቻልም።

1ኛ ሳሙ 2፥28 ፤ ዘጸ 28፥1-43 ፤ ራእይ 1፥6

ሁሉም ካህን ቢሆን ኖሮ ንጉሡ ዖዝያን በድፍረት ወደ ቤተመቅደስ ገብቶ ሲያጥን በለምጽ በሽታ ባልተቀጣ ነበር። 2ኛ ዜና 26፥16-21

## ፳፱ <u>ምንኩስና</u>

በአንድ ልብና ሐሳብ ሆኖ እግዚአብሔርን ለማገልገል ከዓለም ተድላና ደስታ መለየት ማለት ነው። ሰውነትን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ መኖር ነው።

ዘፍ 5፥24 ማቴ 19፥16 1ኛ ቆሮ 7፥32

ኢሳ 56፥5 ማቴ 22፥32 ዕብ 11፥5

ሲራክ 2፥1 ገላ 6፥4 ያዕ 5፥11

## ፴ <u>ልሳን</u>

ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው ። በአዲስ ልሳን መናገር ማለት ተወልደው ባላደጉበት ወተው ወርደው ባልተማሩበት ቋንቋ ሰዎች የሚሰሙትንና የሚናገሩትን



www.ethiopianorthodox.org

ልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር ማለት ነው (ማር 16፥17) ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱ በልሳን መናገር ነው። (ሐዋ 8፥17 ፣ ሮሜ 12፥3 ፣ 1ኛ ቆሮ 12፥10 ሰፎ 3፥9 ፣ ኩፋሌ 9፥25)

በሐዲስ ኪዳን በልሳን መናገር ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለሐዋርያት ሲሆን፤ ዕለቱም በበዓለ ሃምሳ (ጴንጠቆስጤ ለሐዋርያት ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ቀን ፣ ጌታችን በተነሳበት በሃምሳኛው ቀን ነው። (ሐዋ 2፥1-21)

በዓለም ካሉት ቋንቋዎች አንዱን በማይመስልና የቋንቋ ጠባይ እንኳን የሌለውን ማንም ሊተረጉመው የማይችለውን ልሳን ልንለው አይገባም። ምክንያቱም ልሳን በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት የሚሰጥ ጸጋ በመሆኑ በዚህ ስጦታ ደግሞ ሰላምና ደስታ እንጂ ጭንቀት ፣ መንቀጥቀጥ ፣ መንዘፍዘፍ ፣ አዕምሮን መለወጥ የለበትም። (ማቴ 7፥22 ፣ 1ኛ ቆሮ 14፥7-23

## ፴፩ ትንቢት

ትንቢት ወደፊት የሚሆነውንና የሚመጣውን የሚገልጥ ነው። የትንቢትን ቃል መተርጎም ከባድ ነው ስለዚህ በፍጻሜው ይታወቃል እንጂ ከመፈጸሙ በፊት እንዴት እንደሚሆን አይታወቅም። ትንቢትን ሁሉ መቀበል



ሳያዘን ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን መርምረን ማወቅ መረዳት ያስፈልጋል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘዳ 18፥22 | ማቴ 7፥22 | ሚል 4፥5 | ኢዩ 2፥28 |
| 1ኛ ሰሚ 4፥1-5 | ማቴ 11፥4 | ሕዝ 13፥1 | |
| ሐዋ 19፥5 | ሐዋ 3፥18 | ዕብ 1፥1 | |
| 1ኛ ጴጥ 1፥10 | 1ኛ ዮሐ 4፥1 | ራእይ 1፥3 | |
| 1ኛሳሙ 10፥10 | 1ኛቆሮ 12፥10 | ራእይ 22፥7 | |

## ፴፪ በዓላት

በዓል ማለት የተቀደሰ ፣ የተከበረ ልዩ ክቡር ቀን ማለት ነው። በዓላት በልማድ የሚከበሩ ወይንም ስራን ላለመስራት ተብሉ የተፈጠሩ አይደሉም። የበዓላት ሁሉ መነሻ ምንጫቸው ሃይማኖት ነው። በብሉይ ኪዳን የሚከበሩ ብዙ ዓይነት በዓላት ነበሩ። የበዓል ሁሉ መሰረት ግን ቀዳሚት ሰንበት ናት። ሰንበት ማለት ዕረፍት ማለት ነው። (ዘፍ2፥2) በሐዲስ ኪዳን ሰንበት ቅዳሜና እሑድ ነው። ሰንበተ ክርስቲያን እሑድ ጌታ ፍጥረትን መፍጠር የጀመረበት ፣ የተጸነሰበት ፣ ከሙታን ተለይቶ ፣ የተነሳባት ናትና ይህች ዕለት ትከበራለች።(ራእይ 1፥10 ማቴ 28፥1፤ሉቃ24፥1)

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ 16፥23፥20፥8 | መዝ 41፥4 | ምሳ 23፥10 |
| ነህ 8፥9 | መዝ 75፥10 | ሐዋ 20፥7 |
| ኩፋሌ 7፥23 | ዮሐ 10፥22 | 1ኛቆሮ 16፥2 |



www.ethiopianorthodox.org

✝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የበዓላት አከባበር ሥርአት አለው። (1ኛ ቆሮ 14፥40)

## ✝ *የጌታ ዘጠኝ ዐበይት በዓላትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻቸው*

1/ ብስራት= ሉቃ 1፥26

2/ ልደት= ሉቃ 2፥7

3/ጥምቀት= ማቴ 3፥13 ፣ ሉቃ 3፥21

4/ ደብረ ታቦር ማቴ 17፥1፣ማር 9፥2፣ማር 912፣ሉቃ 9፥28

5/ ሆሳዕና= ማቴ 21፥1 ፣ ዘካ 9፥9 ፣ መዝ 117፥26

6/ ስቅለት= ሉቃ 23፥33

7/ ትንሣኤ= ሉቃ 24፥5

8/ ዕርገት= ሉቃ 24፥50

9/ ጰራቅሊጦስ (በዓለ ሃምሳ) ሐዋ 2፥4

## ✝ *ዘጠኙ የጌታ ንዑሳን በዓላት*

1/ መስቀል= ማቴ 27፥1ኛ ቆሮ 1፥18

2/ ስብከት ዮሐ 1፥44 ፣ ዕብ 11፥1

3/ ብርሃን ፣ መዝ 42፥3 ኢሳ 9፥2 ፣ ዮሐ 8፥12

4/ ኖላዊ= መዝ 22፥1፣79፥1 ፣ ዮሐ 10፥1-22 ፣1ኛጴጥ 2፥25



5/ ግዝረት= ዘሌ 12፥3 ፣ ሉቃ 2፥21

6/ ልደተ ስምዖን ሉቃ 2፥25

7/ ቃና ዘገሊላ= ዮሐ 2፥1

8/ ደብረ ዘይት= ማቴ 24

9/ የመጋቢት መስቀል (መጋቢት 10 ቀን)

## *፴፫ ጸበል*

ጸበል በትርጉሙ አረር ፣ ትቢያ ፣ ጭቃ ቢሆንም እንኳን ፥ በቤተክርስቲያናችን ጸበል የተቀደሰ ፣ የተባረከ ውሃ ማለት ነው። ይኸውም ጸበል በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ዘኁ 19፥9 | ኤር 32፥17 | ዮዲት 12፥7 |
| ዮሐ 5፥2 | ሕዝ 47፥3-12 | 2ኛ ነገ 5፥1-15 |
| ዮሐ 9፥6 | | |

## ✝ *ሦስት ዓይነት ነው*

1/ ***የቅዳሴ ጸበል***፦ ቅዳሴ የተቀደሰበት የተለየ ጸበል ሲሆን ፥ የጌታን ሥጋና ደም የተቀበሉ ምእመናን ከአፋቸው እንዳይነጥብ የሚጠጡት ነው።

2/ ***ማየ ጸሎት***፦ የቡራኬ ጸበል ይባላል። ውኃ በሌለበት ቦታ በዕቃ ተቀድቶ ካህኑ ጸሎት አድርጎ እፍ ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ከባረከው በኋላ የሚያጠምቅበት ፣ የሚረጭበት ጸበል ነው።
መዝ 50+7፤ሕዝ 36+25፤ ዮሐ 20+22

✱ ልጅነትን ለማግኘት የምንጠመቅበት ማየ ገቦ (የጐን ውሃ) ይባላል። ይህም በዕለተ ዓርብ ጌታ ጐኑን በጦር ሲወጋ የፈሰሰው ደምና ውሃ ነው። ውሃው የምንጠመቅበት ፥ ደሙ የዘላለም ሕይወትን የምናገኝበት ነው።

3/ በየስፍራው እየፈለቀ የምንጠመቅበት ጸበል ነው። ይኸውም በገዳማትና አድባራት አካባቢ (ግቢ) ውስጥ ያለው ጸጋ እግዚአብሔር ያደረበት የተለያዩ ድንቅ ተአምራት የሚፈጸምበት ቅዱስ ውኃ ነው።

2ኛ ነገ 5+24 ዮሐ 5+4

<u>ለምሳሌ</u> የእንጦጦ ኪዳነምህረት፣ማርያም ፥ የሁራኤል ፥ የዮሐንስ ጸበል . . .

## ፲፱ <u>የጽዋ ማኅበር</u>

ይህ ዓይነቱ ትውፊታዊ ሥርዓት አጀማመሩ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን በሀገራችን በኢትዮጵያ ተጠብቆ የኖረ ፥ ምእምናን በየተራ ምግብና መጠጥ አዘጋጅተው ከችግረኞች ጋር የሚሳተፉበት ሥርዓት ነው። በቤታ ፣ በእመቤታችን ፣ በቅዱሳን መላእክት ፣ በጻድቃን ፣ በሰማዕታት ስም በመታሰቢያ ዕለታቸው ይፈጸማል።



የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችን ሕይወት የሚያስታውስ ነው። ይህ አብሮ መብላትና መጠጣት የአንድነት ፥ የፍቅር ማዕድ አጋፔ (Agape) ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበረ ነው። በዚህም በረከት ይገኝበታል። ዘሌ 16+29

መዝ 3+8 ሐዋ 2+44 ቆላ 2+5
መዝ 54+14 ሐዋ 4+32-37 ዕብ 3+7
ምሳ 10+7 ዕብ 10+25

## ፳ <u>ዝክር</u>

እግዚአብሔር በድንግል ማርያም ፣ በቅዱሳን መላእክት ፣ ጻድቃን ሰማዕታት አድሮ የፈጸመውን ታላላቅ ሥራዎች በማስታወስ ስማቸውን ጠርተው የሚያከብሩት መታሰቢያ ነው።
መዝ 110+2-4 ፤ መዝ 67+35 ምሳ 10+7

✝ እስራኤል ከግብጽ ባርነት የወጡበትን እያስታወሱ በዓል ያከብሩ ነበር።
ዘጸ 12+1 ፣ ዘሌ 23+5

✝ እኛም አምላካችን ያደረገልንን በማሰብ በቤታ ፥ በቅዱሳን ስም የምናደርገው ነው። ማቴ 10+42



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

✞ ድኃ ሀብታም ሳይለይበት ሁሉ ተጠርቶ የሚጋበዝበት ፣ ብድራትን ሳይሹ ከሚፈጸም በጎ ተግባራት (መንፈሳዊ ሥራ) ከሚሰራበት ከተቀደሰ ዓላማ አንዱ ነው።

ማቴ 25፥35፤26፥13 ማር 9፥41 ሉቃ 14፥12 ዕብ 6፥10

✱ መዝ 134፥13

## ፴፮ ሞትና ሐዘን

ሞት የነፍስና የሥጋ መለየት ፤ ሕይወትን ማጣት ነው።

ማቴ 9፥18፤8፥22 ፤ ሐዋ 9፥36

✞ በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ሞት ወደ ዓለም ገባ።

ዘፍ 2፥17 ፤ ሮሜ 5፥12፤6፥23፤ 1ኛ ቆሮ 15፥22፤ ጥበብ 1፥13

✞ ሞት የተጀመረው ወንድሙ ቃየል በገደለው በአዳም ልጅ አቤል ነው። ዘፍ 4፥8

✞ በሥጋ ሞት ለተለዩን ሰዎች ሐዘን ይገባል።

2ኛሳሙ 1፥11፤3፥31፤18፥33 ፤ 1ኛነገ 13፥29፤2ኛዜና35፥25፤ ዘኍ20፥29፤ ዘዳ 34፥8፤ ሲራክ 38፥16-18 ፤ ዮሐ 11፥33

✞ ነገር ግን ሐዘናችን በልክ ሊሆን ይገባዋል እንጂ ጸጉር በመንጨት ፣ ደረትን በመድቃት ፣ ትንሣኤ ሙታንን እንደማያምኑት በቀቢጸ ተስፋ ሊሆን አይገባም።

ዘዳ 14፥2 ፤ 2ኛሳሙ 12፥22 ፤ ኩፋሌ 14፥22 ፤ 17፥3 ፤ 1ኛተሰ 4፥13 ሉቃ 23፥29



✞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ለሞቱ ሰዎች ማልቀስ የሚገባን ሦስት ጊዜ ነው።

1/ ነፍስ ከሥጋ በምትለይበት ጊዜ ፤

2/ አስከሬን ከኖረበት ቤት ወጥቶ ወደ መካነ መቃብር ሲሄድ ፤

3/ ጎብኚት መሬት በሚፈጸምበት ጊዜ ብቻ ነው።

✞ በኃጢአት መኖር ሰዎችን ሙታን ያስብላቸዋል።

ሉቃ 1፥19 ፤ ማቴ 8፥22 ኤፌ 2፥1 ፤ ሮሜ 6፥23

✞ ሰው ሲሞት ከሥጋው የተለየችው ነፍሱ በእግዚአብሔር ፊት ፍርድን ትቀበላለች።

መክ 12፥7 ፤ ሉቃ 16፥19 ፤ 2ኛቆሮ 5፥1-5
ፊልጵ 1፥21 ፤ ዕብ 9፥27 ፤ ያዕ 2፥26

✞ ክርስቶስ በሶስተኛው ቀን ተነስቶ ሞትን ድል አደረገ። የሞት መውጊያ ተሰበረ።

ሉቃ 24፥5 ፤ 1ኛቆሮ 15፥53-57 ፤ 2ኛጢሞ 1፥10 ፤
ዕብ 2፥14 ፤ ራእይ 1፥18 መዝ 77፥65



www.ethiopianorthodox.org

✞ ከሞት በኋላ ትንሣኤ አለ። ያን ጊዜ መልካም የሰሩና ክፉ የሰሩ ተለይተው ዋጋቸውን ይቀበላሉ። ጻድቃን በክብር የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉ። ኃጥአን ግን ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ። ይህም ሁለተኛ ሞት ነው።

ኢሳ 35፥10 ኤር 20፥11 ዳን 7፥14፣12፥12
ማር 9፥45 ዮሐ 5፥24 ማቴ 13፥41፣25፥46
2ኛተሰ 1፥9 ዕብ 10፥27 ሉቃ 16፥22፣23፥43
ራእይ 14፥9፣ 20፥6፣21፥8

✞ የቅዱሳን ሞት ዕረፍት ነው።

መዝ 115፥6 ፣ ራእይ 14፥13 ዮሐ 11፥25

## ፴፯ ተዝካር

ተዝካር ለሙታን በጸሎት ፣ በመስዋዕት ፣ በመብራት፣ በማዕጠንትና በምጽዋት የሚደረግ መታሰቢያ ነው የሚደረገው ጸሎት ለሞቱ ሰዎች ደኅንነት ፣ በሕይወተ ሥጋ ላሉ ደግሞ በረከትን ያስገኛል።

መሳ 11፥40 2ኛ ነገ 4፥32 መዝ 111፥6 ምሳ 10፥7
ዕዝራ ሱቱ 6፥31

✞ ለሞተ ሰው ተዝካር ማውጣት እንደሚገባ ሲራ 7፥33 ፣ 38፥16



## ፴፰ ጸሎተ ፍትሐት

ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩ ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከሰሩትና ከፈጸሙት በደል እንዲነጹ ከማዕሠረ ኃጢአት እንዲፈቱ በካህናት አባቶች ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት ነው። ይህ ጸሎት የሚደረግበት ምክንያት የሞተው ሰው ስለ ኃጢያቱ ተጸጽቶና አዝኖ እያለ የንስሐውን ሥርዓት ከመፈጸሙ በፊት በሞት ቢቀደም እምላክ ይቅርታ እንዲያደርግለት ለመለመን ነው። ቤተክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት የምታደርገው ይሆናል ይደረጋል በማለት በፍጹም እምነት ነው።

2ኛ ነገ 4፥32 ማቴ 7፥7 ዲድስቅልያ አንቀጽ 33
መዝ 115፥6 ማቴ 22፥1 ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 22
ምሳ 15፥29 ማር 11፥24
ጥበብ 4፥16 ዮሐ 14፥13

✞ ሙታንና ሕያዋን የሚገናኙት በጸሎት አማካኝነት ነው። ሕያዋን ለሙታን ሙታንም ለሕያዋን ይለምናሉ።

ሄኖክ 12፥34

## ፴፱ ሐውልት

✞ ሐውልት አንድ ወጥ ከሆነ ድንጋይ ተጠርቦ ለመታሰቢያነት የሚቆም ምልክት ነው። በመካነ መቃብር



www.ethiopianorthodox.org

ላይ የመታሰቢያ ድንጋይ /ሐውልት/ ማቆም የተጀመረው በያዕቆብ ዘመን ፣ በራሔል መቃብር ላይ ነበር። ዘፍ 35፥20፣ ዘፍ 31፥45 ፣ ዘፍ 28፥10-22

✞ በቀድም ዘመን ሐውልት በሁለት ወገኖች መካከል ለሚደረግ ቃል ኪዳን ምልክት ተደርጐ ለመታሰቢያነት ይሆን ዘንድ ይቆም ነበር። ኢያ 4፥6፤24፥27 ፣ 1ኛሳሙ 20፥19 2ኛሳሙ 18፥18

✞ ሐውልት በመታሰቢያነቱ ትውፊት አለ። ነገር ግን አሠራሩ በዘመናችን እንደምናየው ያለ አልነበረም። ሐውልትን ብዙ ገንዘብ አወጥቶ በማፍሰስ በዕብነ በረድ በአሸዋና በሲሚንቶ አግዝፈው ቢሰሩት ሐውልቱ ሰውን በመሬት ውስጥ ከሚደርስበት ሙስና መቃብር ማለትም መፍረስና መበስበስ አያድነም። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ሐውልት ከመታሰቢያነቱ አልፎ የሞተውን ሰው በዚህ ምድር እንዳለ አድርጎ ስለሚያሳስብ ፣ ለሚያዩት ሰዎች ዘወትር ሐዘን የሚቀሰቅስ ቁጭዎችን የሚያዘናጋ ትንሣኤ ሙታን እንዳለ የሚያስረሳ ከንቱ መለያ (አፋአዊ ምልክት) ነው። ዘሌ 26፥1 ፣ ማቴ 23፥27

## ፺ ጥበብ ፡

ክርስቲያኖችን ወደ እውነተኛ መንገድ የምትመራና፣ በእውነት ጸንተን እንድንቆም የምታደርገን ጥበብ ናት።



ሰው በጥበብ መልካም የሆነ መንፈሳዊ ተግባራትን መፈጸም አለበት። ይህ የሚሆነው በጥበብ የተመላለስን እንደሆን ነው።

✞ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔር መፍራትነው። ምሳሌ 1፥7፤8፥11፤9፥1 ፣ መዝ 110፥10 ፣ ማቴ 10፥16 ቄለ 4፥5 ሲራክ 1፥14

✞ ጥበበኛ ክርስቲያን ከኃጢአት ፣ ከክፋት ፣ ከከንቱ ሁሉ ይርቃል። ስለዚህ መንፈሳዊ ጥበብ ሊኖረን ይገባል። ጥበቡን እግዚአብሔር የወደደለት ሰው ምስጉን ነው። ምሳ 4፥5 ፣ ዳን 1፥17

✞ ጥበበኛ አስቀድሞ የሚያስፈልገውን የጽድቅ ሥራ እያበራ አምላኩን በትጋት ይጠብቃል። የክብር ሽልማት ይቀበላል። ማቴ 25፥1-13 ፣ ኢዮብ 28፥28 ያዕ 1፥5

✞ ከእግዚአብሔር የተለየ ጥበብ ሁሉ ሞኝነት ነው። ሮሜ 1፥22 ፣ 1ኛቆር 1፥19፤3፥19

✞ የእግዚአብሔር ጥበብ ጥልቅ ነው። እጅግም የተደነቀ ነው። ሮሜ 11፥33 ፣ ቆላ 2፥3 ፣ ኢሳ 11፥2



www.ethiopianorthodox.org

## ፵፩ መሐላ

ማንም ሰው በሐሰት መማል አልተፈቀደለትም

ማቴ 5፥34-37 ዘካ 5፥3

✞ እውነተኛና በቃሉ ታምኖ ለሚኖር ሰው የእንደበት ንግግሩ ብቻ በቂ ነው ፤ ሌላው መሐላ ግን ትርፍ ነገር ነው። ደግሞም በሐሰት መማል የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ ማድረግ ነው። ብዙ ጊዜ በሐሰት መማል የሚመጣው ሐሰትን ልምድ ከማድረግ የተነሣ ነው።

1ኛነገ 8፥32

✞ የእግዚአብሔርን ሥም በምስጋና ማንሳት እንጂ በከንቱ ነገር ማንሳቱ ተገቢ አይደለም።

ዘጸ 20፥7 መዝ 88፥26

✞ ነገር ግን የንግግር መፈጸሚያው የክርክር ማብቂያው የግድ መሐላ ከሆነ ግን መማል ተገቢ ይሆናል።

| | |
|---|---|
| ዘፍ 21፥23 | ሉቃ 1፥73 |
| ዘጸ 22፥11 | ዮሐ 20፥30 |
| ገላ 1፥20 | ዕብ 3፥11 |
| 1ኛተሰ 5፥27 | ዕብ 7፥20 |
| 2ኛቆሮ 11፥31 | ዕብ 6፥13-16 |



## ፵፪ . ክርስቲያናዊ አለባበስ

ክርስቲያን በአለባበሱ በአኗኗሩ ሁሉ ሌላውን የሚሰብክ መሆን አለበት እንጂ ሌላውን የሚያሰናክል አለባበስ ለብሶ ራሱ በፈተና አይወድቅም፡ሌሎች የሚያዩትንም ቢሆን ለፈተና አይጋብዝም:: ጌታችን ለሞተለት ሕዝብ ክርስቲያንም ይጠነቀቃል:: በቸልተኝነት በማይገባ ምኞት ተጠልፎ ዕርቃንን የሚያሳይ አለባበስን አይከተልም::

ምናልባት የምንወደው አይነት አለባበስ ቢኖር እንኳ ነገር ግን ይህ አይነቱ አለባበስ ደግሞ ክርስትናችንን የሚያስንቅፍና ለተመልካች እንቅፋት የሚሆን ከሆነብን በእኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳይወድቅ መተው ይመረጣል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ.3:21 | 1ኛሳሙ.18:4 | ኢሳ.57፥14 | ሉቃ.15፥22 |
| ዘጸ.28:1-5 | 1ኛሳሙ.17:38 | ዘካ.3፥3 | 1ኛቆሮ.8፥13 |
| ዘጸ.22:5 | ምሳሌ.31፥22 | ማቴ.22፥1-14 | 1ኛጢሞ.2፥9 |

## ፵፫ ቸልተኝነት

ሰዎች ሊያደርጉት የሚገባቸውን ነገር በመዘናጋት (ቸል በማለት) አለመፈጸም አለማድረግ ነው:: ብዙ ጊዜ ሰዎች መልካም ሥራን እንዳይሰሩ፣ ንስሐ እንዳይገቡ፣ትዕዛዙን እየፈጸሙ በቃሉ እንዳይኖሩ በሕጉ እንዳይመሩ በልባቸው ቸልተኝነትን የሚፈጥረው ዲያቢሎስ ነው:: ስለዚህ ቸልተኝነት ከክርስቲያኖች ሊርቅ ይገባዋል:: የእግዚአብሔርን የማዳን ጥሪ በቸልታ ልናጣው ወይም ንስሐ መግባት ሲገባን ለሌላ ጊዜ ልናስተላልፈው አይገባም:: ሐዋ.6፥1 1ኛጢሞ.4፥14 ዕብ.2፥3. ሐዋ.24፥25፣26፥27

## ፵፬ . እውነት

እውነት የመገኛዋ ምንጭ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እውነትን የሚወድ ሰው በሌላው ላይ ክፉን ነገር አይሰራም፣ሌላውን አይጐዳም፣አያዳላም፣ በዘመድ(በወገን) ማንንም አያበላልጥም::

በእውነት የሚኖር ሰው ዘወትር በኑሮው፣በትዳሩ፣በሐብቱ፣በሥራው ሁሉ ደስተኛ ነው:: ታማኝ ነው:: ሐሰተኛ ሰው ግን ደስታው ጊዜያዊና ኃላፊ ነው:: የሐሰት ደስታ እውነት እስኪታወቅ ድረስ ብቻ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

«እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል» እንደሚባለው ሁሉ ለጊዜው እውነት የተሸፈነች ብትመስልም እንኳን ምን ቢዘገይ በፍጻሜው ግን ድል አድራጊነት፣ አሸናፊነቱ የእውነት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው::

ኢዮ.24፥14 ሮሜ.2:2 ኤፌ.4:25
መዝ.30፥5 2ኛተሰ.2:9 ኤፌ.5:9
ዮሐ.8፥32 ቲቶ.1:1

## ፺፭ . ሐሰት

ሐሰት ያልተደረገውን እንደተደረገ ፣ ያልሆነውን እንደሆነ ፣ ያልተባለውን እንደተባለ አድርጎ መናገር ነው:: ሐሰት የእውነት ተቃራኒ ነው:: ዓለም በብዙ ሐሰተኞችና ሐሰቶች የተሞላች ናት:: ዓለም እውነትን አይወድም:: ጌታ የተሰቀለውና ለሞት የበቃው በሐሰኞች ነው:: ስለዚህ ሐሰት እውነት እስኪታወቅ ድረስ በሰዎች ላይ ክትዳር ማለያየትን፣ከሥራ ማፈናቀልን፣ማታለልን፣መዋሸትን ማገዳደልን ያመጣል:: ነገር ግን የሐሰተኞች ታላቅነት እውነት ሲመጣ ይዋረዳል:: የሐሰት አባቷ ዲያብሎስ ነው:: የእውነት አባት እግዚአብሔር ነው::

ዘሌ. 19፥11 መዝ. 26፥12 ማር14፥55 ዮሐ. 8፥44

## ፺፮ . ፍቅር

ፍቅር የሕግ ሁሉ መደምደሚያ ማሰሪያ ነው ፍቅር ትልቅ የጽድቅ መሣሪያ ነው:: ፍቅር ከሁሉም ነገር ይበልጣል:: ጠንካራና ጽኑዕ እውነተኛ ፍቅር በጊዜያዊ ችግርና ፈተና አይለወጥም:: ስለዚህ እውነተኛ ፍቅር ከልዑል አምላክ ከእግዚአብሔር የሚገኝ የክርስትና ሃይማኖት መሠረት ነው:: የመላእክትን ቋንቋ እንኳ አውቀን ፍቅር ከሌለን ሁሉም ነገር ከንቱ ይሆንብናል::

ምሳሌ.17፥1 ዮሐ.15፥12-13 ቈላ.3፥14 1ኛቆሮ.13፥13
ማቴ.22፥37 ዮሐ.14፥15 ሮሜ.12፥19 1ኛጢሞ. 1፥5
ማር.12፥28 ማቴ.5፥43 ዮሐ. 13፥33 ገላ. 5፥22
1ኛዮሐ.3፥18 1ኛዮሐ.4፥6 1ኛዮሐ.5፥3



✞ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል::

1ኛጴጥ. 4፥7፤ ምሳ. 10፥12

✞ እግዚአብሔር ዓለሙን ስለወደደ አንድያ ልጁን ለሕማም፣ ለመስቀል ሞት ሰጠ::

ማቴ. 26፥39 ዮሐ. 3፥16 1ኛዮሐ. 3፥16፣ 4፥19
ሮሜ. 5፥8 ኢሳ. 53፥5 ፊልጵ. 2፥8

✞ በዘመነ ሐዋርያት የነበሩ እውነተኛ ፍቅር የነበራቸው ክርስቲያኖች የሚበሉት በአንድ ላይ ነበር:: ይህ የፍቅር ማዕድ አጋፔ/Agape/ ይባላል::

ሐዋ. 2፥44-47 ሐዋ. 4፥32

✞ ፍቅር አይታበይም፣ አይኮራም:: በሌላ ክፉን አያደርግም::

1ኛቆሮ. 13፥4 ሮሜ. 13፥8-10

## ፺፯ . ጸብና ክርክር

እነዚህ ባሉበት ሰላም፣ ፍቅር የለም:: ሀብትንና ውድ ጊዜን ያባክናሉ:: ሀገርን ያነዋውጣሉ፣ ደስታን ያጠፋሉ:: በሃሳብ መለያየትን ይፈጥራሉ:: የሰውን ሰላም ይነጥቃሉ:: ልናርቃቸው ይገባል::

ምሳ.6፥16-19 ሮሜ. 1፥29 2ኛቆሮ. 4፥1
ምሳ.24፥8 ሮሜ. 13፥3 ገላ. 5፥20
ምሳ.28፥25 1ኛቆሮ.1፥10፣ 3፥3 1ኛተሰ. 5፥2
1ኛቆሮ.11፥16 1ኛጢሞ.6፥4 ቲቶ. 3፥9

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

## ፲፰ . ሰላም

ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱና ዋነኛው ሰላም ነው:: ሰላም ከሌለ ደስታ፣ እረፍት እርጋታ የለም:: ሰላም ካለ ሁሉም ነገር ይኖራል:: ሰላም የሐብት የሕይወት የመኖር የፍቅር አለኝታ/መድሕን/ ነው:: ክርስቶስን ለሚከተል ሰው ሰላም አለው:: እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ከልዑል እግዚአብሔር ነው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ.33፥14 | ማቴ.10፥13 | ሮሜ.5፥1 | 1ኛቆሮ.14፥33 |
| መዝ.84፥10 | ሉቃ.1፥79 | ሮሜ.12፥18 | ኤፌ.2፥14-17 |
| መዝ118፥165 | ሉቃ.2፥14 | ሮሜ.15፥33 | ቆላ.1፥20 |
| ኢሳ.57፥21 | ዮሐ.14፥27 | ገላ.5፥22 | 1ኛጴጥ.3፥10 |
| | ዮሐ.20፥19 | | |

## ፲፱ . <u>ትዕግስት</u>

አለመቸኮል ፣ መቻል ፣ የያዙትን እስኪፈጽሙ ድረስ መከራ፣ሐዘን፣ችግርን ሳይመረሩ እስከመጨረሻው መጓዝ ማለት ነው:: አሸናፊነት የሚመጣው በትዕግስት ነው:: በሃይማኖት ለንኖር ትዕግስትን ገንዘብ ማድረግ ይኖርብናል:: ሰማዕታት በደም ጻድቃን በገዳም ታግሰው በመኖራቸው ነፍሳቸውን አድነዋል:: «ትዕግስት መራራ ናት ፥ ፍሬዋ ግን ጣፋጭ ነው::»

| | | |
|---|---|---|
| ኢዮብ.1፥21፤ 42፥10 | ማቴ.10፥22፤ 24፥13 | 2ኛቆሮ.2፥14 |
| ምሳሌ.16፥32፤ 14፥29 | ሉቃ.21፥19 | ገላ.5፥22 |
| መክ.7፥8 | ሮሜ.2፥4፤ 5፥3፤ 15፥5 | 2ኛጴጥ.1፥5-9 |
| | | ያዕ.1፥2፣ 5፥10 |

## ፳ . <u>ትዕቢት</u>

ትዕቢት ከታላቅ ራተና/ከጥልቅ ጉድጓድ/ ለመውደቅ የሚዘጋጁበት የኑሮ መርዝ፣ የኃጢአት ሥር ነው:: ትዕቢት ራስን ከፍ አድርጉ ሌላውን ማዋረድ ነው:: ትዕቢተኛ ሰው ከራሱ ጋር ብቻ የሚነጋገር እንጂ



የሌላውን ምክርና ተግሳጽ የማይሰማ ነው:: ሳጥናኤል ከስልጣኑ የተዋረደው በትዕቢቱ ነው:: ትዕቢት የሚጠፋው በጾምና በጸሎት በስግደት ነው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኢሳ.5፡15 | ዘጸ.9፡17 | ምሳሌ.21፥4 | ሮሜ.12፥3ና16 |
| ኢሳ.13፡11 | 1ኛሳሙ.2፡3 | ማቴ.23፥12 | 2ኛጢሞ.3፥2 |
| ሚል.4፡13 | ምሳሌ.11፡2፣ 8፥13 | ሉቃ.14፥11 | ያዕ.4፥6 |
| መዝ.61፡10 | ምሳሌ.16፡5ና18 | ሮሜ.11፥12 | *1ኛጴጥ.5፥5 |

## ፳፩ . ትሕትና

ራስን ዝቅ ማድረግ፣ ትዕቢትንና ኩራትን ማስወገድ ማለት ነው:: ትሕትና የነፍስ ጸጥታ/እርካታ/፣ ከውዳሴ ከንቱ መዳኛ ናት:: የክርስቲያኖች መታወቂያ ምልክት ትሕትና ናት:: የትሕትና መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በትሕትና መመላለስ ግዴታችን ነው:: ከዚህ የወጣ የትዕቢት ሕይወት ግን መጨረሻው ውድቀት ነው:: «ትዕቢትስ ጸሩ ለክርስቶስ» ይባላል:: ስለዚህ ትሕትና የመንግስተ ሰማይ መውጫ መሰላል ናት::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ.18፡28 | መዝ.118፥141 | ዘኁ.12፥3 | ዮሐ.1፥ 27 |
| ፊልጵ.2፡7 | ሉቃ.1፥35፣ 2፥22 | ምሳሌ.29፥23 | <u>1ኛጴጥ.5፥5</u> |
| 1ኛሳሙ.18፥18 | ምሳሌ.14፥30 | ዮሐ.13፥5 | 1ኛጢሞ.1፥15 |
| መዝ.38፥5 | ማቴ.11፥29 | 1ኛቆሮ.15፥8 | 2ኛቆሮ.4፥7 |

## ፳፪ . ቅንዓት

ቅንዓት የሚመጣ ከምቀኝነት የተነሳ ነው:: ምቀኝነት ሊነቅሉት የሚያስቸግር የኃጢአት ሥር ነው:: ምቀኝነት ካለበት ልብ ውስጥ ብዙ ኃጢአቶች ይበቅላሉ:: ምቀኝነት ሰውን ከጦርና ከረሃብ የበለጠ ይጐዳል፣ ያከሳል፣ ኃይል ያደክማል:: አስተሳሰብን ይቀንሳል:: ቅንዓት ሰውን ውስጥ ውስጡን የሚጐዳ በሽታ ነው:: ስለዚህ ሰው በሌላው ሀብት፣ ማዕረግ፣ ሥራ ቢቀና ቢመቀኝ ክፉ ቅንዓት ነውና ነቅሎ ሊጥለው ያስፈልጋል::

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ.4፥1 | ምሳ.6፥34፣ 14፥30፣ 24፥1 | ማር.7፥22 |
| 1ኛቆሮ. 3፥3 | ገላ.5፥19-22 | ቲቶ.3፥3 |



www.ethiopianorthodox.org

✞ ነገር ግን ለመንፈሳዊ ትንዓት «ለምትበልጠው ጸጋ» ልንቀና ይገባል:: «ቅንዑ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ» ተብለናል:: ለደግ ነገር መቅናት መንፈሳዊነት ነው::

ዘጸ.20÷6　　1ኛነገ.16÷29　　1ኛቆሮ.7÷7፣ 9÷2
ዘዳ.4÷24　　ማቴ.21÷12　　☆1ኛቆሮ.12÷31
ዘዳ.32÷20　　ሐዋ.22÷3　　ገላ.1÷13
ምሳሌ.14÷30

## ፶፫ . <u>ምኞት</u>

ምኞት የኃጢአት ሁሉ ምንጭ ናት:: የሥጋ ምኞት ሰይጣን ሰዎችን ወግቶ ለመግደል የሚወረውራት የመጀመሪያ ትንሽ ጦር ናት:: ዲያቢሎስ የሰውን ሕይወት ቦርቡሮ ለመግል የሚገባበት ትንሽ ቀዳዳ ምኞት ናት:: ክፉ ምኞትን በጊዜው ካላሸነፉት ለበለጠ ክፉ ነገር ያጋልጣል::

ምሳ.21÷26　　ያዕ.1÷1-23　　1ኛዮሐ. 2÷16
1ኛቆሮ.10÷6　　ኤፌ.4÷19፣ 5÷5　　1ኛጢሞ.4÷9

✞ ክርስቲያን ዘወትር መልካም ሊመኝ መልካም ሊሠራ ይገባዋል::

ማቴ.13÷17　　ሮሜ.12÷17　　1ኛጴጥ. 2÷2-3

## ፶፬ . <u>ፈተና</u>

✞ የሰው እምነት እንዲገለጽ የሚመጣ የእምነት መለኪያ ነው::

ዘፍ. 22÷1　　1ኛሳሙ. 17÷39　　ሮሜ. 5÷3

✞ ሰው መልካሙን ፈተና ተፈትኖ ለበለጠ ክብር ራሱን ማዘጋጀት ይገባዋል::

2ኛቆሮ. 13÷5　　1ኛቆሮ. 11÷28



✞ የምንፈተነው የእግዚአብሔርን ፍቅር እንድናውቅ ነው::

ዘፍ. 22፡11　　ሮሜ.5፡3　　1ኛጴጥ. 4፡12፣ 1÷6

✞ የትዕግስትን ፍሬ ለመቅመስ ክብርን ለመጐናጸፍ እንፈተናለን::

ሮሜ.8፡28　　2ኛቆሮ.12፡　　ያዕ.1፡2　　ራእይ.3፡10

✞ ሰዎች በፈቃዳቸው ዲያቢሎስ ሊፈተኑ ይችላሉ::

ዘፍ.3÷1 5　　ኢዮ.1፡9　　1ኛጴጥ. 5÷8
ማቴ. 4፡3　　1ኛተሰ. 3፡5　　ራእይ. 2÷10

✞ ፈተናን የምንወጣውና የምንቋቋመው በጸሎት ኃይል ነው::

ማቴ. 26፡41　　ገላ. 6÷1

✞ የመጣብንን ፈተና ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል መቃወም እንችላለን:: የፈተናውንም መውጫ እግዚአብሔር ያዘጋጃል::

ዘፍ.22፡15　　☆ 1ኛ<u>ቆሮ.10÷13</u>　　ኤፌ.6÷11
ሲራክ 3÷15　　ኤፌ.4÷27

## ፶፭ . ተስፋ

ሰው በእግዚአብሔር አምላኩ ካመነ ተስፋ ይኖረዋል:: ተስፋ ምንጊዜም ቢሆን የሃይማኖታችን ጽናት ውጤት ነው:: ተስፋ በመከራና በችግር ጊዜ እምነትን አጉልቶ ይገልጻል:: ስለዚህ በእግዚአብሔር የሚያምን ሁልጊዜ ባለሙሉ ተስፋ ነው:: ተስፋ የምናደርገው የምናምነውን ግን የማናየውን ነው:: በእምነት የተነሳ የሚያደርጉት ተስፋ አያሳፍርም::

ሮሜ.8÷24　　1ኛቆሮ.13÷13　　ገላ.3÷5　　ዕብ. 6÷17
ሮሜ.12÷12　　1ኛተሰ.13÷5-8　　ቈላ.1÷4　　ያዕ. 2÷23



www.ethiopianorthodox.org

## ፶፮ . ስድብ

አቅም የሌላቸው ደካማ ሰዎች የሚሰነዝሩት ዱላ ነው። ስድብ ከከፍተኛ ኃጢአት የሚጥል የክፋት መንደርደሪያ ነው። ከመሰዳደብ በኋላ መደባደብ፣ መገዳደል ይመጣል። ስለዚህ እንደበታችን ምርቃትን እንጂ ስድብን፣ርግማንን፣ ክፉ መራራ ቃላትን ማሰማት የለበትም። ሰው በስድብ ምክንያት ሊሰረይ የማይችለውን ኃጢአት ይሰራል። ይህም መንፈስ ቅዱስን መሰደብ ነው።

ማቴ. 5፥22-45 ማቴ. 12፥32 /ኤፌ. 4፥29

## ፶፯ . ሐሜት

ሐሜት ማለት ሌላው ሰው ያላደረገውን በሐሰት ስሙን ማጥፋት ነው። ሐሜት ያለ ካራ/ስለት/ ሰውን እንደ ማረድ ስጋውን እንደመብላት ደሙን እንደመጠጣት ነው። ሐሜት ሰውን ለመጉዳት እውነትን በሐሰት፣ጻድቁን በኃጥእ፣ደጉን በክፉ፤ታማኙን በሌባ ለመለወጥ የሚካሄድ ስውር ዘመቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ በጥላቻ አንዳንዴ በልምድ ይፈጸማል። ነገር ግን ከሁሉ የሚከፋው ወዳጅ መስሎ ወንድምን ማማት እንደመግደል ነው። ሰው ለሐሜት ከተሸነፈ የሐሜት ባሪያ ነው። ክርስቲያን ከሐሜት ሊርቅ ሁሉን ሊወድ ይገባዋል።

መዝ.49፥19-20 ምሳሌ.10፥19 ጥበብ.1፥1 ምሳሌ.11፥9
1ኛጢሞ.3፥11 ቲቶ.3፥11 መዝ.100፥5 ሮሜ.1፥2
2ኛጢሞ.3፥16 ማቴ.7፥1 1ኛጴጥ.2፥1 2ኛጴጥ.2፥9
ያዕ.4፥11

## ፶፰ . ይቅር ባይነት

ተበድሎ ቂምና በቀልን ሳይዝ ብድራትን ሳይፈልግ ቢቀር ይቅር ባይ ይባላል።

✞ እግዚአብሔር በንስሐ ለሚመለሱ ይቅርታን ይሰጣቸዋል።

ነህ. 9፥17 ኢሳ. 55፥7፤ 1፥18



✞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰቀሉት ሳይቀር ይቅርታ ለምኗል።
ሉቃ. 23፡34

✞ እኛን እግዚአብሔር ይቅር ካለን እኛም ሌሎችን ይቅር ባዮች መሆን ይጠበቅብናል። ይቅር ብንል ከእግዚአብሔር ይቅርታን እናገኛለን።

ማቴ.6፡12-14፤ 18፥23 ሉቃ.6፥37፤ 17፥4 ኤፌ.4፥32
ቈላ.3፡13 ያዕ. 2፥13
ሉቃ. 3፥13

✞ ብድራት የአምላክ ነውና ይቅር ባዮችን እግዚአብሔር ይወዳቸዋል። ክብርን ይሰጣቸዋል።

ዘፍ. 45፥4-15 ዘዳ. 32፥35 ምሳ. 19፥11 ሐዋ. 7፥6
ሮሜ. 12፥19

## ፶፱ . ቁጣ

ከልባችን እየመነጨ የሚወጣ የኃጢአት መነሻ ምክንያት ነው። ሰው ሲቆጣ ይሳደባል። ሲሳደብ ይማታል፣ሲማታ ይገድላል ስለዚህ ብዙ ሕግ ይተላለፋል፣ያፈርሳል። ቁጣ ፍቅርን ከማጣት፣ባልንጀራን ከመጥላት የተነሳ የሚመጣ የዓመፃ ማሠሪያ ነው። ስለዚህ ቁጡ ሰው ወዳጅ የለውም። ቁጡነትን ማራቅ ያስፈልጋል። ኃጢአትን የሚያስከትል ክፉ ቁጣ እንዳለ ሁሉ መልካምና ተገቢ የሆነ ቁጣም አለ።

### ሀ/ ተገቢ ያልሆነ ቁጣ

ዘፍ.4፥5 መክ.7፥9
2ኛዜና.26፥19 ሮሜ.12፥12
መዝ.36፥5 ኤፌ.4፥31
ምሳ.12፥16፤ 21፥19 ያዕ.1፥19
ምሳ.22፥24፤ 14፥29

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ ተገቢ የሆነ ቁጣ

ዘጸ. 32፥19
ዘኍ.16፥15
1ኛነገ.19፥10
ነህ.5፥6
ኤፌ.4፥26

## ፳ . ጉቦኝነት

ጉቦ ፍርድ እንዲጓደል፣ድሀ እንዲበደል ተደርጐ የሚሰጥ መማለጃ ነው:: ጉቦ እውነትን ወደ ሐሰት ይለውጣል:: ሰዎችን ከስነምግባር ውጭ ያደርጋል:: አድሉአዊነትን በሰዎች መካከል ያሰፍናል:: ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲተላለፍ ያደርጋል::

| | | |
|---|---|---|
| ዘጸ.23፥8 | 1ኛሳሙ.8፥3 | መክ.7፥7 |
| ዘዳ.10፥17 | 1ኛሳሙ.12፥3 | ኢሳ.33፥15 |
| ዘዳ.16፥19 | መዝ.25፥10 | አሞጽ. 5፥12 |

## ፳፩ . ገንዘብ

ገንዘብ በዚህ ዓለም ከተጠቀሙበት ብዙ ደግ ሥራ የሚሠራበት ነው:: ደግሞ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ብዙ ኃጢአት ይሠራበታል:: ገንዘብን በአግባቡ ሲይዙት ለሥጋም ለነፍስም ይጠቅማል::

ካልተጠቀሙበት ግን ገንዘብ የኃጢአት ሥር ነው:: የሥጋና የነፍስ ሞት ያመጣል ፤ ፍቅረ ንዋይ ካለብን እንዋሻለን ፣ እንሰርቃለን እናታልላለን ፣በሐሰት እንምላለን ፣ ፈጣሪያችንን እንክዳለን:: ገንዘብ እኛን እያዘዘን ሲሄድ ደግሞ ገንዘብን በክህደት እንፈልገዋለን:: ምንጊዜም ገንዘብን እናስባለን::በዚህም ገንዘብን ወደ



ማምለክ እንሄዳለን:: መገዛትና ማምለክ እግዚአብሔርን ነው እንጂ በገንዘብ ፍቅር የተነሳ የእግዚአብሔርን ፍቅር ልንለውጥ አይገባም:: ሠርተን ባገኘነው ገንዘብ ለመጠቀም እግዚአብሔርን ጋሻና ረዳት አድርገን በፍቅረ ንዋይ (በገንዘብ ፍቅር) የሚመጣ ኃጢአትን መዋጋት ያስፈልጋል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ37፡28 | 2ኛነገ5፡15 | ማቴ6፥14-21 | ሉቃ8፥3 |
| መሳ9፡4 | ሲራክ5፥1 | ማቴ19፥15 | ሉቃ12፥13 |
| መዝ48፡6 | ሲራክ11፥24 | ማቴ26፥15 | ሐዋ5፥1 ፤ 8፥18 |
| መዝ118፡72 | ሲራክ34፥3-10 | ማቴ27፥3 | 1ኛጢሞ6፥6-17 |

## ፳፪. ልብ

እግዚአብሔር አምላካችን በንስሐ የተለወጠውን ልብ ይወዳል:: እኛ ለአምላካችን ልንሰጠው የሚገባ ታላቅ ስጦታ ልባችንን ነው:: ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የተሰበረ ልብ ያስፈልጋል:: ልባችን ዘወትር ቃሉን ለመስማት የተከፈተ፡ በእምነት የጸናና የበረታ መሆን አለበት::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ6፥5 | መዝ72፥1 | ኢሳ57፥15 | ሐዋ2፥46 |
| ዘጸ35፥5 | ምሳሌ3፥3 | ኤር31፥33 | ሐዋ13፥22 |
| ዘዳ6፥6 | ምሳሌ4፥23 | ሕዝ11፥19 | ሐዋ16፥14 |
| 1ኛሳሙ10፥9 | ምሳሌ12፥20 | ኢዩ2፥12 | ሮሜ6፥17 |
| 1ኛሳሙ16፥7 | ምሳሌ14፥30 | ማቴ5፥28 | ሮሜ10፥10 |
| 1ኛነገ8፥58 ፤14፥8 | ምሳሌ20፥9 | ማቴ22፥37 | 2ኛቆሮ1፥22 |
| መዝ7፥10 | ምሳሌ23፥12 | ማር12፥30 | ኤፌ3፥17 |
| *መዝ50፥10 | *ምሳሌ23፥26 | ሉቃ16፥15 | 1ኛዮሐ3፥19 |

## ፳፫. መጠጥ /የስካር አስከፊነት/

መጠጥ በጊዜያዊ ደስታ ዘላለማዊ ጸጸትና ኃዘን ጥሎ የሚያልፍ የሰው ልጆች ጊዜያዊ ወዳጅ ነው:: በመጠጥ ኃይል /በስካር መንፈስ/ ተገፋፍቶ ኃጢአትን መስራት ለከፋ በሽታ፥ ለጤና መታወክ ይዳርጋል:: ስካር ኃይለኛውን ደካማ፥ ብርቱውን ሰነፍ፥ ክቡሩን ወራዳ ያደርጋል:: ስካር ኃጢአትን ሁሉ በያይነቱ ደርድሮ የሚያሰራ ነው:: ስለዚህ



www.ethiopianorthodox.org

በመዝ 104፥15 ፤ 1ኛ ጢሞ 5፥23 በመድኃኒትነት ትንሽ ወይን እንዲጠጣ አዘዘ እንጂ ጠጪነትን ለማበረታታት አይደለም። በመሆኑም አብዝቶ መጠጣት ኃላፊነትን ያስረሳል። የጽድቅን መንገድ ያስታል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ9፥20 | 2ኛሳሙ11፥13 | ኢሳ5፥11 | ሉቃ21፥34 |
| ዘፍ19፥30 | ምሳሌ20፥1 ፤ 21፥29 | ኢሳ5፥22-25 | 1ኛቆሮ5፥18 |
| ዘዳ21፥20 | ምሳሌ23፥20 ፤23፥29 | ሆሴዕ4፥11 | ገላ5፥21 |
| 1ኛሳሙ25፥36 | 2ኛመቃ15፥40 | ሲራክ34፥24 | ኤፌ5፥18 |

## ፳፬. መዝሙር

- መዝሙር ለአምላክ የሚቀርብ የምስጋና መስዋዕት ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘጸ15፥20 | ኢሳ12፥2 | ኤፌ5፥19 | ማቴ26፥30 |
| መዝ91፥1 | ኢሳ42፥10 | ቈላ3፥16 | |

✞ ሰዎች በአገልግሎት ከመላእክት ጋር የሚመሳሰሉት በመዝሙር ነው። መዝ102፥20 ፤ ኢሳ6፥3 ፤ ራእይ4፥8 ፤ ሉቃ2፥13

✞ መዝሙር ለእግዚአብሔር ስናቀርብ ከልብ በማስተዋል ይሁን። መዝ46፥7

✞ ከእግዚአብሔር ከሚሰጡ የጸጋ ስጦታዎች አንዱ መዝሙር ነው፡ 1ኛቆሮ14፥26 ፤ ቈላ3፥16 ፤ መዝ39፥3

✞ ቅ/ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በገና ሲመታ ከንጉሡ ሳዖል ክፉ መንፈስ ይርቅ ነበር። 1ኛ ሳሙ 26፥26

✞ ቅ/ጳውሎስና ሲላስ ሲዘምሩ የእስር ቤቱ መሠረት ተናውጿል፤ ሠንሰለቱ ተበጥሷል። ሐዋ 16፥25 ፤ ያዕ5፥13

✞ የመዝሙር መሣሪያዎች የሚባሉት፦ ጸናጽል፡ መቋሚያ፡ ከበሮ፡ በገና፡ ክራር፡ መሰንቆ፡ ዋሽንት፡ እምቢልታ፡ መለከት ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| መዝ70፥22፤ 97፥5 | 1ኛሳሙ16፥16፤ 18፥6 | ኢዮ1፥12፤30፥3 |
| መዝ56፥8፤ 149፥3 | 1ኛዜና15፥16-21 | ዳን3፥5 |
| መዝ150፥1፤ 91፥3 | ዘፍ4፥21 | ራእይ5፥8 |
| ሕዝ28፥13 | አሞጽ 6፥5 | ማር14፥26 |



## ፳፭. ሕመም

ሕመም በሰው ላይ የሚመጣው ለክብር ማለትም የአምላክ ሥራ በእኛ ላይ እንዲገለጥ ወይም ደግሞ እግዚአብሔርን ካለመፍራት የተነሳ ለቅጣት የሚመጣ ሊሆን ይችላል።

| | | |
|---|---|---|
| ዘዳ 28፥58 | ኤር 15፥18 | ዮሐ 11፥4 |
| ኢዮ 1፥21 | ዳን 8፥28 | |

✞ እግዚአብሔር ለሕመምተኞች ፈውስ ማድረግ ይቻለዋል።
መዝ 40፥3 ማቴ 4፥23 ማቴ 8፥14-17
መዝ 102፥3 ሉቃ 7፥11 ማቴ 9፥18

✞ ሕመምተኞች የሆኑ ሁሉ መድኃኒት ያስፈልጋቸዋል። ይኸውም የዘላለም ሕይወት የሚሰጠው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። ያመኑ ሁሉ ይድናል።
ማቴ 9፥12 ዮሐ 6፥53 ማር 9፥23

✞ ለእግዚአብሔር ካለመታዘዝና በኃጢአት በመኖር የተነሣ ፈውስ የሌለው ለሞት የሚያደርስ በሽታ ይላካል።
ዘሌ 26፥14 ዘዳ 28፥27 2ኛ ሳሙ 12፥16
2ኛ ዜና 20፥1

✞ በኃጢአት መኖር በበሽታ ይመሰላል። ኢሳ 1፥4-6

✞ ሕመማችን ልንፈተንበት የተላከ ጸጋ ልናገኝበት ሊሆን ይችላል።
ኢዮ 2፥1-9 ሉቃ 13፥16

✞ ለሕመምተኞች መጸለይ ይገባል።
መዝ 34፥13 ኢሳ 38፥1-9 ማር 6፥13 ያዕ 5፥14

✞ በሽተኞችን መጠየቅ መጎብኘት ይገባናል።
1ኛ ሳሙ 30፥11 ማቴ 25፥34 ሉቃ 10፥33

✞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ ደቀመዛሙርትና ለአገልጋዮቹ ቅዱሳን የመፈወስ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። ዛሬም በቅዱሳን መካናት በሚገኙ ጸበሎች ፈውስ ይደረጋል።

| | | |
|---|---|---|
| ዘኁ 12፥1 | ማቴ 10፥1 | ሐዋ 9፥32 |
| 1ኛነገ 17፥17 | ሐዋ 2፥43 | ሐዋ 19፥11 |
| 2ኛነገ 4፥32 | ሐዋ 3፥8 | |



www.ethiopianorthodox.org

✞ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕሙማንን በተለያየ ዓይነት መንገድ ፈውሷል። ይኸውም:-

1. በቃሉ በመናገር ⇨ ማቴ 8÷17 ፤ ማር 2÷5
2. በእጁ በመዳሰስና እጁን በመጫን ⇨ ማቴ 8÷15 ፤ ማር 5÷13 ፤ ማር 6÷5
3. የልብሱን ጫፍ በመዳሰስ ⇨ ማቴ 14÷36 ፤ ሉቃ 8÷44
4. ጭቃን በመቀባት ⇨ ዮሐ 9÷6
5. ያለ ምንም መናገርና መዳሰስ በሃሳብ ብቻ ⇨ ዮሐ 2÷1-11 ፤ ዮሐ 4÷50

## ፳፮. <u>ቃል ኪዳን</u>

እግዚአብሔር ለተመረጡ ቅዱሳን ቃል ኪዳን ያደርጋል። ቃል ኪዳኑንም አይረሳም። መዝ 88÷3 እና 34 ፤ መዝ 110÷5 ፤ ሕዝ 34÷25 ፤ 2ኛሳሙ 23÷5 ፤ ኢሳ 54÷10

✞ አምላክ በሚያደርገው ቃል ኪዳን ምልክትን ይሰጣል። ዘፍ 2÷8 ፤ 9÷17 ፤ 17÷21
✞ አምላክ ቃል ኪዳኑን አስቦ ሰዎችን ይምራል። ይራራልናል። 2ኛነገ 13÷23 ፤ መዝ 104÷42 ፤ ኤር 14÷21 ፤ ዳን 9÷4
✞ ሰዎች እርስ በርሳቸው ቃል ኪዳንን ያደርጋሉ። 1ኛሳሙ 18÷2
✞ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለዘላለም ነው። ዘፍ 17÷13 ፤ ኢሳ 55÷3 ፤ 59÷21 ፤ 61÷8 ፤ ሕዝ 37÷26
✞ የቅዱሳን ቃል ኪዳናቸው አይረሳም። ዘዳ 4÷31 ፤ 1ኛነገ 8÷23፤ መዝ 104÷8 ፤ ሉቃ 1÷73
✞ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቁና የሚታዘዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን በረከት ይቀበላሉ። ዘጸ 19÷5 ፤ ዘጸ 24÷7 ፤ መዝ 54÷20 ፤ መዝ 102÷18 ፤ 131÷12 ፤ ኢሳ 56÷4 ፤ ሕዝ 16÷59-63
✞ የተቀደሱ ቦታዎች የማዳን ቃል ኪዳን አላቸው። ነህምያ 1÷8-9 ፤ ሕዝ 34÷25-26
✞ ቃል ኪዳኑን መናቅ፥ መቃወም አይቻልም። ኤር 33÷20 ፤ ምሳ 2÷17 ፤ 2ኛነገ 17÷38 ፤ ገላ 3÷15 ፤ ኢሳ 24÷5
✞ ጌታ በዘመነ ሐዲስ የፈፀመው ኪዳን አዲስ ኪዳን ይባላል። ዕብ 8፡8 ፤ ኤር 31÷31 ፤ ማቴ 26÷27 ፤ ሉቃ 22÷20 ፤ 1ኛቆሮ 11÷25



## ፳፯. <u>ሰላምታ</u>

ሰላምታ ሰዎች በሚገናኙበት ጊዜ የሚሰጣጡት፥ የሚለዋወጡት የስሜት መግለጫ ነው።

✞ ሰላምታ በመሳሳም --ማቴ 26÷49 ፤ ሮሜ 16÷16 እጅ ለእጅ በመጨባበጥ-- ገላ 2÷1 ይፈፀማል።
✞ መልእክቶቻቸውን ሲጽፉ በሰላምታ የጀመሩና የፈጸሙ ቅዱሳን ሐዋርያት አሉ። ሮሜ 1÷1-7 ፤ 16÷21-23 ፤ ዕብ 13÷24
✞ ሰዎች ሲገናኙ የሚለዋወጡት የሰላምታ ቃል፥ የንግግር መጀመሪያ ልክ እንደ ጌታ ሰላም የሚል ነው። ዮሐ 20÷19
✞ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ለብስራት ሲመጣ ሰላምታ አቀርቧል። እመቤታችንም በሰላምታው ተገረመች። ሉቃ 1÷28-29 ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ሰላምታ ስትሰማ ጽንሱ በማህፀንዋ ዘለለ፥ መንፈስ ቅዱስም ሞላባት። ሉቃ 1÷41-44
✞ ወደ ቤት ሲገባ ሰላምታ ማቅረብ ይገባል። ማቴ 10÷12
✞ ይሁዳ ጌታን በመሳም ሰላምታ ሰጥቶ አሳልፎ ሰጠ። ማቴ 26÷49
✞ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ለማይቀበል ሰላምታ አይገባም። 2ኛ ዮሐ 10
✞ ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው በተቀደሰ አሳሳም በፍቅር ሰላምታ መስጠት ይገባቸዋል። ሮሜ 16÷16፤ ፊልጵ 4÷21፤1ኛጴጥ 5÷14

## ፳፰. <u>ደስታ</u>

እውነተኛ የሕይወት ደስታ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው። ነህ 8÷10 ፤ መዝ 50÷8 ፤ ዮሐ 15÷11 ፤ ሮሜ 15÷13

✞ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ ነው። ገላ 5÷22 ፤ ሮሜ 14÷17
✞ በእውነት መንገድ ከመሄድ የበለጠ ደስታ የለም። 3ኛ ዮሐ 3
✞ በመከራና በኀዘን ሕይወት ውስጥ ከኋላ ደስታና ሐሴት ይገኛል። መዝ 125÷5 ፤ 29÷5 ፤ ኢሳ 35÷10 ፤ 61÷3 ፤ 2ኛቆሮ 7÷4 ፤ 2ኛ ቆሮ 8÷2 ፤ 6÷10
✞ የክፉዎች ደስታ አጭርና ጊዜያዊ ነው። ኢዮብ 20÷5
✞ ለጊዜው በሚመጣ ትንሽ ቅጣት ታግሠን ደስታ እንቀበላለን። ዕብ 12÷11፤ 2ኛቆሮ 12÷9፤ ያዕ 1÷2፤ 1ኛጴጥ 1÷8 ፤ ይሁዳ 24



www.ethiopianorthodox.org

- ✞ ሰው ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ሊለው ይገባል። ፊልጵ 4፥4 ፤ 1ኛ ተሰ 5፥16
- ✞ ለእግዚአብሔር በደስታ መገዛት ስሙንም ማመስገን ይገባል። መዝ 62፥5 ፤ መዝ 99፥1

## ፳፱. መከራ

በዚህ ዓለም የሚኖሩ ክርስቶስን የሚከተሉ የዓለም ብርሃናት የሆኑ ሰዎች መከራን ሊቀበሉ የግድ ነው። ክርስቶስ መከራን ተቀብሏልና። ዮሐ 16፥33 ፤ ፊልጵ 1፥29 ፤ 2ኛ ጢሞ 2፥9 ፤ ዕብ 13፥12 ፤ 1ኛጴጥ 5፥9-10

- ✞ በኃይማኖት የተነሳ የሚመጣ ፈተና ለክብር ነውና በደስታ መቀበል እንጂ እንድንማረር አይገባም። ሮሜ 5፥4 ፤ 1ኛ ጴጥ 4፥13-19 ፤ ራእይ 2፥10
- ✞ መከራ በኃጢአት ምክንያትም የሚመጣ ሊሆን ይችላል። ምሳ 22፥8 ፤ ሮሜ 2፥9 ፤ ገላ 6፥7 ፤ ራእ 2፥22
- ✞ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በሰይጣን መከራ ይመጣባቸዋል። ኢዮብ 1፥12
- ✞ መከራ ይመክራል። ሰዎችን ከክፉ ስራቸው እንዲመለሱ፥ እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች እንዲያውቁት ያደርጋቸዋል። ምሳ 3፥11-12 ፤ ዳን 4፥37
- ✞ እውነተኛ ክርስቲያን መከራን ሁሉ በደስታ ይቀበላል። በትዕግሥትም ያሳልፈዋል። ዘፍ 35፥3 ፤ መዝ 9፥9 ፤ 45፥1 ፤ መዝ 53፥7 ፤ 2ኛቆሮ 1፥4-7 ፤ 7፥5-7
- ✞ በመከራ ጊዜ እግዚአብሔር ይረዳናል፥ ያጽናናናል። ሲራክ 2፥1-18
- ✞ መከራ ለጊዜው ነው ያልፋል። ግን የማያልፍ የእግዚአብሔርን ክብር ያስገኛል። 2ኛቆሮ 4፥16-18 ፤ 2ኛጢሞ 1፥9 ፤ ዕብ 11፥25፤ 1ኛ ጴጥ 1፥11፤ 1ኛ ጴጥ 2፥19-21 ራእይ 7፥14
- ✞ መከራ ሲገጥመን መጸለይ ይገባል። ያዕ 5፥13

## ፴. ሕልም

ሰው ተኝቶ ሳለ በእንቅልፍ ጊዜ የሚያየው ነገር ነው።

- ✞ በቀን የታየና የታሰበ ነገር በመኝታ ሊታለም ይችላል። መክ 5፥3
- ✞ እግዚአብሔር ለነቢያት፥ ለወዳጆቹ በሕልም ፈቃዱን ይገልጽላቸው፥ ያነጋግራቸው ነበር። ዘፍ 20፥3 ፤ ዘፍ 30፥11 ዘኁ 12፥6 ዘፍ 28፥12 ፤ ዘፍ 37፥5 1ኛነገ 3፥5 ማቴ 1፥20
- ✞ ሕልም የመተርጎም ስጦታ ለተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ነው። ዘፍ 40፥8 ፤ 41፥15 ፤ ዳን 2፥26 ፤ 4፥5
- ✞ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መልካም ሕልምን ሊያልሙ ይችላሉ። ኢዩኤል 2፥28 ፤ ሐዋ 2፥17
- ✞ አንዳንድ ጊዜ ግን ሕልም ሰዎችን ሊያስት ይችላል። ዘዳ 13፥1-5

## ፴፩. ራእይ

ሰው ሳያንቀላፋ በተመስጦ የሚያየው ነገር ነው። ራእይና ሕልም ይለያያል። ራእይ በተመስጦ ነው። ሐዋ 10፥10 ፤ 11፥5

- ✞ ራእይ እግዚአብሔር ለመረጣቸውና ላደረባቸው ሰዎች ይገለጣል። ዘፍ 15፥1 ሕዝ 1፥1 ዳን 7፥7 ዘኁ 12፥6 ዳን 2፥19 ኢዩ 2፥28 ሐዋ 2፥17
- ✞ እግዚአብሔር በራእይ ለነቢያት፥ ለሐዋርያት፥ ለወዳጆቹም ተገልጧል። ሉቃ 1፥22 ሐዋ 10፥3 ሐዋ 18፥9 ራእ 1፥17 ሐዋ 9፥11፤ ሐዋ 10፥10-23 ራእ 4፥1
- ✞ ነቢያት በእስራኤል ዘንድ "ባለራእይ" ተብለው ይጠሩ ነበር። 1ኛ ሳሙ 9፥9 አሞጽ 7፥12
- ✞ ራእይ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ቀድሞ ያስታውቃል፥ ቢዘገይም ግን ይፈፀማል። ዕን 2፥2 ፤ ሐዋ 9፥10



www.ethiopianorthodox.org

## ፳፱. ተአምር

ተአምር የድንቅ ነገር ምልክት ነው።

- ✞ የማያምኑ ሰዎች እንዲያምኑ ምልክት ይደረግላቸዋል። ዘጸ 7፥3 ፤ ዘዳ 34፥11
- ✞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረጋቸው ብዙ ድንቅ ምልክቶች አሉ። ዮሐ 2፥11 ፤ 3፥2 ፤ 4፥54 ፤ ሐዋ 2፥22
- ✞ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን በሰማይና በምድር ቢሆን በድንቅ ተአምራት ያድናል። ዳን 6፥27
- ✞ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ተአምራት ማድረግ ነው። 1ኛቆሮ 12፥10 እና 28
- ✞ ሐዋርያት በጌታ ስም ድንቅ ምልክትን እያደረጉ ይፈውሱ ነበር። ማር 16፥20 ፤ ሐዋ 4፥5-22 ፤ 5፥12 ፤ 6፥8
  <u>ለምሳሌ</u> :- ቅ/ጴጥሮስ በጥላው (ሐዋ 5፥12-16) ቅ/ጳውሎስ በልብሱ ጫፍ (ሐዋ 19፥11) ይፈውሱ ነበር።
- ✞ ጌታ አምላክ መሆኑን ሳያምን ተአምር ማድረግ የሚቻለው የለም። ማር 9፥39
- ✞ ምልክትን ካላዩ የማያምኑ አሉ። ሉቃ 23፥8 ፤ ዮሐ 4፥48 ፤ 1ኛቆሮ 1፥22
- ✞ ክርስቲያን ተአምር ብቻ የሚፈልግ በምልክት ብቻ የሚለወጥ መሆን የለበትም። ማቴ 12፥39 ፤ 16፥4 ፤ ሉቃ 11፥29 ፤ ራእ 13፥13

## ፴. ቃል

ሀ/ ኢየሱስ ክርስቶስ አካላዊ ቃል ነው። ዮሐ 1፥1-14፤ ራእ 19፥13
እግዚአብሔር ዓለምን በቃሉ ፈጠረ። ዘፍ 1፥3 ፤ መዝ 32፥6 ፤ ዕብ 11፥3

ለ/ የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም። ዘላለማዊ ነው። ኢሳ 40፥8፤ ኢሳ 55፥11 ፤ ማቴ 24፥35 ፤ ዕብ 4፥12 ፤ 1ኛጴጥ 1፥25

- ✞ የእግዚአብሔር ቃል የሕይወት መብራት ነው። መዝ 118፥105 ፤ 1ኛጴጥ 1፥19
- ✞ የሕይወት ምግብ እና መጠጥ ነው። ማቴ 4፥4 ፤ ዮሐ 4፥13፤ ዮሐ 7፥37
- ✞ ቃሉ እውነት ነው። መዝ 118፥140 ፤ ዮሐ 17፥17
  ቃሉን እንራባለን። አሞጽ 8፥11-12
- ✞ የእግዚአብሔር ቃል በእሳትና በመዶሻ (ኤር 23፥29) በመንፈስ ሰይፍ (ኤር 6፥17) በወተት (1ኛጴጥ 2፥2) ተመስሏል።
- ✞ ቃሉ ዲያብሎስን የምናሸንፍበት ጦርና ጋሻ ነው። መዝ 17፥30

ሐ/ የሰው ልጆች ቃል መግባቢያ፣ የሃሳብ መግለጫ ነው።
ሰው በቃሉ ይታወቃል፤ በንግግሩ (በቃሉ) የተነሳ ይፈረድበታል። ማቴ 12፥37

## ፴፩. ኢትዮጵያ

- ✞ የአባይ ወንዝ መነሻ ሀገር ናት። ዘፍ 2፥13
- ✞ በእምነትም ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላት ናት። መዝ67(68)፥31
- ✞ በማዕድን እጅግ የከበረች ሀገር ናት። ኢዮብ 28፥19
- ✞ ስለ ኢትዮጵያውያን መልክና ቁመት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል፡ ኤር 13፥23 ፤ ኢሳ 45፥14
- ✞ ስለ ኢትዮጵያ መልክዐ ምድር አቀማመጥም ተገልጿል። ሕዝ 29፥10
- ✞ ስለኢትዮጵያዊቷ ንግስተ ሳባ ብዙ የተገለጹ አሉ። 1ኛነገ10፥1-13፤ 2ኛዜና9፥1-12፤ ማቴ12፥42፤ ሉቃ11፥31

## ✞ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ 2÷13 | መዝ 67÷31 | ኤር 38÷7 | ዕን 3÷7 |
| ዘኅ 12÷1 | መዝ 71 ÷9 | ኤር 38÷10 | ሶፎ 2÷12 |
| 2ኛነገ 19÷9 | መዝ 73÷14 | ኤር 38÷12 | ሶፎ 3÷10 |
| 2ኛዜና 12÷4 | መዝ 86÷4 | ኤር 39÷16 | ሐዋ 8÷27 |
| 2ኛዜና 14÷9 | ኢሳ 11÷11 | ኤር 46÷9 | ዮዲት 1÷10 |
| 2ኛዜና 14÷12 | ኢሳ 18÷1 | ሕዝ 29÷10 | አስ 3÷1 |
| 2ኛዜና 14÷13 | ኢሳ 20÷3 | ሕዝ 30÷4 | አስ 3÷12 |
| 2ኛዜና 16÷8 | ኢሳ 20÷4 | ሕዝ 30÷5 | አስ 7÷1 |
| 2ኛዜና 21÷16 | ኢሳ 20÷5 | ሕዝ 30÷9 | አስ 7÷9 |
| አስቴር 1÷1 | ኢሳ 37÷9 | ሕዝ 38÷5 | 1ኛመቃ 25÷9 |
| አስቴር 3÷12 | ኢሳ 43÷3 | ዳን 11÷43 | 1ኛመቃ 28÷38 |
| አስቴር 8÷9 | ኢሳ 45÷14 | አሞ 9÷7 | 1ኛመቃ 34÷2 |
| ኢዮብ 28÷19 | ኤር 13÷23 | ናሆ 3÷9 | 1ኛመቃ 34÷9 |
| | | | ተረፈ ኤር 8÷8 |

## ፸፰. በጸጋው መዳን ማለት ምን ማለት ነው?

ጸጋ ማለት ስጦታ፥ ቸርነት፡ በጎነት፥ምሕረት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ያለዋጋ በነፃ የሚገኝ የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተለያየ ጸጋ ይሰጣል፡፡ ሮሜ 12÷6

ቅዱስ ጳውሎስ " በጸጋ ድናችኋል፡ . . . ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፡ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡" ኤፌ2÷4-9 ሲል የክርስቶስን ሕማም ሞት፥ በቀራኒዮ አደባባይ፡ በመስቀል ላይ የፈጸመውን የቤዛነት፥ የፍቅር፥ የማዳን ሥራ የሚገልጽ ነው፡፡ ሮሜ 3÷23፡፡ እኛ ጠላቶቹ ሳለን እሱ ግን በፍቅሩ ታላቅነት ፡ በምሕረቱና ቸርነቱ ፍጹም አዳነን፡፡ ሮሜ 5÷10



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ያዳነን በቸርነቱ ነው እንጂ፥ እኛ በሥራችን የዳንን አይደለም ሲል ነው እንጂ በጎ ምግባር አያስፈልግም አልተባልንም፡፡ ሰው በጎ ምግባር ሳይሰራ በእምነት ብቻ ወይም እምነት ሳይኖረው በምግባር ብቻ ሊድን አይችልም፡፡ ያዕ 2÷17 እምነት የሚገለጠው በመልካም ሥራ ነው፡፡ ያዕ2÷26 ፤ ዮሐ 5÷29

በመሆኑም የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ መልካም ሥራ የሚመራ እንጂ በጎ ተግባርን የሚፃረር አይደለም፡፡ በጎ ስራን ሠርቶ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ልንመካበት /ልንመጻደቅበት/ አይገባም፡፡ ሉቃ 1÷28፤ ሐዋ 20÷32 ፤ ሮሜ 5÷6 ፤ ኤፌ 3÷8 ፤ ቲቶ 2÷11 ፤ 2ኛጢሞ 1÷5-8 ፤ ዕብ 13÷9

ስለዚህ በጸጋው ድነናል እያሉ ያለ መልካም ሥራ ያለቱሩፋት መቀመጥ አይገባንም፤ ሕጉን ትእዛዙን ፈጽሞ መገኘት ነው፡፡ የወንጌልን ቃል መጠበቅ፥ በጥምቀት ያገኘነውን የልጅነት ጸጋ አክብረን መያዝ፥ የእግዚአብሔርን መንግስት /መንግስተ ሰማያትን/ በተስፋ መጠባበቅ ይኖርብናል፡፡

ሮሜ8÷1 ፤ 12÷6 2ኛቆሮ 9÷14 ፤ 12÷9 ይሁዳ 4
ዕብ 4÷16 2ኛጢሞ 1÷9 ፤ 2÷1

## ፸፱. አዋልድ መጻሕፍት

አዋልድ መጻሕፍት -ማለት የመጻሕፍት ልጆች ማለት ነው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወለዱ፥ የተገኙ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ተከትለው የተጻፉ፥ ምንጫቸውና መገኛቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነውና አዋልድ ተብለዋል፡፡ አዋልድ መጻሕፍት ለመገኛቸው፥ ለዋና ምንጫቸው መጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ናቸው፡፡ አዋልድ መጻሕፍት በውስጣቸው የያዙት ቃለ እግዚአብሔርን በመሆኑ ቀጥራቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ከ81ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ያልወጡ በመሆናቸው አዋልድ መጽሐፍትን ቤተክርስቲያን አክብራ ትቀበላቸዋለች፡፡

ምሳሌ፦ ሃይማኖተ አበው፣ ግብረ ሕማማት፣ ገድላት፣
ድርሳናት፣ ተአምራት፣ ቅዳሴያት፣ ጸሎታት ...
ወዘተ ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ኢዮብ 10፥13 | 2ኛነገ 10፥34 | ዮሐ 21፥20 |
| 2ኛሳሙ 1፥18 | 2ኛነገ 12፥20 | ሮሜ 15፥4 |
| 1ኛነገ 11፥41 | 2ኛዜና 9፥29 | ገላ 1፥8 |
| 1ኛነገ 14፥19 | 2ኛዜና 12፥15 ፤ 13፥22 | 1ኛጢሞ 3፥14 |
| 1ኛነገ 16፥5 | 2ኛዜና 20፥34 ፤ 24፥27 | * 2ኛጢሞ 3፥16 |

## ፳፮. 666 (አውሬው ማነው?)

በመጨረሻው የዓለም ፍጻሜ ዋዜማ ላይ የሚነሳ፣ ብዙዎችን የሚያስት፣ በሰው መጠን ልክ ሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት ያለው ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት (666) ጅማቶች (አውታሮች) ያሉት የዕለተ ዓርብ ሰብዓዊ ፍጡር ነው። ከባሕር የሚወጣና ሥራውም ክፉ ስለሆነ አውሬ ተብሏል። አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች አሉት። የእግሮቹ ጣቶች ጠማማዎች ናቸው።

እኔ ክርስቶስ ነኝ እያለ ሐሳዊ መሲህነቱን ያውጃል። እግዚአብሔርንና የአምላክ ማደሪያዎችን ቅዱሳንን፣ አብያተ ክርስቲያናትን፣ ቤተክርስቲያንን ይሳደባል። ይህ ሐሳዊ መሲህ (መጪው አውሬ) 42 (አርባ ሁለት) ወራት ማለትም ሶስት ዓመት ከመንፈቅ በምድር ላይ ብዙዎችን በምትሐታዊ ሥራው እያሳተ ይቆያል።

ዛሬም በዘመናችን ከተነሱት የአውሬው መንገድ ጠራጊዎች ከሃዲዎች ልንጠበቅ ያስፈልጋል።

| | | |
|---|---|---|
| ዳን 8፥23 ፤ 9፥26 | ማቴ 24፥23 | ራእይ 13፥1-18 |
| ዳን 11፥36 | 2ኛተሰ 2፥1-5 | ራእይ 14፥9 |

## ፳፯. ጸሎተ ሃይማኖት

ሠለስቱ ምዕት (318) ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን መናፍቁ አርዮስን ለማውገዝ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ተሰብስበው የወሰኑት የሃይማኖት መግለጫ ፦

1. ሁሉን በያዘ፣ ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር እናምናለን።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ 1፥1 | ነህ 9፥6 | ኤፌ 4፥6 | ራእይ 1፥8 |
| ዘጸ 20፥3 | ኢሳ 64፥8 | 1ኛቆሮ 8፥6 | |
| ዘዳ 6፥4 | ማቴ 3፥16 | 1ኛጢሞ 6፥14 | |
| መሳ 6፥21 | ዮሐ 14፥25 | ኤፌ 3፥16 | |

2. ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድያ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።

| | | |
|---|---|---|
| መዝ 2፥7 | ዮሐ 3፥14 | 1ኛቆሮ 8፥6 |
| መዝ 109፥3 | ሐዋ 16፥31 | ፊልጵ 2፥10 |

3. ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ የባሕርይ አምላክ የተገኘ አምላክ፣ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ በባሕርዩ ከአብ ጋር የሚተካከል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኢሳ 9፥2 | ዮሐ 1፥1፤ 10፥30 | ዮሐ 14፥9 | ፊልጵ 2፥6 |
| ማቴ 28፥19 | ዮሐ 5፥23 | 1ኛ ዮሐ 1፥5 | ያዕ 1፥17 |

4. ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ በሰማይም ካለው በምድርም ካለው ያለእርሱ ምንም ምን የሆነ (የተፈጠረ) የለም።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ 18፥1 ፤ 32፥6 | ዮሐ 1፥3 | ቈላ 1፥15 | ዕብ 11፥3 |

5. ስለ እኛ ስለሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሰው ሆነ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኢሳ 7፥14 | ሉቃ 1፥26 | ገላ 4፥4 | 1ኛጢሞ 2፥5 |
| ማቴ 1፥18 | ሉቃ 2፥39 | ዕብ 4፥14 | 1ኛጢሞ 3፥16 |

6. ሰው ሆኖ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ መከራን ተቀበለ፣ ታመመ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ። በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ 3፥5 ፤ 12፥15 | ሉቃ 24፥25 | ሐዋ 1፥11 | ኢሳ 45፥11 |
| መዝ 21፥16 | ማር 10፥33 | ሐዋ 4፥27 | ኢሳ 53፥4 |
| ማቴ 27፥57 | ማር 15፥42 | 1ኛጢሞ 3፥16 | ኢሳ 66፥1 |
| ማቴ 28፥5 | ዮሐ 3፥13 | 1ኛ ጢሞ 6፥13 | ዳን 9፥15 |
| ሉቃ 23፥32 | ዮሐ 19፥38 | 1ኛጴጥ 3፥18 | |

www.ethiopianorthodox.org

7. በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ፥ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፥ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፤ ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ 46፥5 | ሉቃ 1፥33 | ራእይ 22፥5 | 1ኛተሰ 4፥15-18 |
| ዳን 7፥13 | ሉቃ 24 | ሉቃ 22፥29 | 1ኛጢሞ 3፥16 |
| ኢሳ 9፥7 | ራእይ 5፥13 | ዮሐ 3፥13 | ዕብ 1፥1 |
| ማቴ 16፥27 | ራእይ 9፥24 | ሐዋ 1፥11 | 1ኛጴጥ 3፥22 |
| ማቴ 25፥3 | ራእይ 20፥11 | 1ኛቆሮ 15፥24 | |

8. ሕይወትን በሚሰጥ፥ ከአብ በሠረፀ፥ ከአብና ከወልድ ጋር የሚሰገድለት በነቢያት አድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ 1፥2 | ሕዝ 13፥1-7 | ዮሐ 4፥24 | 2ኛጢሞ 3፥14 |
| ኢሳ 6፥2-5 | ማቴ 28፥19 | ዮሐ 15፥26 | ኤፌ 4፥4 |
| መዝ 32፥6 | ሉቃ 24፥41 | ሐዋ 2፥21 | 1ኛ ጴጥ 1፥21 |
| መዝ 50፥11 | ማር 9፥31 | ሐዋ 4፥25 | 2ኛጴጥ 1፥20 |
| መዝ 15፥8 | ማር 12፥36 | ሐዋ 28፥25-28 | 1ኛዮሐ 5፥7 |

9. ዓለም ዓቀፋዊትና ሐዋርያዊት በሆነች በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን እናምናለን።
ማቴ 16፥18 ኤፌ 5፥25 ፤ 4፥1 ማቴ 28፥18 ኤፌ 2፥20

10. ኃጢአትን ለማስተስረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

| | | |
|---|---|---|
| ዮሐ 3፥1-11 | ሐዋ 2፥38 | 1ኛቆሮ 10፥1 |
| ማር 7፥3 | ሐዋ 11፥16 | ኤፌ 415 |
| ማር 16፥16 | ሮሜ 6፥1-4 | ዕብ 6፥1 |

11. የሙታንን መነሳትና የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን። ለዘላለሙ አሜን።

| | | |
|---|---|---|
| ዳን 12፥2 | ማቴ 25፥31-46 | 1ኛተሰ 4፥13 |
| ማቴ 13፥43 | ሉቃ 20፥27 | ፊልጵ 1፥19-21 |
| ማቴ 22፥30 | 1ኛ ቆሮ 15፥35 | ራእይ 20፥11-15 |
| ማቴ 24፥36 | 2ኛጢሞ 3፥14-17 | ራእይ 21፥1-4 |



## ፴፱. ከመናፍቃን እንዴት እንጠበቅ?

ቅድስት ቤተክርስቲያን መስራቿና መሪዋ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት የዋጃት፡ በማይፈርስ በጠንካራ ዓለት ላይ የመሰረታት፡ ሐዋርያት ፅንፍ እስከ ፅንፍ የሰበኳት፡ ቅዱሳን አባቶቻችን ሰማዕታት በአጥንታቸው ክስካሽ በደማቸው ፍሳሽ ያኖሯት የሰማይ ደጅ፡ የቅዱሳን ማረፊያ፡ የድሆች መጠጊያ፡ የምሕረት መገኛ ናት። ማቴ 16፥18

ስለዚህ ከእውነተኛዪቱ ቤት አስወጥቶ ሰዎችን ወደ ክህደት መንገድ ለመምራት የሚሯሯጡ ቀሳጢ ተኩላዎች መናፍቃን በየጊዜው አልጠፉም። ማቴ 7፥15 ዛሬም ሐሰተኛና ምትሐታዊ ተአምራትና ምልክት በማድረግ ብዙዎች የዋሃንን ወደ አስቡት የጥፋት ጎዳና እየመሩና እያሳቱ ይገኛሉ። 2ኛ ተሰ 2፥10-15

| | | |
|---|---|---|
| ማቴ 7፥15 | ገላ 1፥6-9 | 1ኛጢሞ 5፥8 ፤ 6፥12 |
| ማቴ 24፥4 | ኤፌ 5፥5 | 2ኛጢሞ 3፥13 |
| ሮሜ 16፥17-20 | ኤፌ 6፥10 | ቲቶ 3፥9 |

በተለይም ደግሞ የእውነተኛ አገልጋዮችን መነከሳትና ካህናት ልብስ በመልበስ፥ ቆብ በማጥለቅ፥ መስቀል በመያዝ እንደ ተኩላ ከበጎች ጋር በመቀላቀል፥ ተመሳስለው በመቅረብ፤ የጸሎትንና የጾምን ሥርዓት በማፍለስ "ምናለበት" በሚል አነጋገር አማኙ በጥርጥር ንፋስ እንዲወሰድ በሚያቆላምጥ ንግግር በመቅረብ እንደ እባብ የክህደት መርዛቸውን እየረጩ ይገኛሉ። ሮሜ 16፥18

ታዲያ በእውነተኛዪቱ ቤተክርስቲያን ጥላ ስር ተሰባስበን የምንገኝ እኛ ክርስቲያኖች ከእምነታችን ከቅዱሳን እቅፍ ሳንወጣ ከተጣራጣሪዎች ትምህርት በመጠበቅ የዓለምን ፈተና በፅኑ ሃይማኖታዊ ተጋድሎድል አድርገን ለሰማያዊት ርስት ለመንግስተ ሰማያት መብቃት ይኖርብናል።

ለዚሁም ቸሩ አምላካችን በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ልመና ይርዳን።

ይቆየን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

<u>ዋቢ መጻሕፍት</u>


- ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ፤ በብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
- ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ፤ በብጹዕ አቡነ ገብርኤል
- ክርስቲያናዊ ሰነ ምግባር ፤ በብጹዕ አቡነ መልከጼዴቅ
- ኩኩሐ ሃይማኖት ፤ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ
- እምነትና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ፤ በአባ ኃይለ ገብርኤል ግርማ
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ፤ በጠ/ ቤተክህነት
- ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም ፤ በጠ/ ቤተክህነት
- ዓምደ ሃይማኖት ፤ ብርሃኑ ጎበና
- ኒቂያ ፤ ብሩክ ዘውዴ
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
- ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ ፤ በቀሲስ ደጀኔና በቀሲስ እሸቱ
- የመናፍቃን ማንነትና መልሶቻቸው ፤ በዲ/ን አሐዱ አስረስ
- ሐመር መጽሔት እና መለከት መጽሔት
- የተለያዩ አባቶች ትምህርቶችና ስብከቶች




www.ethiopianorthodox.org